# ወልቂጤ ዩንቨርሲቲ

## የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

'' እንሳሮ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን እና ከእንስታዊነት እንቤ አንጻር''


በ

ታለማ ደጉ

የጥናቱ አማካሪ

ሸኩር ናስር


ነሐሴ 2013

# “እንሳሮ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን እን ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር”

በ

ታለማ ደጉ

የጥናቱ አማካሪ

ሸኩር ናስር

ለአርትስ ኦፍ ባችለር ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ወልቂጤ ዩንቨርሲቲ ነሐሴ 14/12/2013

## የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በወልቂጤ ዩንቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለው

የአማካሪው ስም ....................................

ፊርማ..............................................

ቀን............................................

ይህ ጥናት በታለማ ደጉ እንሳሮ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን እና ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር በሚል ርዕስ የተሰራዉን የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጽሁፍ ዩኒቨርሲቲዉን ጥራት ደረጃ ያሟላ እና ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት መሆኑን ማረጋገጫ ነዉ።ይህም በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል።

ፈታኝ አንድ

ስም ..............................................

ፊርማ .........................................

ቀን...........................................

ፈታኝ ሁለት

ስም ...........................................

ፊርማ .........................................

ቀን ...............................................

# ምስጋና

በቅድሚያ ጥንካሬ እና ብርታት ለሆንከኝ ላንተ ለመድሃኔአለም ክብርና ምስጋና ይግባልኝ።በተጨማሪም ይሄን ጥናታዊ ጽሁፍ በምሰራበት ወቅት ምክር በመስጠት፣ስህተቴን በማረም እና በጥቆማ በማስተካከል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ለረዳኝ ለማካሪዬ መምህር ሽኩር ናስር አክብሮት እና ምስጋናየ ከልብ ነዉ፣ እንዲሁም ጓደኛዊ እና ወንድማዊ ምክር በመስጠት ከጎኔ ላልተለይኝ ለዮርዳኖስ ገረመዉ እና ለጥናቱ የሚሆኑ መስሪያ መሳሪያዎች እንዳይቸግሩኝ ላመቻቸልኝ ለሚካኤል ጌታቸው እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

# አበርክቶ

ለአባቴ ደግሽ እና ለእማየ ዞማነሽ ይሁንልኝ

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የእንሳሮ ፊልምን ከዝግጅት አላባዉያን አንጻር እና ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር በሚል የቀረበ ነዉ።ስለሆንም የእንሳሮ ፊልም ከዝግጅት አንጻር የተለያዩ ግብዓቶች አሉት እነሱም ካሜራ፣ ትወና፣ምስል ቅንብር፣አልባሳት፣ጭብጥ፣ቃለ ምልልስ፣መቼት፣ግብዓት ብርሃን፣ድምጽ፣ገጽ ቅብ ናቸዉ። አጥኝዉም እነዚህን አላባዉያኖች ተንትኗል። ከእንስታዊነት፣ከራዲካል እንስታዊነት እሳቤ እና ከሴት ገጸ ባህርያት አንጻር ተንትኗል። የጥናቱ አላማ እንሳሮ ፊልምን የተስተዋሉ ደካማ እና ጠንካራ ጎን መዳሰስ ነዉ። አላማዉን ለማሳካትም የተጠቀመዉ የጥናት አይነት ገላጭ የምርምር አይነት ሲሆን የመዛግብት እና የመረጃ ትንተና እንዲሁም ምልከታ አካሂዷል።በዚህ በተገኘዉ መረጃም እንሳሮ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን እና ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር ምን እንደሚመስል ተንትኗል። ስለሆነም እንሳሮ ፊልም የፊልም ዝግጅት አላባዉያኖችን የገመገመበት ነዉ።

# ማውጫ

ምስጋና ........................................................................................................ III

አበርክቶ ........................................................................................................ IV

አጠቃሎ ........................................................................................................ V

ምዕራፍ አንድ ........................................................................................................ 1

1 መግቢያ ........................................................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................................ 2

1.2 የጥናቱ አላማ ........................................................................................................ 2

1.2.1 አብይ አላማ ........................................................................................................ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................................................ 2

1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች ........................................................................................................ 2

1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................................................................................ 3

1.6 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................................................ 3

1.8 የጥናቱ አወቃቀር ........................................................................................................ 4

1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................................................................................ 5

ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................................ 6

2.የንድፈ ሃሳብ እና የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ........................................................................................................ 6

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ........................................................................................................ 6

2.1.1 የፊልም ምንነት ........................................................................................................ 6

2.1.2 የፊልም ዝግጅት ምንነት ........................................................................................................ 6

2.2 የእንስታዊነት ምንነት ........................................................................................................ 16

2.2.1 ሊበራል ፌሚኒዝም ........................................................................................................ 16

2.2.3 ጀንደር ፌሚኒዝም ........................................................................................................ 17

2.3 የእንስታዊነት እሳቤ ባህርያት ........................................................................................................ 17

2.4 የገጸባህርያት ምንነት ........................................................................................................ 18

2.5 የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃ ........................................................................ 18
2.5.1 አካላዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃ ................................................................ 19
2.4.2 ማህበራዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል ....................................................................... 19
2.4.3 ስነ ልቦናዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል ..................................................................... 20
2.5 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ..................................................................................... 20
ምዕራፍ ሶስት ........................................................................................................... 22
መረጃ ትንተና .......................................................................................................... 22
3.1 የእንሳሮ ፊልም አጽመ ታሪክ ................................................................................. 22
3.2 የእንሳሮ ፊልም ከምስል ቀረጻ አንጻር ..................................................................... 24
3.2.1 እጅግ በጣም የሩቅ ምስል ቀረጻ(Extreme long shot) ................................................ 24
3.2.2 እጅግ በጣም የቅርበት ምስል ቀርጻ(extreme clouse up) ........................................... 25
3.2.3 የቅርብ ዕይታ ቀረጻ (clouse up) ........................................................................ 26
3.2.4 የሩቅ ቀረጻ(Long shot) .................................................................................. 27
3.2.5 ከትከሻ በላይ ቀረጻ ......................................................................................... 28
3.2.6 pov (point of view) ....................................................................................... 29
3.2.7 የቅርብ ዕይታ ቀረጻ (clouse up) ........................................................................ 30
3.3 እንሳሮ ፊልም ከቀረጻ ማዕዘን አንጻር ..................................................................... 31
3.3.1 የዝቅተኛ ማዕዘን ቀርጻ ..................................................................................... 31
3.3.2 የከፍተኛ ማዕዘን ቀረጻ (high angle) .................................................................. 32
3.3.3 የሰያፍ ማዕዘን ቀረጻ (oblique) ......................................................................... 33
3.3.4 የወፍ ዕይታ ቀረጻ ማዕዘን ................................................................................. 34
3.3.5 ልከኛ የቀረጻ ማዕዘን ...................................................................................... 35
3.4 እንሳሮ ፊልም ከብርሃን አጠቃቀም አንጻር ................................................................ 36
3.5 እንሳሮ ፊልም ከሙዚቃ እና ድምጽ አጠቃቀም አንጻር ................................................... 38
3.7 እንሳሮ ፊልም ከፊልም ቅንብር አንጻር ..................................................................... 42
3.8 እንሳሮ ፊልም ከገጽ ቅብ አንጻር .......................................................................... 43
3.9 እንሳሮ ፊልም ከአልባሳት አንጻር ......................................................................... 44

3.10 እንሳሮ ፊልም ከመቼት አንጻር........................................................................ 46
3.11 እንሳሮ ፊልም ከ ቃለ ምልልስ  አንጻር................................................................... 47
3.12 እንሳሮ ፊልም ከጭብጥ አንጻር ........................................................................... 48
3.13 በእንሳሮ ፊልም ዉስጥ የሴት ገጸ_ባህርያት አሣሣል ትንተና .......................................... 49
3.14 እንሳሮ ፊልም ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር ....................................................... 51
3.15 በእንሳሮ ፊልም ዉስጥ ያሉ ሴት ገጸ ባህርያት ከራዲካል ጽንሰ ሀሳብ አንጻር ምን ይመስላል ?.... 54
ምዕራፍ አራት ..................................................................................................... 55
4 ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ.............................................................................. 55
4.1 ማጠቃለያ ........................................................................................................ 55
4.2 የመፍትሄ ሃሳብ.................................................................................................. 56
ዋቢ መጽሃፍት
አባሪ

# ምዕራፍ አንድ

## 1 መግቢያ

በኪነጥበብ ዉስጥ ከምናገኛቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ፊልም ሲሆን በገሃዱ አለም የምናገኛቸው የምናደርጋቸዉ የምናያቸዉ የምናስባቸዉ ድምር ዉጤት ነዉ። ጳዉሎስ አዕምሮ "የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ" በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያብራራል። "የኢትዮጲያ ፊልም ዕይታ (የመታደም)ታሪክ የጀመረው በኢትዮጵያ የቴክኖሎጅ ትዉዉቅን መሰረት በማድረግ ሲሆን የሙብራት የስልክ የትራንስፖርት እና ሌሎች የኢንዱስትሪ አዉታር መነሻ የሆኑ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች በሃገሪቱ ሲተዋውቅ የፊልም ጥበብም በአዉሮፓ በተቀመረበት አጭር ጊዜ ዉስጥ በ1888 አ ም በሰኔ ወር አጼ ምኒሊክ እስቴቨን ሰው ጋር ባደረጉት ዉይይት የሲኒማን መፈጠር እና የሲኒማን ጥቅም ሊረዱ በመቻላቸው የፊልሙ ጥበብ በአስችኩዋይ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ እና ለህዝቡ እንዲተዋወቅ ታዕዛዝ ሰጡ ።በዚህም መሰረት በ1889 ዓ.ም የመጀመሪያው ፊልም እና ፊልሙ የሚታይበትን ምስል አንጸባራቂ ወደ ሃገር ውስጥ አስገባ።" (2010፤23)

እንዲሁም ወሰን የለህ ጥላሁን "የፊልም ጥበብ ቅኝት" በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ሃሳቡን ያጠናክርልናል። "ፊልም ማንኛዉንም የምናስበዉን ነገር የመወከል ብቃት ሲኖረው ጊዜን ወደ ኋላ ወይም ወደእንዲፈጥን ማድረግ አቅም ያለው የጥበብዘርፍ ነው።የማይታይና የማይዳሰሰዉን ፍንትው አድርጎ ያሳየናል።ምትሃት መሳይ ታዕይንት በአየር ዉስጥ ሲምዘገዘግ ወይንም የአበባ እምቡጥ እስኪፈነዳ ያለው ረጅም ሒደት በሰከንዶች ውስጥ ታጭቀው ግልጽ በሆነ መልኩ ያስመለክተናል።ይህ የጥበብ ዘርፍ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቶ ባሻዉ መልክ ማቅረብ ከመቻሉም በላይ ነገሮችን እዉን የማድረግ የላቀ ብቃት ያዘለ መሆኑ የበለጠ ተፈላጊነቱን ሲያጠናክር ፍሰት ያለዉ ትእይንት ድምጽና እንቅስቃሴ የአሁንነትና የዚያዉነት ደስታን ስለሚፈጥር ተመልካቹን በሲኒማው ሂደት ዉስጥ በተመስጦ ይጨምረዋል።ስለሆነም በፊልም አማካኝነት የሚከሰተው ሰመመን የእዉናዊዉን ዓለም ቅርጽና ስሜት መምሰል ከመቻሉም በላይ የፊልም ሁኔታና አቀራረብ የዉስጥ ስሜትን አዉጥቶ ከማሳየት አካላዊ ጀብዱዎችን እስከማቅረብ ይዘልቃል።ከዕይታ አንጻር አኳያም ስሜታዊ ከሆነው እስከሚዳሰሰው ያለውን ሰፊ ልዩነት እሸፍናል።"(ወሰን የለህ ጥላሁን ህዳር 2009)

ከዚህ በመነሳትም አጥኚዉ ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን አንጻር ይሰራል።በዚህም መሰረት ጳዉሎስ አዕምሮ የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ በሚለው መጽሃፉ ስለፊልም ዝግጅት አላባዉያን እንዲህ ያብራራል። "የፊልም ዝግጅት በጽሁፍ የተቀመጠን ታሪክ በምስል እና በቅንብር ሃይል የመተርጎም ጥበብ ነው።ሆኖም በምስል ሃይል ታሪክን ለመተረክ ደግሞ የፊልም ዝግጅት አላባዉያንን ጠንቅቆ ማወቅ የግድ ነው።"

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አጥኚው "እንሳሮ"የተሰኘዉን ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን እና ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር ለመስራት ያነሳሳዉ ምክንያት ይህ ፊልም የዝግጅት አላባዉያኖችን በሚገባ ተጠቅሟል ወይ?የሚለውን ሂሳዊ ትንተና ለመስጠትና በዚህ ፊልም ላይ ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር ሴት ገጸ ባህርያት እንዴት ተስለዋል ?በምን መልኩ ተስለዋል?የሚሉትን በመገምገም እና ይህ ፊልም ለዕይታ የበቃው ቅርብ ጊዜ ከመሆኑ አንጻርና በዚህ ፊልም ዙሪያ ጥናታዊ ጽሁፍ ተሰርቶ ያልተመለከተ በመሆኑ የፊልሙን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን ለመገምገም በመነሳሳቱ ነዉ።

## 1.2 የጥናቱ አላማ

### 1.2.1 አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አብይ አላማ እንሳሮ የተሰኘዉን ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን እና ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር ትንተና መስጠት ነው።

1.2.2ንዑስ አላማ

- እንሳሮ በተሰኘዉ ፊልም ዉስጥ ያሉ ሴት ገጸ ባህርያትን ከገጸ ባህርያት አሳሳል ትንተና ምስጠት
- እንሳሮ ፊልም ከራዲካል እንስታዊነት እሳቤ አንጻር መተንተን ነዉ።

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከዚህ በኋላ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ለሚሰሩ አጥኝዎች እንደ ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል። እንዲሁም ስለ ፊልም አዘገጃጀት ዘዴ እዉቀትን ለሚሹ እንደ መንደርደሪያ ሐሳብ እንዲሆን እና ከዚህ በኋላ ለሚሰሩ የፊልም አዘጋጆች ጠንካራ ጎንን እንደ እንደ ማስተማሪያ ደካማ ጎንን እንደ ክፍተት በመዉሰድ የተሻለ ፊልም ለመስራት ያስችላል። እንዲሁም ሴቶች ለማህበርሰቡ ያላቸዉን ቦታ ለማሳየትና ሴቶች ከወንዶች እኩል አቅም እና ችሎታ አላት እንዲሁም ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንደምትችል ለማህበረሰቡ ያስገነዝባል ።

## 1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች

- እንሳሮ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን መስፈርቶች አንጻር እንዴት ተዘጋጅቷል?

- ፊልሙ ከእንስታዊነት ጽንስ ሃሳብ አንጻር እንዴት ተገልጿል?
- በዚህ ፊልም ዉስጥ ሴት ገጸ ባህርያት በምን አይነት መልኩ ተስለዋል

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረቱን የሚያደርገዉ እና የሚያተኩረው እንሳሮ የአማርኛ ፊልም ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን አንጻር ማለትም ከካሜራ፣ከገጽ ቅብ፣ከግብአተ መብራት፣ከግብዓተ ድምጽ፣ከትወና፣ከመቸት፣ ከታሪክ፣እና አልባሳት ጽንስ ሃሳብ በማዛመድ የፊልሙን ዝግጅት ይተነትናል።እንዲሁም ከእንስታዊነት ጽንስ ሃሳብ ጋር አያይዞ ከራዲካል እንስታዊነት እና ሴት ገጸ ባህርያትን ብቻ ከ ገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃዎች ማለትም ከ አካላዊ፣ማህበራዊ፣ስነልቦናዊ እና ሞራላዊ ጽንስ ሃሳብ ጋር አዛምዶ ፊልሙን ይተነትናል።

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

አጥኚዉ ይህን ጥናት ሲሠራ ገላጭ የምርምር ስልትን መሰረት አድርጎ ሰርቷል ። ምክንያቱም በፊልሙ ዉስጥ የታዩትን መልካም እና ደካማ ጎኖች ልንገልጻቸው ወይም ልናሳያቸው የምንችለው በማብራራት እና ምክንያታዊ በሆነ ገለጻ ነው። ያለው እንግዳ አወቅ ሙሉ "የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር" በሚለው መጽሃፉ ላይ ስለ ገላጭ የምርምር ዘዴ እንደሚከተለው አስቀምጧል።

> ''ገላጭ ምርመር ከስሙ እንደምንረዳው ተመራማሪው አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን እንደሆነ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ በትርካዊ መንገድ የሚቀርብበት ነው። ገላጭ ምርምር በጣም ጠቃሚ የሆነ መረጃ ሊገኝበት የሚችል ጥሩ የምርምር አይነት ነው። በተለይ ወደፊት በዚያ ዙሪያ ሰፋ ያሉ ምርምሮች የሚካሄዱ ከሆነ የችግሩን መልክ ለመለየት ና የምርምሩን አቅጣጫ ለመወሰን ያስችለናል።''

አጥኚዉ ይህን የጥናት ዘዴ መሰረት በማድረግ ፊልሙን ደጋግሞ በመመልከት እንዲሁም በፊልም ዙሪያ የተጻፉ መጽሃፍትን በማንበብ፣የተዛማጅ ጽሁፎችን ቅኝት በማድረግ በተጨማሪም ከተለያዩ ድረ ገጾች በማሰስ ጥናቱን ሰርቷል።

### 1.6.1የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

## 1.6.1.1 መዛግብት

አጥኝው ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሰራ መዛግብት የተሰኘዉን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መሰረት አድርጎ ተነስቷል። መዛግብት ማለት በቤት መዘከር የሚገኙ የታሪክ መዛግብት፣መጽሃፍቶችን ፣መጣጥፎችን ፣ ጋዜጦችን፣መጽሄቶችን ሲሆን መዛግብት መርማሪዉን ስላለፈው ይሁን በወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸዉ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸዉ።መዛግብት በጽሁፍ መልክ ከቤተ መጻህፍት፣ቤተ መዛግብት ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎች እና እንደ ሁኔታው ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ስለሆነም  በዚህ መሰረት አጥኝዉ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በማሰስ ማለትም ከቤተ መጽሃፍት በተገኙት መጻህፍት እና መረጃዎች ፣ከማህበራዊ ድህረ ገጽ በተለጠፉት መረጃዎች፣ፊልሙን በተደጋጋሚ ምልከታ በማድረግ ጥናቱን ለመስራት ችሏል።

## 1.8 የጥናቱ አወቃቀር

አጥኚዉ ይሄን ጽሁፍ ሲያዘጋጅ በአራት ምዕራፎች ከፋፍሎ የሚያዋቅር አዋቅሯል።በዚህም መሰረት በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ ዓላማ፣የጥናቱ ንኡስ አላማ፣የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ፣ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ አወቃቀር ያቀፈ ምዕራፍ ነው።

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት እና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ማለትም ስለ ፊልም ዝግጅት ምንነት፣ የፊልም ዝግጅት አላባዉያን ማለትም የካሜራ ቀረጻ፣ግብዓተ ሙብራት፣ግብዓተ ድምጽ፣አልባሳት፣ገጽ ቅብ፣ ፊልም ቅንብር፣ትወና፣ሙዚቃ ግብዓት፣ጭብጥ፣መቼት፣ቃለተዉኔት እንዲሁም ስለ እንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ፣ራዲካል እንስታዊነት፣ጀንደር እንስታዊነት፣ሊበራል እንስታዊነት፣የእንስታዊነት መለያ ባህርያትና እንዲሁም ስለ ገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃዎች ምንነት የተብራሩበት ምዕራፍ ነዉ።

በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ዋና አላማ የሚሰፍርበት ምዕራፍ ነዉ።ማለትም በምዕራፍ ሁለት ከተገለጹት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር በማያያዝ እና በምዕራፍ ሁለት ላይ በተሰጠዉ ገለጻ መሰረት እንሳሮን ፊልም የተተነተነበት ምዕራፍ ነዉ፣

እንዲሁም በምዕራፍ አራት ላይ የጥናቱ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች የሚሰፍርበት ምዕራፍ አድርጎ አዋቅሯል።

## 1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አጥኚዉ የገጠመዉ ቢኖር በተደራራቢ ስራዎች ምክንያት የጊዜ እጥረት አጋጥሞታል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.የንድፈ ሃሳብ እና የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

## 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የፊልም ምንነት

በኪነ_ጥበብ ዉስጥ ከምናገኛቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ፊልም ሲሆን ፊልም በገሃዱ አለም የምናገኛቸው፣የምናያቸው፣የምናደርጋቸው፣የምናስባቸው....ነገሮች ድምር ዉጤት ነው።ይሄንን ሃሳብም ወሰን የለህ ጥላሁን "የፊልም ጥበብ ቅኝት" በሚለው መጽሃፉ ላይ ያጠናክርልናል። "የፊልም ጥበብ በምስሎች አማካኝነት ለተደራሲያን ታሪክ የሚነገርበና መልዕክት የሚተላለፍበት የሰው ልጆች ኪነ ጥበባዊ ተግባብቦት መንገድ ነው።አብዛኛዉን ጊዜ ታሪኩ የሚነገረው በድርጊት እና በምስል ላይ ተመስርቶ ስለሆነም የፊልሙ ጥበብ ዕይታዊ ጥበብና ህሊናዊ የሆኑ ረቂቅ ሃሳቦች ፣አመልካከቶች ፣ተጨፍልቀዉ የተለያዩ ስሜቶች ወደ ተጨባጭ ምስልና ድምጽ የሚተረጎምበት የፈጠራ ሂድት ነው ።

የፊልም ጥበብ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አሳማኝ የሆኑ ምክንያቶችን በማቅረብ ተመልካቹ የአመለካከት የግንዛቤ እና የባህሪ ለዉጥ እንዲያመጣ የማስቻል ተጽዕኖ የመፍጥር አቅም አለዉ።የፊልም ጥበብ ኪነ ጥበባዊ አገላለጽ የተለያዩ የፈጠራ መንገዶችን በመጠቀም የአንድን ማህበረሰብ ባህል የሚያሳዩ አስተሳሰቦችና፣አመለካከቶች፣እሴቶችና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲሁም የተለያዩ ትዉን ጥበባትን ያቀርብልናል።እንዲሁም ፊልም ማንኛዉንም የምናስበዉን ነገር የመወሰን ብቃት አለው።ጊዜን ይጎትታል ወይም እንዲፈጥን ያደርጋል፣እናም የማይታይና የማይዳሰሰውን ይገልጣል።"(2009፤3)

### 2.1.2 የፊልም ዝግጅት ምንነት

ዝግጅት ማለት አንድን ነገር ብቁ ለማድረግ የሚሰራ ቅድመ ሂደት ነው ።የፊልም ዝግጅትም ፊልሙ ብቁ ሆኖ ለተመልካች እስኪቀርብበት ያለዉን ሁኔታ አካቶ ያዘለ ነዉ።ጳዉሎስ አዕምሮ "የፊልም ዝግጅት ምንነት"በሚለው መጽሃፉ ላይ ሃሳቡን እንዲህ ይጋራል።የ "ፊልም ዝግጅት ከፊልም ጽሁፍ መረጣ ጀምሮ ፊልሙ ተሰርቶ ለተመልካች እስኪቀርብ ያለዉን የቀረጻ ፣መብራት፣ቦታ መረጣ,፣ትወና ግብዓት ድምጽ፣ በአጠቃይ በፊልሙ ሂደት ዉስጥ ያሉትን ዝግጅት አካቶ ለተመልካች የሚቀርበበት ሂደት ነው።የፊልም ጽሁፍ በሰው ልጆች ተጠንቶ ተተዉኖ እና በአዘጋጁ የማቀናበርያ ክህሎት ተቀናብሮ እና ህልዉና አግኝቶ ፊልም በመሆን ለዕይታ የሚቀርብበት መንገድ ዝግጀት እንለዋለን።በአጠቃላይ የፊልም ዝግጅት በፊልም ሂደት ዉስጥ ያለ ለፊልሙ የሚያስፈልጉ ሁሉ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸዉ።ማለትም ፊልሙ ሲዘጋጅ ቀረጻ፣

ቅንብር፣ግብዓት ድምጽ፣መብራት፣ቦታ መረጣ፣በአጠቃላይ በፊልም ጉዘት ዉስጥ ያሉትን አካቶ የሚይዝ ነዉ።እንዲሁም በጽሁፈተ ፊልም ዉስጥ የተገለጹትን ታሪኮች በተንቀሳቃሽ ምስል ቀራጭ እና በተንቀሳቃሽ ምስል ቅንብር አማካኝነት በፈጠራ ክህሎት የማቅረብና የመተርጎም ጥበብ ነዉ።”(2010፤ )

## 2.1.3.1 የፊልም ዝግጅት አላባዉያን

የፊልም ዝግጅት አላባዉያን ማለት አንድን ፊልም ሙሉ እና ትዓማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ እንደ አጋዥ እና ተራዲ ግብዓት የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች ናቸው።ዪህ ማለት አንድን ቤት ለማቆም እና ጠንካራ ለማድረግ የተለያዩ ጥሬ እቃዎች ከሌሉ ቤቱ ቤት እንደማይሆን ሁሉ ፊልምም ያለ እነዚህ አላባዉያን ነፍስ የሌለው ነው ማለት ነው ።ስለሆነም ፊልሙን እዉናዊ እና ተአማኒ ለማድረግ እነዚህ አላባዉያን አስፈላጊ ናቸው። ጳዉሎስ አዕምሮ “የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ” በሚለው መጽሃፉ ላይ ሃሳቡን እንዲህ ያስቀምጣል። “የፊልም ዝግጅት በጹሁፍ የተቀምጠን ታሪክ በምስልና እና በቅንብር ሃይል የመተርጎም ጥበብ ነው።በምስል ሃይል ታሪክን ለመተረክ ደግሞ የፊልም ዝግጅት አላባዉያንን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። አላባዉያን አንድ የስነጹሁፍ ወይም የኪን ጥበብ ስራ የተሰራበት ዋና ይዘታዊ ወይም ዉስጣዊ ነገሮች ናቸዉ።በፊልም ዝግጅት ዉስጥ ሁሌም ዉጤታማ አዘጋጆች የሚሰሩትን የቀረጻ ድርጊት በሙሉ ጽንስ ሃሳብ የፊልም ምርት የስራ ደረጃ አጠናቀዉ ዎደ ቀረጻ ይገባሉ።በዚህም የዝግጅት ተግባራቸዉ ዉስጥ ዋና ዋና የዝግጅት አላባዉያን ይካተታሉ ።እነዚህም የምስል ቀረጻ፣የቀረጻ ማዕዘን ፣ ግብዓተ መብራት ፣ሙዚቃ እና የድምጽ ግብዓት ፣ትወና፣የፊልም ትዕይንት ግንባታ እና የፊልም ቅንብር ናችው።”(2010፤56)

### 2.1.3.1.1 የምስል ቀረጻ

የምስል ቀረጻ አንድ ለታሪካችን ወይም ለምንሰራው ስራ ተዛማጅ እና አስፈላጊ የሆነን ምስል የምንቀርጽበት አንዱ አላባ ነው። ጳዉሎስ አዕምሮ “የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ”በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያስቀምጣል። “ይህ አላባ በፊልም ዝግጅት ዉስጥ አንድን የሚቀርጽ ምስል የዕይታ ማዕቀፍ የሚወሰን ነው ።የፊልም አዘጋጆች ለአንዳች ሁነኛ ጉዳይ ሃሳብ ገለጻ ለተመልካች የሚያሳዩትን የሰው ፣የግዑዝ አካል፣ የምናብ ገጸ ባህሪ ድርጊት በካሜራ ዕይታ ማዕቀፍ ዉስጥ በማስገባት የሚገልጹበት ሲሆን የፊልም ጽሁፍ ጸሃፊዉ ታሪኩን በጹሁፍ እንደሚተርከው ሁሉ የተዋጣላቸዉ የፊልምን አዘጋጆች ደግሞ እያንዳንዱን ታሪክ በምክንያታዊ የምስል ቀረጻ አይነት ምርጫ በሚገባ ያዋቅሩና ያቀርቡታል ።ተቀባይነት ተገቢና ምክንያታዊ ምስል ለመፍጠርም እያንዳንዱን ከዝግጅታቸዉ ትርጓሜ ጋር ያያይዙታል።የፊልም አዘጋጆች ለዝግጅት ትርጓሜአቸዉ የቀረጻ አይነቶችን ጥቅም ማዎቅ ብቻ ሳይሆን በካሜራ እና በግብዓት አማካኝነት የራሳቸዉን የተለየ ምስል የመፍጠር ክህሎት ሊያዳብሩ ይገባል።ይሄን ለማድረግ ደግሞ መነሻ

የሆኑትን አራቱን የምስል ቀርጻ አላባዉያን ከተፈጥሮ እና ከሚተርኩት ታሪክ ጋር በማያያዝ መተንተን ይኖርባቸዋል።እነርሱም የቅርብ እይታ ቀረጻዎች ፣የመካከለኛ ዕይታ ቀረጻዎች፣የሩቅ ዕይታ ቀረጻዎች ፣ እና የአጠቃላይ እይታ ቀረጻ ናቸው።(ጳውሎስ አዕምሮ) እንዲሁም እጅግ በጣም የቅርብ ቀርጻ EXTREAME CLOSE UP) ፣የሩቅ ቀረጻ (LONG SHOT) የመካከለኛ ርቀት ቀረጻ (MEDIMUE LONG SHOT)የቅርብ ምስል ቀርጻ (CLOSE UP)፣ከትከሻ በላይ የምስል ቀረጻ(OVER SHUOLDR SHOT) የመካከለኛ ቅርበት ቀረጻና ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ምስሎች የማካተት ቀርጻ የተካተቱበት የአላባዉያን አይነት ነው ።"(2010፤57፤58)

- የቅርብ ዕይታ ቀረጻ ; በዚህ የቀረጻ አይነት አዘጋጁ ከአንገት በላይ ያሉትን እይታዎችን በመምረጥ እንደየአስፈላጊነቱ የተዋያኑን አትኩሮታዊ እንቅስቃሴ ለማሳየት የሚጠቀምበት ነው።በፊልሙ ዝግጅት ዉስጥ የቅርብ እይታ ቀርጻዎች የጋራ የሆነ መነሻ ትርጓሜ ሊኖራቸዉ ቢችልም አዘጋጁ ግን እንደራሱ የታሪክ አረዳድና ዝግጅት ግብ ሊጠቀምባቸዉ ይችላል።የቅርብ ዕይታ ቀረጻ ትርጓሜዎችም የገጸባህርይን ስሜት ይገልጻሉ፣ዕይታን ለማጉላትና ፣ለማስረዳት በታሪክ ዉስጥ የልብ ሰቀላን ለመፍጠር የተሻለ የቀርጻ አዪነት ነው ።
- መካከለኛ የእይታ ቀረጻ በዚህ የቀረጻ ማዕቀፍ አይነት ዳይሬክተሩ የሰዉ ልጅ ቁስን እና የሚቀረጹ ማንኛዉንም አይነት ገጸ ባህርያትና ትዕይንቶችን በመካከለኛ የመቅረጽ ምስል ርቀት ማዕቀፍ የሚቀርጽበት የቀረጻ አይነት ነው።ትርጓሜዉም ተፍጥሯዊ የዕይታ ልኬት ይኖራቸዋል።ከርቀት በተሻለ መልኩ የድርጊት ትወናንን ይገልጻሉ።በከፊል የሰዉነት ክፍል የሚደረጉ ተተኳሪ ትወናዎችን በግልጽ ያሳዉቃሉ።
- የሩቅ ዕይታ ቀረጻ በአንድ ፊልም ዉስጥ የቦታን የጊዜንና ገጸ ባህርይን የጥምረት ትዕይንት ክንዉን በጥቅል ለመግለጽ የሚጠቅም የቀረጻ አይነት ነዉ።የዕይታ ማዕቀፉም ከርቀት የመቅረጸ ምስዕይታ የተቀናበረ እና በሌንሶች አማካኝነት በስፋት የሚቀረጽ ነዉ።ዪህ የቀርጻ አይነት ከርቀት ለተደራሲያን በመቸቱ ዉስጥ መረጃን ሳይመርጥ በጥቅል ያሳይበታል ።በፊልሙ ዉስጥ የታሪክ ተራኪ ዉስጥ ዕቂያ ለመስጠት የምንጠቀምበት የቀርጻ አይነት እና
የት?መቸ?ነዉ ታሪኩ የሚፈጸመዉ የሚለዉን ጥያቄ ይመልሳል።

- አጠቃላይ የዕይታ ቀረጻ ብዙ የፊልም አዘጋጆች ይህን የቀርጻ አይነት የድባብ መመስረቻ የታሪክ ጅማሬ ቀረጻ አድርገው ይዎስዱታል።አጠቃላይ የዕይታ ቀረጻ ከሩቅ የእይታ ቀረጻ ጋር ተመሳሳይነት አለዉ።በርቀት የአእይትራ ማዕቀፍን ወይንም መቸትን በማስተዋወቅ የሚመሳሰሉ ሲሆን ስሜትን መሰረት ያደረገ የዕይንት ፈጠራ ላይ ግን ይለያያሉ።በመሆኑም አጠቃላይ የቅርብ ዕይታ ቀረጻ

የፊልሙ ታሪክ የሚከናወንበት ቦታ ከነሙሉ ድባቡና ጽንፉ በማሳየት በተረጋጋና በተደጋጋሚ ዕይታ በተደራሲያን አዕምሮ ዉስጥ የታሪከን መከወኛ ቦታ ስሜትና ድባብ እንዲጋባባቸዉ ያደርጋል።በዚህም ባህሪው ከርቀት ዕይታ ዪለያያል።የዚህ የቀረጻ ዕይታ ጠቀሜታም የጊዜ ለዉጥዪገልጽበታል ፤የተፈጥሮን ለዉጥ ያሳይበታል፤የታሪኩን መከወኛ ቦታ ይገልጽበታል።

- ከትከሻ በላይ ቀረጻ  በዚህ የቀረጻ አይነት ዉስጥ ሁለት ምስሎች በምሰል ማዕቀፍ ዉስጥ ይካተታሉ።የመጀመሪያው ምስል በአትኩሮት ዉስጥ በመግባት ከአንደኛው ምሰል ጀርባ መነሻነት የሚካሄድ የቀረጻ አዪነት ነው ።የምስል ቀረጻው ከአንደኛዉ ገጸ ባህሪ ትከሻ አንጻር ትይዩ ሌላኛዉ ገጸ ባህሪ ያለዉን የትወና አትኩሮት ለማሳየት የሚረዳ የቀረጻ አይነት ነው። ጠቀሜታወች የሚከተሉት ናቸው።

  1.የሁለት ገጸ ባህርያትን የድርጊት ጥምረት ለማሳየት

  2 የምልልስ ትወናዎችን በአንደኛወዉ ገጸ ባህሪ  ትከሻ ጀርባ መነሻነት በምምልልስ በትኩረት ለማሳየት ዪረዳል።(ጳዉሎስ አዕምሮ ፤2005)

- በጣም የቅርበት ምስል ቀረጻ  በዚህ የቀረጻ አይነት የሚካሄደው ከተተኳሪው የሰው መይም የቁስ አካል ምስል በጣም የቀረበ ሁኔታን የሚቀርጽ ነው።በምስሉ በቅርበት የጎላ የአካል ክፍል ስሜቱን እና ያልተካተቱ የገጸባህሪዉን የአካል ወይም የቁስ ክፍሎች ምዕቀፍ አያደርም።በጣም የቅርበት ምስል ቀረጻ  ጥቅሞም በጣም በቅርበት ሊገለጹ የተፈለጉ ስሜቶችን በከፍተኛ ቅርበት ለመግለጽ ያስችላል።

- እጅግ በጣም የቅርበት ምስል ቀረጻ  በዚህ የቀረጻ አይነት የሚቀረጸው የሰው ወይም የቁስ ምስል የተወሰነ አካል ወይም ቁስ ክፍል ብቻ በምስል ማዕቀፍ ዉስጥ በማካተት ብቻ ነው።የሚካተተው የአካል ክፍል የጣት፤የእግር ፤ከፊል የፊት ገጽታ ወይም ከፊል የቁስ ገጽታ ነው።የዚህ የቀረጻ አይነት ጥቅሞችም ዉስን ስሜትና ድርጊትን በተወሰነ የአካል ክፍል ለማሳየት እና ትኩረት ማዕቀፍን በመወሰን ዉሰን  ነገር ብቻን ከዉስን አካል ጋር ለማሳየት ያገለግላል።

## 2.1.3.1.2 የቀረጻ ማዕዘን

የቀረጻ ማዕዘን ማለት ካሜራዉ ምስሉን የወሰደበት አቅጣጫ ወይም የቦታ ሁኔታ ማለት ሲሆን ይህም በሚሆን ጊዜ ትርጉም የሚሰጥ እና ምክንያታዊ መሆን  ይጠበቅበታል ፡፡ጳዉሎስ አዕምሮ “የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ”  በሚለው መጽሃፉ ላይ ስለቀረጻ ማዕዘን እንዲህ ያስቀምጣል። “በፊልም ዝግጅት ዉስጥ ማንኛዉም አዘጋጅ ጥሩ ዝግጅት ለማካሄድ የሶስት ነገሮች ቁጥጥር በሚገባ ያጤናል።

1 የምቅረጽ ምስል አቀማመጥና ለትዕይንቱ የተመተጠዉን የቀረጻ አይነት

2 የተዋናይ የትወና እንቅስቃሴ

3 የተዕይንቶች ቅንብር ከግብዓት አጠቃቅእም አንጻር ናቸው። እንዲሁም የተለያዩ የቀረጻ ማዕዘን አይነቶች አሉ እነዚህም

- የልከኛ ማዕዘን ቀረጻ  የፊልም አዘጋጅ መቅረጽ ምስል ማዕቀፍ የሚጠቃለለዉን የገጸ ባህርያት ሰዉነት ወይም የቁስ ክፍል በሰው ልጅ አይን ዕይታ ደረጃ የርቀት መጠን የሚቀረጽበት የመቀረጻ ምስል አይነት ነው ።
- የዝቅተኛ ማዕዘን ቀረጻ  አይነት የገጸ ባህርይን ሃያልነት ለማሳየት አዘጋጁ የሚመርጠው የምቅረጻ ምስል የቀረጻ ማእቀፍ ነው።የአንድን ገጸ ባህሪ የስራ ደረጃ ፤የስሜት ሁኔታ በፊልም ዝግጅት ዉስጥ ይህ የቀረጻ ታ ከሌሎች ገጸ ባህርያት ጋር ያለዉን የግንኙነት ደረጃ በአንድ ድርጊት ዉስጥ ለተደራሲያን ማስተዋዎቅ ሲፈልግ ይጠቀምበታል።(
- የከፍተኛ ማዕዘን ቀረጻ በዚህ የቀረጻ አይነት የአዘጋጁ የዝግጅት ትኩረት የሚሆነው በፊልም ታሪኩ ዉስጥ ያሉ ገጸ ባህርያት ያሉበትን የዝቅተኛ ስሜት ኑሮ።የድርጊት ደረጃ ከሌሎች ገጸ ባህርያት ወይም ከገቡበት ስሜት ጋር በማነጻጸር ለማሳየት ነው ።የህ የቀረጻ አይነት የሚያመላክተውም ተስፋ ቢስ መሆንን ፤የበታችነት ስሜት ፤ሽንፈትን፤ያልተጠበቀ ዱብዳን በፍረሃት መጠበቅ።አቅም ማጣትን፤ነገሮችን መቋቋም አለመቻል የመሳሰሉትን ስሜቶች ይገልጹበታል።
- የወፍ ዕይታ ቀረጻ  ታሪኩ የሚፈጸምበት ቦታ እና የጊዜዉን ድባብ ከላይ ወደ ታች በወፍ ዕይታ ማዕቀፍ ለማሳየት የምንጠቀምበት የቀረጻ አይነት ነው ።ይህ የቀረጻ አይነት በሄሊኮፍተር፤ በአዉሮፐላን ወይም በብራሪ ቁስ አካል በመጠቀም በከባድና ቀላል መቅረጽ ምስል አማካኝነት ቀረጻዉን ያካሂዳሉ።ይሄም ያልተጠበቀ ክስተት ፤ፍርሃትን ፤ፍለጋን ፤ጊዜን ቦታን አልፎ መጓዝን ለመግለጽ የሚጠቅም የቀረጻ አይነት ነው።
- የሰያፍ ማዕቀፍ ቀረጻ  በመቅረጽ ምስል የሚቀረጸው ምስል ወደ ጎን ያጋደለ ነው።ምስሉ ከተለመደው የምስል አቀማመጥ በተለየ 40 ፐርሰንት ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ያጋድላል። አገልግሎቱም የተዛባ ፍርድን፤ያልተጠበቀ ጠማማ ምልሽ ፤ተቃወሞ ፤ውጣ ዉረድ የበዛበት ያልተስተካከለ ህይወት የስሜት መዛባት ፤ስካር፤ንዴት፤መደናበርን፤ለማሳየት ይጠቅማል።"(2010፤ 91-99)

## 2.1.3.1.2 የብርሀን ስርጭት

መብራት ማለት በእለት ተዕለት ኑሯችን ብረሀን የሚለዉን  ትርጓሜ የሚሰጠን ሲሆን ይህም በቀን እና በማታ እንዲሁም በሁነቶች የሚፈጠር ይሆናል ፤ ይህም ማለት በቀን ከፀሀይ በተፈጥሮ የሚናገኘዉ

ብረሀን አንዱ ሲሆን በማታ ደግሞ በተመሳሳይ በተፈጥሮ ከጨረቃ እና ከከዋክብት የሚናገኛቸዉ ብረሀን ነዉ፡፡ በተጨማሪም በሰዉ ሰራሽ ዘዴ ብረሀን የሚፈጠር ሲሆን ለምሳሌ ኩራዝ፣ ሻማ፣ ፋኖስ፣ የአምፖል መብራት፣ እንዲሁም ሌሎች የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ ይሄን

ሃሳብም ወሰንየለህ ጥላሁን “የፊልም ጥበብ ቅኝት” በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያስቀምጣል። “የሰው ልጅ አይን ለማየት ብርሀን ያስፈልገዋል።በፊልም ቀረጻ ውስጥም የመቅረጽ ምስል አይን ነገሮችን በተገቢው መንገድና መጠን እንዲመለከት ብርሀን ያስፈልገዋል።ወሰን የለህ ጥላሁን የፊልም ጥበብ ቅኝት በሚለው መጽሃፉ ላይ ስለ ርሃን ስርጭት እንዲህ ያስቀምጣል።የብርሃን ድምቀት አቅጣጫና ስርጭት በመቆጣጠር አዘጋጁ ጥልቅ ስሜትን ፣ተመስጦ እና የተለያዩ ድባባዊ ዉጤቶችን መፍጠር ይችላል።ግልጽ የሆነ የብርሃን አጠቃቀም ልዩነት ለሚካሄደው ድርጊት የተለያዩ ስሜቶችንና ድባቦችን ይፈጥራል።የተለያዩ የብርሀን አጠቃቅም ስልቶችም አሉ እነርሱም low key lighting and high key lighting ናቸው ።

- LOW KEY LIGHTING  አብዛኞችን የታሪክ አካባቢዎች በጥል ዉስጥ የሚቆይ ሲሆን አንደዚህ አዩነቱ የብርሃን ድባብ ልብ ሰቀላን እና የሃዘን ድባቦችን የምንፈጥርበት የብርሃን አይነት ነዉ።አብዛኛዉን ጊዜ በሚስጥራዊ እና አስፈሪ ፊልሞች ወስጥ ጥቅም ላይ ይዉላል።
- HIGH KEY LIGHTING  በተቃራኒዉ ከጥላማ ይልቅ በብርሀን የተሞላ አካባቢ ለመፍጠር ይዉላል።በዚህ በርሃን አጠቃቀም ሰዎች ወይም ነገሮች በመካከለኛ ደረጃ ግራጫማ እና ብራሃናማ ሆነው ይታያሉ።high key lighting በአስቂኝ እን በሙዚቃዊ ድባቦች ዉስጥ አገልግሎት ላይ ይዉላሉ።”(2005፤106)

## 4 ሙዚቃ እና የድምጽ ግብዓት2.1.3.1.

በፊልም ዝግጅት ዉስጥ አዘጋጁ በሚገባ ሊያዋቅራቸዉና ሊጠቀምባቸው የሚገቡ የፊልም ዝግጅት አላባዎች ናቸዉ።ድምፅ የምንለዉ በአከባቢያችን በተለያዩ ምክንያቶች ተፈጥሮ ወደ ጆሮኣችን የሚደርስ ድምፅ ማለት ነዉ፡፡ በፊልም ዉጥ ደግሞ የድምፅ ግብዓት ማለት በፊልሙ ዉስጥ የሚኖሩ ወይም የሚፈጠሩ በጆሮ የሚደመጡ ምንም ዓይነት ድምፆች ማለት ነዉ፡፡እነዚህ ድምፆች በፊልሙ ለሚከናወኑ ድርጊቶች እና ስሜቶች ህይወትን የሚዘሩ ይሆናሉ፡፡ ይህም ማለት በተዋንያን መካከል የሚደረጉ ምልልሶች፣ ድባቡን የሚያጠናክሩ ማጀቢያ ሙዚቃዎች፣ ሁነቶችን ፣ ክስተቶችን እና መቼትን የሚገልፁ ድምፆች ማለትም የዕቃ ግጭት፣ የኮቴ ድምፅ፣ የሙብረቅ፣ የዝናብ፣ ሌሎችም ዓይነት ድምፆች በትክክለዉ ሰዓት እና ቦታ ላይ ሲገኙ ማለት ነዉ።ጳዉሎስ አዕምሮ “የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ”በሚለው መጽሃፉ “ሙዚቃ በፊልሙ ታሪክ ላይ በመመርኮዝ የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም ለሙዚቃ ባለሙያ ፣በሙዚቃ ግጥም ጸሀፊ ፣በዜማ ደራሲ በሙዚቃ እና በአቀናባሪ አማካኝነት በሚገባ የሚቀመር የፊልም ዝግጅት አንዱ አላባ እዉ።በፊልም ዝጅግት ዉስጥ አዘጋጁ ፊልሙን ጽሁፍ በመተንተን በተገነዘበዉ መሰረት የተዋጣለት

የሙዚቃ ባለሙያ መርጦ የፊልሙን ጽሁፍ በማስገንዘብ እና የሚፈለገዉን የዝግጅት ስነ ስልት በማስረዳት የፊልሙ ሙዚቃ እንዲዘጋጅ ያደርጋል።

የፊልም ሙዚቃ ግብዓቶች ፤የማጀቢያ ሙዚቃ ፤የመሸጋገሪያ ሙዚቃ ፤የስሜትና የድርጊት መግለጫ ናችው።"(2010፤111-118)

## 2.1.3.1.5 ትወና

በጽሁፈተ ፊልም ዉስጥ በቃለ ተዉኔት በገለጻ እና በትረካ የተገለጸን ሃሳብ ወደ ድምጽና ክዋኔ የመለወጥ ዘዴ ነው።በፊልም ዝግጅት ወቅት የፊልም አዘጋጁ ተዋናዮችን በሚገባ ለትወና ማዘጋጀት አለበት።ይህን ሀሳብ ዘላለም ተፈሪ "የፊልም ትወና ጥበብ" በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያስቀምጣል ። "ትወና ሙያ ነው ሰወች በትያትር ፤በቴሌ ቪዥን ፤በፊልምና በሬዲዮ ።በመሰል የተለያዩ ታሪክን በሚተርኩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች ምናብ የተቀረጸ ገጸባህርያትን በመሆን የተጻፈ (ያልተጻፈም ሊሆን ይችላል።)ታሪክን በምስል እንቅስቃሴ በንግግር ፤በዘፈን ፤በድርጊት ፤ወዘተ ለተደርሲያን የሚተረክበት ኪነ_ጥበባዊ ሙያ ነው። (2010፤

እንዲሁም ወሰን የለህ ጥላሁን በዚህ ሃሳብ ላይ በዚህ መልኩ ያስቀምጣል ።አንድን ፊልም ለማየት ከመወሰናችን በፊት የምናነሳው የመጀመሪያው ጥያቄ አዘጋጁ ወይም ሲኒማቶግራፈሩ ማነው ?የሚል አይደለም እነማን ይሰሩበታል የሚል ጥያቄ ነው የምናስቀድመው ።ይህ ተፈጥሮአዊ ጥያቄ ነው ። ምክናያቱም ከሁሉም የተዋናዩ ጥበብ በግልጽ የሚታይ ነው።"(2005፤35)

## 2.1.3.1.6 የፊልም ቅንብር

የፊልም ቅንብር በዝግጅት ዉስጥ የፊልም አዘጋጁ ከቀረጻ በኋላ ከፊልም አቀናባሪዉ፤ከቀረጻ ክትትል ባለሙያ ጋር በጥምረት የሚሰራበት የፊልም አላባዉያን ዋና ቅንብር ክፍል ነዉ።ሰለሞን መኮነን "የፊልም ገበታ"በሚለው መጽሃፉ እንዲህ ያስቀምጣል። "የፊልም ኤዲቲንግ ከፊልም ቀረጻ በኋላ ያለ የፊልም ስሪው አንድ አካል ነው ።ፊልም ኢዲቲንግ የሚለው ቃል የተወሰደው ፊልምን ማረም ወይም ማስተካካል እንዲሁም አስፈላጊ ነገሮችን መጨመር የሚለዉን ሀሳብ የሚተካ ተደርጎ ነው።ፊልም ኤዲተሮች ተቀርጾ የመጣላቸውን ፊልም አንግሎች ፊልም አንግሎች ቅደም ተከተሎችን ድምጽና የምስል ጥራቱን ከግምት ዉስጥ በማስገባት የሚሰራ ስራ ነው ።ስለዚህ የፊልም ኤዲተር በአጭሩ በሲኒማ ኢንዱስትሪዉ ዉስጥ የግድ አስፈላጊና ከፊልም ስራው ሂደት ተነጥሎ የማይታይ ነገር ግን የተለየ ጥበባዊ እይታንና ችሎታን የሚጠይቅ ራሱን የቻለ ሙያ ነው ።በዚህም የተነሳ የፊልም ኤዲቲንግን የፊልም ባለሙያዎች እማይታየው ጥበብ በማለት ይጠሩታል።ምክንያቱም ፊልም ኤዲተሮች በፊልም ስራ ዉስጥ ለተመልካች የሚቀርብ ጉልህ ለእይታ ቦታ የላቸዉም።ፊልም ኤዲተር የተለየ ጥበባዊ ቴክኒካዊና ምስሎችን ሳቢ በሆን መልኩ

የመገጣጠም በተገቢው ቦታ እና ቅደም ተከተል የመደርደር እንዲሁም ምስሎችንና ድምጾችን የማከም እዉቀት ሊኖራችው ይገባል።በአጠቃላይ የኤዲተር ስራ ድምፆችን ከመቆራረጥ እንዲሁም ትዕይንቶችን ከማስተካካል በዘለለ ስነ ጥበባዊ የፈጠራ ብቃት ዉጤት ሊኖራቸው ይገባል።ኤዲተሩ ምስሉን በታሪኩ ታሪኩን ከቃለተዉኔቱ ቃለተዉኔቱን ከሙዚቃው ሙዚቃዉን ከአጠቃላይ የፊል ታሪኩ ፍሰት ጋር የማቀናጀትና ሳቢ የማድረግ ሚናን ይጫወታል።በአጭሩ ኤዲተር ፊልምን የሚሰራና ፊልምን ፊልም የሚያደርግ ታላቅ ባለሙያ ።ፊልም ኤዲተሮች በተለያየ ጊዜ እየተሻሻሉ የሚወጡ እና የሚፈጠሩ ፊልም መስሪያ ሶፍትዌሮችን በመጠቀምና ከረዳት ኤዲተሮችን ከዳይሬክተሩ ጋር በመቀናጀት የመስራት ሀላፊነት አለባቸው።ቀደም ባሉት አመታት የፊልም ኤዲተሮች ስራ ምስልንና ድምጽን ማቀናበር ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር ።አሁን ባለንበት ዘመን ግን ኤዲተሮች ከዚህም በዘለለ በርካታ ቪዥዋል ኢፌክቶችን የማካተት ሃላፊነት አለባችው።በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን በአነስተኛ ወጭ ለሚሰሩ ፊልሞች የፊልም ኤዲተሩ ምስሉንና ድምጹን ከማስተካከልና ከማከም በዘለለ ተጨማሪ ድምጾችንና ምሶችን በኮምፒውተር ፈጥሮ ያካትታል።በአጠቃላይ ኤዲተሩ የመጨረሻዉን የፊልሙን የድምጽና የምስል ጥራት የሙዚቃዉን የቪዥዋል ኢፌክቱን ጥምረት ከታሪኩ ፍሰት ጋር የማዋሃድ ሀላፊነት አለበት።የፊልም ኤዲቲንግ ስራ በተለያየ መልኩ ይሰራል ።በኤዲቲንግ የተለያየ መልኩ ይሰራል ።በኤዲቲንኝ ምስሎች እና ድምጾች እንዲጣመሩ ታዋናዩ ላይ በግልጽ የማይታዩ ስሜቶች ብቃቶች እና እንቅስቃሴወች ይፈጥራሉ።በቅንብር ትዕይንቶችንና ክስተቶች በተለያየ አንግል እንዲታዩ ማድረግ ይቻላል።በቅንብር የታሪኩን ነገራ ሂደት ማስተካከል የሌሉና ሊፈጠሩ የማይችሉ አደጋዎችን አስፈሪ ፍጡሮችን ፍንዳታዎች እንቅስቃሴዎችን ሳቢ በሆነ መልኩ ለተመልካች ያቀርባል።”(2007፤70-71)

## 2.1.3.1.7 ጭብጥ

ጭብጥ ማለት በአንድ ኪነ ጥበብ ዉስጥ ልናሳየው እና እና መልዕክት የምናስተላልፍበት ዋነኛ አንኳር ሲሆን ልንዘነጋው የማይገባ ዋና አላማ ነው።ወሰን የለህ ጥላሁን “የፊልም ጥበብ ቅኝት”በሚለው መትሃፉ ሃሳቡን ያጠናክርልናል። “ከፊልም ትንተና አንጻር “ጭብጥ”የተጠቃለለዉን የፊልሙን ማዕከላዊ ጉዳይ ወይም አንድ የሚያደርገዉን የትኩረት ነጥብ ያመለክታል።ፊልሞች ስለ ነገሮች ናችው ይሁነኝ ተብሎ ባይካተትም አንኳን ጭብጥ አለው።ስለምን እንደምሰሩ በሆነ መንገድ ማወቅ ይኖርብናል ።ጭብጡ በተበታተነ ሁኔታ ወይም በፍጻሜው ሊገኝ ቢችልም እንኳን በሆነ ደረጃ ያ ፊልም የተሰራበት ምክንያት ሊኖረው ይገባል።

የአንድን ፊልም ጭብጥ መለየት ቀላል አይደለም።ጭብጥ በጨረር አማካኝነት በቀጥታ ስክሪኑ(ሸራው) ላይ አይንጸባረቅም ፊልሙን በማየት በመጠኑ ዋነኛ ትርጉሙን መረዳት ብንችል እንኳን የፊልሙን ትክክለኛ ጭብጥ ማግኘት ማለት ሌላ ጉዳይ ነዉ።

የፊልም ማሳያ አዳራሹን ጥለን እስክንወጣና እስክንወያይበት ድረስ ይህንን ማድረግ እንደሚያዳግተን ግልጽ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንድን ፊልም ላላየ ለሌላ ሰዉ ለመንገር የጭብጡን ዋነኛ ጭብጥ ፍንጭ ማግኘትን ይጠይቃል። ምክንያቱም ስለፊልሙ ስናወራ የምናዘብለዉ ስሜታችንን ወደ ነካው ነገር በመሆኑ።”(2005፤21)

## 2.1.3.1.8 መቼት

መቼት ማለት አንድን ኪነ ጥበብ ስናዘጋጅ የምንከዉንበት ሰአትና ቦታ ማለት ነው።ፊልም በምናዘጋጅበት ወቅትም ታሪኩን የተከተለ እና የምነከዉንበትን ቦታ እና ጊዜ ግልጽ እና ታማኝ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።ይሄንን ሃሳብ ወሰን የለህ ጥላሁን “የፊልም ጥበብ ቅኝት” በሚለው መጽሃፉ ላይ ስለ መቼት እንዲህ ያስቀምጣል። “መቼት የፊልሙ ታሪክ  የሚከናወንበት ቦታን ጊዜ ማለት ነው ።ለጭብጡም ሆነ ለአጠላይ ፊልሙ ዉጤት መቼት አካል ነው።መቼት እንደሴራ ገጸ ባህሪ ፣ጭብጥ፣ግጭት፣ተምሳሌታዊነት ካሉት የፊልሙ አላባዉያን ጋር ዉስብስብና ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ በመቼት አማካኝነት የሚተላለፈው መልዕክት በአግባቡ በተመልካቹ ሊጤን ይገባዋል።”(2005፤90)

እንዲሁም ዘሪሁን አስፋው “የስነጽሁፍ መሰረታዉያን”በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ይገልጸዋል። “መቼት ታሪኩ የተከናወነበት እና ገጸ ባህርያቱ የሚኖሩበት ወይም የኖሩበት የገጠር ወይም የከተማ አካባቢ ብቻም አይደለም።አያሌ ነገሮችን ይጨምራል።ከገጠሩና ከከተማው ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች አካቶ በመያዙም ጓዘ ብዙ ነው።ለምሳሌ ታሪኩ በአንድ ከተማ  ዉስጥ የሚፈጸም ቢሆን የዚህ ከተማ መልከአምድራዊ አቀማመጥና ተፈጥሯዊ መልክ፣ቤቶችና ህንጻዎች ጎዳናዎች ፣መስሪያ ቤቶች ፣ ትምህርት ቤቶ፣የገበያ ቦታዎች፣ሰዎቹ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ወዘተ የመቼት አካል ናቸው።”

## 2.1.3.1.9 ቃለ ምልልስ

ቃለ ፊልም በፊልሙ ዉስጥ የተካተቱ ገጸ ባህርያት የሚያወሩት ንግግር ነዉ።ፋንታሁን እንግዳ “የተዉኔት አፃፃፍ ዘዴ” በሚለዉ መጽሃፉ እንዲህ ያስቀምጥል። የፊልም ቋንቋ ገጸ ባህርያቱ ከአንደበታቸዉ የሚወጣዉ ቃለ ፊልም ወይም የንግግር ምልልስ ነዉ። ቃለ ፊልሙ ሊደረግ የሚችለዉ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገጸ ባህርያት መካከል ሲሆን በአብዛኛው ግጭቶችን ያመለክታል።ከቋንቋ አንጻር ማንኛዉም ጽሁፍ የሚመዘነዉ በቃለትዉኔቱ ፣ተገቢነት እና ተፈጥሯዊነት እንደሆነ ተደርጎ

ይታመንበታል።ይህም ማለት በመጀመሪያ ቃለ ተዉኔት ለተሳለዉ ገጸ ባህሪ ተገቢ እና ተፈጥሯዊ መሆን አለበት። ይህም ሲባል የገጸ ባህሪው የንግግር ተፈጥሮ ምን እንደሚመስል ፣በምን ምክንያት አሁን ያዳበረዉን ንግግር ሊይዝ እንደቻለ መጠየቃችን አይቀርም።ተገቢ ምልስ የምናገኘዉም ታዲያ የገጸ ባህርያትን የአሣሣል ደረጃዎችን በደንብ በማጤን አካላዊ፣ማህበራዊ፣ስነልቦናዊ፣ሞራላዊ ተፈጥሮ ጠንቅቀን ለማወቅ የቻልን እንደሆነ ብቻ ነዉ። የሳልነዉ ገጸ ባህሪ የሞራል ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ ለምሳሌ የሚናገረዉ ቋንቋ ደርዝ ያለዉ የተመረጠና የመደበኛነት ደረጃ ያልተለየዉ ነዉ። ቃለ ፊልም የግድ ከገጸ ባህሪው ስብዕና ጋር መስማማት አለበት።

## 2.1.3.1.10 አልባሳት

አልባሳት የገጸ ባህሪውን ማንነት፣የኑሮ ደረጃዉን፣ባህሉን እንዲሁም የጊዜ ሁኔታዉን ይገልጻሉ ።ይህ ሲባል ተዋናኝ የሚለብሰው ልብስ ፣ወጣት ይሁን ሽማግሌ፣ሃብታም ይሁን ደሃ ፣ከተማ ይሁን ገጠር ንጉስ ይሁን ሎሌ፣ወታደር ይሁን ገበሬ፣ያልተማረ ይሁን የተማረ የሚገልጽበት የገጸ ባህርይ ማንነት መለያ ነው ።ይህ ብቻ ሳይሆን አልባሳቱ የተፈጸመበት ዘመን እና ቦታን የገጸ ባህሪዉን አካለ መጠን ጋር የሚመጣጠን የፊልሙን ድባብ የአቀራረብ ስልቱ ከመብራት ቀለሞች ጋር የፊልሙን ዘዉግ የማይቀይር መሆን ይጠበቅበታል።ይሄን ሃሳብ ፋንታሁን እንግዳ "ተዉኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው"በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያስቀምጣል።"አልባሳት ተዋንያን ዝግጅታቸዉን ለህዝብ በሚያቀርቡ ጊዜ የሚለብሱት የልብስ መጠሪያ ነዉ። አልባሳት የሚለው ቃል ምንጩ ከቤተክርስቲያን ሲሆን ጳጳሳት፣ ቀሳዉስት እና ዲያቆናት በክብረ በዓላትና እንዲሁም በስረዓተ ቅዳሴ ወደ ቤተ መቅደስ በሚገቡበት ጊዜ የሚለብሱትን ልብስ እና የሚዘረጉትን ጃንጥላ ይጨምራል።አላባሳት፣ጊዜን፣ቦታን፣የኑሮ ደረጃን፣እምነትን፣ ጾታን፣የሙያ መስክን፣ግላዊ ጸባይንና የንቃተ ህሊናን ደረጃ ሳይቀር ሊወክሉ ወይም ሊጠቁሙ ይችላሉ። "(1993፤62)

## 2.1.3.1.11 ገጽ ቅብ

በፊልም ዉስጥ የገፅ-ቅብ የምንለዉ በቆዳ ላይ ወይም በሰዉነት አካል ክፍል ላይ የሚደግ ምክንያታዊ ለዉጥ ሲሆን ፤ የገፅ-ቅብ የአንድን ገፀ-ባህሪ እድሜ፣ የአእምሮ ደረጃ፣ ፆታ፣ ስብእና፣ የፊልሙን መቼት እና ዘዉግ መግለፅ ይችላል።ከዚህም በተጨማሪ ገፀ-ባህሪዉ  የአካል ጉዳት ያለበት ወይም በአደጋ የተፈጠረ አካላዊ ለዉጥ ካለዉ በገፅ-ቅብ ጠሚገለፅ ይሆናል። በሌላ በኩልም ዉበትን ለማጉላት እና ለማደብዘዝ ጥቅም ላይ ይዉላል። ወሰን የለህ ጥላሁን "የፊልም ጥበብ ቅኝት"በሚለው ምጽሀፉ ላይ ስለ ገጽ ቅብ እንዲህ ያስቀምጣል። "ገጽ ቅብ (makeup)የሚፈልገዉን ገጽታ ለመፍጠር ድርሻዉ ቀላል አዪደለም ።ገጽ ቅብ የተዋናዩን ማንነት ፈጽሞ ወደተለየ ሌላ ማንነት የመቀየር አቅም አለው።ለዉጡ በጊዜ ሂደት ዉስጥ

የሚፈጠር ወይም ድንገታዊ ሊሆን ይችላል።ገጽ ቅብ መጠቀም ያለብንም ጸሀፊው ፊልሙን በሚያዘጋጀው መሰረት ሲሆን የምንጠቀመው የገጽ ቅብ የተጋነነ መሆን አይኖርበትም ።”(2005፤104)

## 2.2 የእንስታዊነት ምንነት

እንስታዊነት ማለት ለሴቶች እኩልነት ህጋዊ በሆነ መልኩ ለማስከበር የሚታገል ንቅናቄ ነው ።ይህም ጾታን ብቻ ያተኮሩ ተጽዕኖዎችን በመቃረን እኩልነትን የሚደግፍ እንቅስቃሴ ነው።እንስታዊነት በሴትና በወንድ እኩልነት እኩልነት ላይ ተመስርቶ የሴቶች መብት እንዲከበር እና ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸዉ የሚለዉን መብት ለማስከበር የሚሰራ ንቅናቄ ነዉ።እንዲሁም እየሩሳሌም ሙሉጌታ “ሰዉነቷ ፊልም ከእንስታዊነት ጽንስ ሃሳብ አንጻር” በሚል ለባችለር አፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያ ባዘጋጀችው ጥናታዊ ጹሁፍ ስለ እንስታዊነት እንዲህ ታስቀምጣለች። “አባት ወይም የቤተሰብ ትልቅ የሆነን ወንድ ቤተሰብንም ሆነ ዘር ማንዘሩን ባሰበው መንገድ የሚያስተዳድርበትና የቤተሰቡ ራስ የሚሆንበት የማህበረሰቡ አገዛዝ ስርዓት ነው ይባላል።ዪህ አገዛዝ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ አንስቶ የነበረ ሲሆን ለወንድ ብቻ የቤት ሃላፊ ፤አዛዥ መሪ እንዲሆን አድርጎታል።እናም በማህበረሰቡ ዉስጥ የሴቶች ተሳትፎ በቤት ዉስጥ ለአባወራው ወይም ለቤቱ ባለቤት ወንድ ገረድ መሆን ሲሆን በግርድናዉም ምግብ ማብሰል፣ ልጅ መዉለድ፣ልብስ ማጠብ ወይም ጽዳት ላይ ያተኮሩ ማንኛዉም ስራወችን መስራት ብቻ ነው።ስለዚህ ሴት ልጅ የፈለገችዉን ወዳ ፈቅዳ ማግባት ፤መልበስ፣መዉጣት፣መግባት፣መምረጥም ሆነ መመረጥ ፤መሰብሰብም ሆነ መሰብሰብ ፤ አለመቻሏን ያሳያል ሆኖም ግን ዪህ አስተሳሰብ ዉድቅ እና ፈጽሞ ትክክል ያልሆነ መሆኑን ብዙ ተመራማሪወች ዪገልጻሉ ከዚህም በመነሳት ነወ ሴት ሊጅ በአለም ላይ ተጽዕኖ መፍጠር ትችላለች፣ መምራትም ሆነ ማስተዳደር ፤ማንኛዉንም ስራ ከማህበረሰቡ እኩል መስራት ትችላለች ።”(2013፤10)

### 2.2.1 ሊበራል ፌሚኒዝም

ሊበራል ፌሚኒዝም ሴቶች ከወንዶች እኩልና ተመሳሳይ መብት አላቸው የሚል ንቅናቄ ነዉ።ተክሉ አስኳሉ “የአመጸ መንገድ” በተሰኘው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያብራራል። “በ 1960ዎቹ መጀመሪያ የተወሰኑ ሴቶች “ሊብራል ፌሚንዝም” በሚል ስያሜ የሴቶችን ህጋዊ እኩልነት ለማከስበር እንቅስቃሴ በማድረግ ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩበት ወቅት የእንቅስቃሴው ተሳታፊ የነበሩ ሴቶች ሊበራል ፌሚኒዝም ይጠሩት የነበሩት ኢኪዉቲ ፌሚኒዝም በማለት ነበር ።የሌበራል ፌሚኒዝም አመልካከቶችም ሴቶች በማህበረሰቡ ዘንድ የወንዱን ያህል ነጻነት ሊኖራቸዉ ይገባል።ከማህበራዊ ህግጋት ይልቅ በግላዊ እምነ ልቦና የተመሰረተ ገደብ የለሽ ሰብአዊ ነጻነት መስፈን ይኖርበታል።የሊበራል ፌሚኒስት ጥያቄዎችም ያለ ምንም ተቃዉሞ የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ዉጫዊ የስራ ህይወት እንዲኖራቸው ማድረግ ፤እኩል የመማርና የስራ

ዕድል ማግኘት ናቸው። ስለዚህ ሊበራል እንስታዊነት ሴት በማምኛውም የፖለቲካ፣ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣የስራ ሁኔታ ተሳትፎዎች ላይ መሳተፍ ትችላለች የሚል ንቅናቄን ይዟል።በዚህም ንቅናቄ ሃሳቡን የሚደግፉ ወንዶችም ተሳትፎ ሲያደርጉበት ቆይተዋል።ሆኖም ሊበራል እንስታዊነት ያለምንም ተቃዉሞ የህግ ድጋፍ አገኘ።"(2007፤205)

### 2.2.2 ራዲካል ፌሚኒዝም

ራዲካል ፌሚኒዝም ወንድና ሴት እኩል ናቸው በሁለቱ ጾታ መካከል ያለው ልዩነት የጥምረት ሳይሆን የከረረ ቅራኔ ነው።አባዊ ስረዓት መደቆስ አለበት።የሚል መርሆዎችን ይዞ የሚንቀሳቀስ የፌሚኒዝም ዝትነት ነዉ።ራዲካል ፌሚኒዝም እንቅስቃሴ መሪዎች የአባዊዉን ስርዓት ነቅለን እንጥለዋለን የሚል እሳቤ ይይዛሉ።ይህ የእንስታዊነት ንቅናቄ ወግ፣ባህል፣እምነት፣.....የሚባለው ህግ ሴቶችን ለመጨቆንና ለማሰር የመጣ ነው ይላሉ።(2007፤206)

### 2.2.3 ጀንደር ፌሚኒዝም

ጀንደር ፌሚኒዝም ጾታን መሰረት ያደረገ ሲሆን ማንም ሰው ወንድም ይሁን ሴት ከተወለደ በኋላ ጾታዉን ከተፈጥሮ ስጦታ በዘለለ ራሱን በራሱ የመወሰን መብት እንዳለው የሚያበረታታ ንቅናቄ ንዉ።ይሄን ሃሳብ ተክሉይ አስኳሉ "የአመጻ መንገድ"በሚለው  መጽሃፍ እንዲህ ያብራራል። "ጀንደር ፌሚኒዝም ከ 1990ዎቹ አጋማሽ በስፋት እንዲተዋወቅ ተደረገ፣በምዕራቡ አለም ከ 1970ዎቹ ጀምሮ የጀንደር አጀንዳ በትልቅ የትምህርት ተቋማት በነበሩበት ልሂቃን ዩንቨርሲቲ እና ኮሌጅ ዉስጥ የመወያያ ርዕስ ጉዳይ የነበር ነዉ።እንዲሁም የአንድ ግለሰብ ባዮሎጂካል ጾታ (ሴክስ)በተፈጥሮ የሚያገኘዉ ነዉ።ሴክስ የሚለው ቃል የአንድ ሰው ባዮሎጂካዊ ወንድ አሊያም ሴት መሆንን የሚያመላክት ነው።(ስፐርም እና ኦቫል)ጀንደር የሚለው ቃል በተቃራኒዉ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ማህበረሰባዊ አልያም ልማዳዊ ፣ህይወታዊ ሁናቴ (ኮንቴክስት)የሚዎክል በመሆኑ አንድ ሰው ከአደገ በኋላ እንደፈቃዱ/ዷ ወንድ አልያም ሴት ወይም ተሰይሞ ያልታዎቀ መሆን ይችላል።የሚል ፍች ይዟል። ስለሆነም ይህ የእንስታዊነት ንቅናቄ ማንም ሰው ከዉልደቱ በኋላ ጾታዉን የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው የሚል ንቅናቄ ነዉ።"(፣2007፤207)

## 2.3 የእንስታዊነት እሳቤ ባህርያት

"ይህ እሳቤ በማህበራዊ ፣ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ እና ሌሎች ለሰው ልጅ አስፈለጊ የሆኑ ግልጋሎቶችን ለወንዱም ሆነ ለሴቷ በእኩልነት መጠቃቀምን የሚደግፍ ነው።እንዲሁም በጾታ (በሴትነታቸው)በቋንቋ፣

በሃይማኖት ዝንባሊያቸዉ፣በፖለቲካ ወይም በማህበራዊ ተሳትፎዎች በሴትነታቸው ምክንያት እንዳይነፈጉ ማድረግ  እና ሴት ልጅ ከወንድ እኩል አቅም እና ችሎታ እንዳለቸው ማደርግ ነው።

## 2.4 የገጸባህርያት ምንነት

ገጸ ባህርያት አንድ ደራሲ ገጣሚ፣ሰአሊ፣ጸሃፊ፣ሃሰቡን ለመግለጽ ታሪኩን ለማስጀመርም ለማስጨረስም የሚፈጥራቸው አካላት ናቸው።ይህን ሃሳብ ወስን የለህ ጥላሁን "የፊልም ጥበብ ቅኝት" በተሰኘው መጽሃፉ ላይ እንዲህ አስቀምጧል። "ተመልካቾችን ልናሳትፍ የምንችለው ሰዉ ይዘን ነዉ።ተመልካቾችህን በጸሃይ ጥልቀት ምስሎች ፣በአስገራሚ ማባበያዎች ፣በካሜራህ አይነት ፣አቅርቦትና አርቀ በመቅረጽ ወይም በሌላ የሲኒማ ጥበብ ጥሩ ተመልካች ልታደርጋቸው አትችልም።ይህ ለነሱ ስሜት አይሰጣቸዉም ።ነገር ግን የሆነ ሊያሳስባቸዉ የሚችል ነገር ልትሰጣቸዉ ይገባል።የሚያስቡለት ሰዉ ፣የሚጨነቁለት ሰው፣ያን ጊዜ ትማርካቸዋለህ።"(2005፤52)

## 2.5 የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃ

የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃዎች በአራት የተከፈሉ እና የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቅሴ ያማከሉ ተደርገው የተዋቀሩ ናቸዉ ይሄንን ሃሳብም ፋንታሁን እንግዳ "የተዉኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ" በሚለው መጽሃፉ እንዲህ ያብራራል። "አንድ ድርሰት ድርሰቱ በተደራሲያን ተቀባይነት ለማግኘት ያስችለዉ ዘንድ ለሚጽፈው ጹሁፍ ለሚገጥመው ግጥም የሚፈጥራቸዉ  ገጸ ባህርያት የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃን ማሟላት ይጠበቅበታል። ገጸ ባህሪ የሚለዉ ቃል በፈጠራ ታሪክ ዉስጥ ያሉትን የድርሰቱን ሰዎች (አበበ፣ ከበደ፣አልማዝ)በድርሰቱ ዉስጥ የተሳሉትን እንስሳት(አህያ፣ጅብ ፣በግ ፣ዶሮ፣በግ፣ቀበሮ፣)በታሪኩ ዉስጥ የሚቀረጹትን ሰማያዊ ወይም ሃተታ ተፈጥሯዊ ፍጥረታትና መናፍስት (ሰይጣናት፣መላዕክት፣ሰናይ መናፍስት፣እኩይ መናፍስት፣ጣእረ መንፈስ )እና ረቂቅ ሃሳቦችን (ተንኮል፣ደኘት ፣መልካም ስራ ፣ ቁንጅና)የመሳሰሉትን ይወክላል።በሌላ በኩል ደግሞ በፈጠራ ሥራ ዉስጥ የሚገኙትን የድርሰቱን ሰዎች የሞራል ፣የስነምግባር ፣የስነልቦና እና በአጠቃላይ የዉስጣዊ ጸባይና የውጫዊ አመልን ድምር መልክ የሚወክል ትርጓሜንም ይሸከማል።ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለጽ ገጸ ባህሪ የሚለው ቃል የድርሰቱን ባለታሪክ አካላዊ ገጽታ ፣ዉስጣዊ ጸባይና አስተሳሰብ በአንድነት የሚሸከም ነዉ።የሚፈጥራቸዉ ገጸ ባህርያትም በአራት ገጸ ባህርያት  ደረጃ ሊቀርጻቸው ይገባል። እነዚህም ስነ ልቦናዊ ፣ሞራላዊ።አካላዊ፣እና ማህበራዊ የገጸ ባህያት አሳሳል ናቸዉ።"(2009፤26 )

## 2.5.1 አካላዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃ

አካላዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል ደረጃ እንዲሁ በእይታ ብቻ ልንገልጻቸው የምንችል እና የምንስላቸው የአሳሳል አይነት ነዉ።ፋንታሁን እንግዳ "የተዉኔት ድርሰት አጻጻፍ"በሚለው መጽሃፉ በዚህ ሃሳብ ላይ እንዲህ ያብራራል። "ከምንም በፊት ምንነታቸው ለአንባቢም ሆነ ለተመልካች ይፋ የሚሆነው በመጀመሪያዉ የገጸ ባህሪያት አሳሳል ደረጃ ማለት በነፍስ ወከፍ አካላዊ አቋማቸው ገለጻ አማካኝነት ነዉ። እንቅስቃሴ፣ጤና፣ድምጽ፣መልክ ፣ጥቁረት፣ንጣት፣ጠይምነት፣አቋምን ማለትም ዉፍረት ፣ቅጥለት ርዝመት፣ አጥረት ፣ምን እንደሆነ ያስረዳል።ይህ የአሳሳል ደረጃ አይነት ከስሙ እርንደምንነሳው የእያንዳንዱ የገጸ ባህሪያት የዉጫዊ ክፍል ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህን የአሳሳል አይነት አይተን ልንናገር የምንችለው ክፍል ነው።የገጸ ባህርያት አካላዊ ቀረጻ ብዙ ጥበብን የሚጠይቅ አይደለም ልክ በመንገድ ከሚተላለፉት ሰዎች የአንዱን አቋም ተመልክተን ከምንናገረው የተለየ አይደለም።በዚህም ምክንያት ታዲያ የገጸ ባህርያት የመጀመሪያ ደረጃ አሳሳል ማለትም የአካላዊ አቋማቸው ቀረጻ በጣም ቀላሉ የገጸ ባህርያት አሣሣል ዓይነት ተደርጎ ይወሰዳል።"(2009፤27)

## 2.4.2 ማህበራዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል

ይህ የአሳሳል አይነት ገጸ-ባህሪያትን ስንገልጽ ገጸ ባህርያቶች ከማህበረሰብ ጋር ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት፣የኑሮው ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው።ይህ የአሳሳል አይነት በአይናችን አይተን መናገርና በቀላሉ መረዳት እንድንችል ያደርገናል።ይሄን ሃሳብ ፋንታሁን እንግዳ "የተዉኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ"በሚለው መጽሃፉ ላይ እንዲህ ያብራራል። "ከአካላዊ አቋም ገለጻ በማስከተል የሚመጣዉ የገጸ ባህርያት የአሣሣል ደረጃ የሰፋና የጠለቀ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚመለከት ነዉ።ይህን የተወሳሰበ ማህበራዊ ግንኙነት ለማወቅ በመንገድ ስንሄድ ተመልክተን በእርዝመታቸው እና በጥረታቸው ወይም በሽምግልናቸው እና በወጣትነታቸው እንደምንፈርጃቸው ሰዎች(ገጸ ባህርያት )ልንገነዘባቸው መሞከሩ ከቶ የማይቻል ነው። ስለሆነም የእያንዳንዱ ገጸ ባህሪ ማህበራዊ  ግንኙነት ለማዎቅ የግድ ወደ ተዉኔቱ ታሪክ ጠልቆ መግባት ያስፈልጋል።የትምህርቱን ደረጃ በተመለከተ ለምሳሌ የቀርጸው ገጸ ባህሪ የተማረ ወይስ ያልተማረ፣የተማረ ከሆነ ዘመናዊ ወይስ ባህላዊ ትምህርት ነው የቀሰመው በየት አገርና ከተማስ ተማረ በትምህርቱስ ሰነፍ ነበር ጎበዝ ፣ልጤ ዎይስ ያገባ ፣የፖለቲካ አቋም፣የትኛው ሃይማኖት ተከታይ ፣ሃብታምነትና እና ደሃነት ፣ የተማሩበት የሙያ መስክ የመሳሰሉትና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን (ሁኔታዎችን )የምገልጽበት የገጸ ባህርያት አሣሣል አይነት ነው።"(  2009፤28)

## 2.4.3 ስነ ልቦናዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል

ስነልቦናዊ አሳሳል አይተን የምንገምተው (የምናዉቀው)ሳይሆን ዉስጣዊ ፍላጎትንና ግብ ላይ ትኩረት ያደረገ ነዉ።ይሄን ሃሳብ ወሰን የለህ ጥላሁን "የፊልም ጥበብ ቅኝት በሚለው መጽሃፉ እንዲህ ያስረዳል። "ንቁና ጥንቁቅ በሆኑ ተመልካቾች እንኳን ሊታይና ሊደመጥ የማይችል የዉስጣዊው ዓለም ድርጊት አለ። ገጸ ባህሪዉን በዕዉነት ለመረዳት ይች አለም አቅፋ የያዘችው የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ሚስጥር አብዛኛዉን ጊዜ አስፈላጊ ነው።ዉስጣዊ ድርጊት በገጸ ባህርያቱ አዕምሮና ስሜት ዉስጥ ያለን ሚስጥር፣ያልተነገሩ ሃሳቦችን፣የቀን ህልሞችን፣ትዉስታዎችን፣ፍራሃትን፣ምኞቶችን፣ ቅዠትን አጠቃሎ የያዘ ነዉ።የሰዎችን ባህሪ ለመጨበጥ ፣ተስፋቸዉን፣ህልማቸዉን፣ምኞታቸዉን፣መረዳት አስፈላጊ ነው።በተጨማሪም ፍርሃታቸው ያለመረጋጋታቸው ከማንኛዉም ዕዉናዊ መቅሰፍት የከፋ ይሆንባቸዋል።"(2005፤55)

## 2.4.4ሞራላዊ የገጸ ባህሪያት አሳሳል

ግብረ ገባዊ የአሳሳል ደረጃ የአንድን የገጸ ባህሪ የዉስጣዊ አመለካከት ማለትም መልካምነቱን ወይ መጥፎነቱን ፣ጽድቁን ወይም ኩነኔዉን፣ቸርነትና ንፉግነቱን ጉረኝነቱን እና ትሁትነቱን ድል የማድረግ እና መሸነፍ የመሳሳሰሉት ሞራላዊ የሆኑ ነገሮችን የምንገልጽበት ነዉ።ፋንታሁን እንግዳ "የተዉኔት አጻጻፍ ዘዴ" በሚለው መጽሃፉ ላይ በሃሳቡ ላይ እንዲህ ያስቀምጣል። "ሞራላዊ የገጸ ባህርያት አሳሳል የሚያወሳው እንደ ስነ ልቦና የገጸ ባህርያት አሣሣል ሁሉ በረቂቅ ሃሳቦች ማለትም ህሊናዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።ልዩነቱ ይሄኛው በሰው ልጅ ፍጥረት የመከበርና የመዋረድ የሞራል ጥያቄ ላይ መሰረት በማድረግ የሚቀርብ መሆኑ ነው።ተፈጥሮ ከሚፈቀደው በታች ወርዶ ቅጥ ያጣ ስግብግብ ሆኖ ሲቀርብ ፣ ወይም ከሚገባው በላይ ክብር ፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፣ወይም ከሁለቱ በተቃራኒ አለማዊ መንፈሳዊ መመሪያዎችንና ህጎችን ተቀብሎ የሞራል አስተማሪና ሰባኪ መሆን በሚያሳዩና በመሳሰሉት ፍሬ ሃሳቦች ላይ በማተኮር ገጸ ባህርያትን ከዚህ አንጻር በመቅረጽ ላይ ያነጣጥራል። የሞራልን ጉዳይ እንደ አቢይ ጉዳይ በመዉሰድ ገጸ ባህርያቱን የሞራል ባለቤት ወይም የሞራል ደሃ አድስርጎ በመቅረጽ በተለይ በታምራዊ እና ግብረገባዊ የሃይማኖት ተዉኔቶች የተለመደ ያጻጻፍ ስልት ነው።"( 2009፤28-29)

## 2.5 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

አጥኚዉ ይህን ጥናታዊ ጹሁፍ ሲጽፍ ለመስራት ሲነሳ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያልቸዉን ስራዎች ቅኝት በቀትታም ሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመቃኘት ሞክሯል።

በ 2010 ዓ.ም ወለላ አበጀ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሚያ ያቀረበችው "የነገን አልወልድም "የአማርኛ ከፊልም ከዝግጅት ትንተና አንጻር በሚል

የቀረበዉን ጥናታዊ ጽሁፍ ቃኝቷል ።ይህ ጥናታዊ ጹሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር አንድ የሚያደርገው በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣የጥናቱ፣አላማ የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ ንዑስ አላማ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች እና የጥናቱ አወቃቀር ጋር ሲዛመድ እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት የንድፈ ሃሳብ እና የተዛማጅ ጹሁፍ ቅኝት ማለትም ስለ ፊልም ዝግጅት ምንነት፣የፊልም ዝግጅት አላባዉያን ማለትም የካሜራ ቀረጻ፣ግብዓተ መብራት፣ግብዓተ ድምጽ፣አልባሳት፣ገጽ ቅብ፣ፊልም፣ቅንብር፣ትወና፣ሙዚቃ ግብዓት፣ጭብጥ፣መቼት ጽንሰ ሃሳቦች ጋር የተዛመደ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት ስለፊልም ዝግጅት የመረጃ ትንተና ማለትም በምዕራፍ ሁለት ላይ በገቡት ሃሳቦች መሰረት ትንተና ማካሄዱ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በቀጥታ ለመገናኘት ችሏል።በምዕራፍ አራትም የማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች  ሲያመሳስላቸው ይህ ጥናት ለየት የሚያደርገው ስለ እንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ ጭምር ለመስራት በመነሳሳቱ ነው።

በ 2013 ዓ.ም እየሩሳለም ሙሉጌታ በወልቂጤ ዩንቨርሲቲ ለትያትር ጥበባት ትበባት ትምርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያነት ካቀረበችዉ ሰዉነቷ የተሰኘዉን የአማርኛ ፊልም ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ እሳቤ አንጻር በሚል የቀረበዉን ጥናታዊ ጽሁፍ ቃኝቷል።ይህ ጥናታዊ ጹሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በምዕራፍ አንድ የእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ያደረገ ማለትም መግቢያ፣የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ አላማ፣ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች እና የጥናቱ አወቃቀር እና በምዕራፍ ሁለት ስለ እንስታዊነት ንድፈ ሃሳብ እና የተዛማጅ ጹሑፍ ቅኝት ማለትም ስለ እንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ፣ራዲካል እንስታዊነት፣ጀንደር እንስታዊነት፣ሊበራል እንስታዊነት፣ስለ ገጸ ባህርያት አሳሳል የሰፈሩት ሃሳቦች ዝምድና ሲኖራቸው

በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና የሰፈረበት እና በምዕራፍ ሁለት በተቀመጠው እሳቤ መሰረት መተንተኗ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ሲያመሳስላቸው ከዚህ ጥናት ጋር ለየት የሚያደርገው  የዚህ አጥኚ የራዲካል እንስታዊነት እሳቤ መሰረት በማድረግ ተጨማሪ ትንተና መስጠቱ ነዉ። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች የሚሉትን አካቷል ።ከዚህ ጥናት ጋር ለየት የሚያደርገው ስለ ፊልም ዝግጅት አላባዉያን አንጻር ትንተና መስጠቱ ነዉ።

# ምዕራፍ ሶስት

# መረጃ ትንተና

## 3.1 የእንሳሮ ፊልም አጽመ ታሪክ

ፊልሙ የሚጀምረው ሁለት ህጻናት በማሳ ላይ እየተጫወቱ ሲሆን ከርቀት የጥይት ተኩስ ሰምተው ምንነቱን ለማረጋገጥ ከማሳዉ ወጥተው ሲሮጡ አንደኛዉን ልጅ እናቱ ከጓደኛው ነጥላ ስትወስደው አንደኛው ልጅ ደግሞ ወደተተኮሰበት ቦታ ሲሄድ አባቱ ተገድሎ አጎቱ ደግሞ አግሩ በጥይት ተመቶ ቆስሎ ያገኘዋል።ይህ ከተፈጠረ ከሃያ አመት በኋላ ልዑልና ሃሴት የሚባሉ የሚዲያ ባለሙያዎች ወደ ገጠር ማለትም ልዩ ስሙ እንሳሮ ወደሚባል ቦታ ለመስክ ስራ ሄደው ቀረጻቸዉን ከአንድ ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን ላይ የመጀመሪያ ቀረጻቸዉን ካደረጉ በኋላ አካባቢው ካለ ጠላ ቤት ገብተው እየተጨዋወቱ እያለ ድንገት ልዑል የእንሳሮ ልጅ እንደሆነ በተዳጋጋሚ እየፎከረ ሲያዎራ ጠላ ቤቱ ያሉት ሰዎች ስለማንነቱ ይጠይቁታል።

ማነንቱን ሲነግራቸዉም እንሱም የጎበዝ ጀግና ልጅ እንደሆነና እንሳሮ ላይ አባቱ እንደታሰረ ሲነግሩት ልዑል በመደናገጥ እና ምን አድርጎ እንደታሰረ ሽማግሌውም ዝም ሲሉት ሁሉም ወጥተው ይሄዳሉ ።በዚህ ጊዜም ቁጭ ብሎ ሲሰማ የነበረው የአቻም መልዕክተኛም ያየዉን ሁሉ ለአቻም እና ከንዴ ሲነግራቸው

አቻም በደም ፍላት ልዑልን (የአባቱን ገዳይ ልጅ )ለመግደል ዉጣ ዉረድ ይጀምራል።ከዚያም የልዑል ቤተሰቦችም ልዑልን የደም ማድረቂያ ሊያደርጉትና ሊገድሉት እንደሆነ መልዕክት ሰምተው ማሬ ልዑልን ለማዳን ጠመንጃዉን ይዛ እነልዑልን ለማዳን ታጥቃ ትነሳለች።

በዚህ መሃልም አቻም ያባቱ ገዳይ ልጅ አለበት የተባለው ቦታ ሄዶ ከመኪናቸው ላይ ቆመው እነልዑል ሲከራከሩ ከርቀት በመተኮስ ሲያስደነግጣቸው በመበርገግ እነ ልዑል ወደጫካ ሲገቡ ሾፌሩ ወደህግ አካል የተፈጠረዉን ለመናገር እየነዳ ይሄዳል።አቻምም እነ ልዑል ከገቡበት ጫካ ተከታትሎ ሊገድላቸው በተዳጋጋሚ ተኩሶ ይስታቸዋል ።ማሬም ከወንድሟ ጋር በመሆን ትፈልጋቸዋለች።እንዲህ እያለ እነ ልዑል በጫካው ላይ እንዳሉ ይመሽባቸዉና የጅብ ጩሀት ሲሰሙ ሃሴትና ልዑል በፍራት ላይ እያሉ ማሬ ደርሳላቸው ወደ ቤት ወስደዋቸው ካደሩ በኋላ አቻም በጠዋት መጥቶ ሊገድል ቢፈልግ ማሬ በጎን እየተኮሰች አልቻለው ስትል ከ ልዑል ጋር የመጣችዋን ሃሴትን ተሸክሞ በመዉሰድ ያግታታል። ከዚያም ሀሴትን መያዣ አድርገው ልዑልን እንዲሰጡን እና ደማችን እንወጣ በማለት አቻም ሽምግልና ቢልክም ማሬ እና ቤተሰቦቿ አሻፈረኝ በማለት መልዕክተኞችን ያስሯቸዋል ።

በኋላም አቻም እና ልዑል ፍልሚያ እንዲገጥሙ ተስማምተው ማሬ ልዑልን ራቅ ወዳለ ቦታ በመዉሰድ መሳሪያ ታለማምደዋለች።በኋላም የፍልሚያ ጊዜያቸው ደርሶ ለፍልሚያቸው የሚገባላቸው ደግሞ የልዑል አባት ይሁኔን ቢያስቡም የልዑል አባት ከእስር ገና ከመፈታቱ እንዲሁም ደግሞ ንስሃ ስለገባሁ ምንም አይነት ፍልሚያ አላደርግም ይላቸዋል።እነሱም ልዑል ፍልሚያ ስለማይችል እሱን መጀመሪያ እናስገባና ሀሴትን ከለቀቃት እኛ ተረባርበን እናስጥለዋለን በማለት ይመካከራሉ።

ከዚያም ማሬ ልዑልን መሳሪያ አስይዛ ስትልከው የታሰረችዉ ሃሴት ትለቀቃለች።ልዑልና አችምም ተኩሳቸዉን እየቀጠሉ እያለ ፖሊሶች ይመጡና መጀመሪያ ከንዴን ይይዛሉ።ቀጥሎም መሚደንቅ ፍጥነት ማሬ ልዑል አድርጎት የነበረዉን ሙሉ ልብስ ተደብቃ በመልበስ ወንድ መስላ ትመጣና አቻምን ልትታኮሰው ስትል ልዑልን ከአቻም ጀርባ የሷን ሙሉ ልብስ ለብሶ ከሩቅ እየተመልከተችው ባለበት ወቅት ተዘናግታ እያለ አቻም ተኩሶ ይገላታል።ተጠግቶ ሲያያትም ሴት እንደገደል ሲያይ ይናደዳል።

ከዝያም ሃሴትና ሉዑል ፊትና ኋላ መጥተው ልዑልን ሊገለው ከሀሴት ጋር ሲከራከር ከሩቅ ተው ልጀ እያለ ትልቅ ሰው(የልዑል አባት) ይመጣና እኔ ነኝ ያባትህ ገዳይ ይለዋል።አቻም ያባቴ ገዳይ አንተ ከሆንክማ እገልሃለው ብሎ መሳሪያዉን ሲደቅንበት የልዑል አባትም ለአቻም በግንባሩ ተደፍቶ አባትህ ጥፋተኛ አልነበርም አጎትህ ከንዴ ነው ሚስቴን በሌልሁበት የደፈራት የሱ እጣ ፋንታ ነው ላባትህ የሆነው አባትህ ንጹህ ሰው ነበር።እባክህ ይቅር በለኝ ሲለው በመራራት የደቀነዉን ጥይት ወደላይ ይተኩስና መሳሪያዉን ሲጥል የህግ አካላት መጥተው ይይዙታል።ማሬንም ይቀብሯታል።በመጨረሻም ሁሉም

ተሸማግለው ከደም ነጻ ተባብለው ይታረቁና ከማሬ ቤተሰቦች ቤት ድል ያለ ድግስ ደግሰው ይቅር ተባብለው ፊልሙ ይፈጸማል።

## 3.2 የእንሳሮ ፊልም ከምስል ቀረጻ አንጻር

### 3.2.1 እጅግ በጣም የሩቅ ምስል ቀረጻ(Extreme long shot)

ይህ የቀርጻ አይነት የሚቀርጸዉን አካል ከአለው አካባቢ አንጻር ወይም ከመልከዓምድረ ጋር በስፋት በማጣመር የሚቀረጽበት የቀረጻ አይነት እና ትዕይንቱ የሚፈጸሙበት ቦታ ጥቆማ ለመስጠት የሚያገለግል ሲሆን በዚህ ፊልም 00፡02፡47 ላይ ሁለቱ ህጻናት ጨዋታ ላይ በነበሩበት ሰአት ተኩስ ይሰማሉ።በተኩሱ ተደናግጠው ሲሮጡም የሚሮጡበትን ቦታ(መቼቱን) ለመግለጽ በማሳው እና እንዲሁም አጠቃላይ የዚህ ትዕይንት ቦታ ገጠር መሆኑን እና የዚህን ፊልም መቼት በቀላሉ እንድንገምተው፣ልጆቹ የነበሩበትን ዳራ በሰፊዉ በማስዳሰስ በዚህ እጅግ በጣም የሩቅ ቀርጻ በሚባለው የቀረጻ አይነት ማሳየት መቻሉን ያሳየናል።



ምስል 1 እጅግ በጣም የርቀት ምስል ቀረጻ

በተጨማሪም ይህ የቀረጻ አይነት በ 00፡07፡15 ደቂቃ ላይ ልዑልና ሃሴት ለመስክ ስራ ወደ እንሳሮ በመኪና እየሄዱ ያለዉን ትዕይንት ያሳየል።በመሆኑም ለመስክ የወጡበት ቦታ ገጠር መሆኑን እንደማመላከት እና የአካባቢዉን ዳራ በስፋት ያሳያል። እንዲሁም በዚህ የቀረጻ አይነት የተካተቱ እና ለፊልሙ ተገቢ የሆነ መልዕክት በማስተላለፍ ተመልካች ያለምንም መደናገር እንዲመለከት፣ ፊልሙ እንዲያስተላልፍ የተፈለገዉን መልዕክት የሚያንጸባርቁና ከመቼቱ ጋር እየተዋሃዱ ምስል እንዲከስቱ የተደረጉበት ሁኔታ ታይቷል።በመሆኑም አጥኝዉ ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ ይሆነው ዘንድ ከዚህ በታች የተጠቅሱትን ማመሳከሪያዎች እንዲመለከት ያሳስባል።

00፡07፡42-00፡08፡20 ባለው ቀረጻ ላይ ሃሴት እና ልዑል ወደ መስክ ረጅም ርቀት እየተጉዙ መሆኑን እና የሚጓዙበት አካባቢም ገደላገደል መሆኑን በሰፊ ዳራ አስመልክቷል።እንዲሁም የሚጓዙበትን ቦታ በስፋት በማስቃኘት እንሳሮ የተባለዉን አካባቢ ያለዉን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ በማስዳሰስ ጉልህ ሚና

የተጫወተ የምስል ቀረጻ አይነት ነዉ። እንዲሁም 00፡14፡03-00፡14፡17፣ 00፡39፡46፣00፡42፡32፣00፡46፡57፣00፡42፡32 ደቂቃዎች ላይ ባሉት ትዕይንት ላይ በዚህ የቀረጻ አይነት በመጠቀም የቦታዉን ወይም የፊልሙን አጠቃላይ መቸት እንድንዳስሰው እና የመልከዓምድሩን ዉበት እያስቃኘ፣ ወጣ ገባ እንደሆነ እና ተፈጥሯዊ ዳራዉን በማሣየቱ ጉልህ ሚና ተጫዉቷል። ይህ ማለት እጅግ በጣም የርቀት ምስል ቀረጻ ዋና አገልግሎቱ ታሪኩ የሚከወንበትን ቦታ በስፋት ለማሳየት እና መቼቱን ግልጽ ለማድረግ ሚና ያለዉ በመሆኑ በዚህ ትዕይንት ላይም የተጠቀሙት የቀረጻ አይነት ረጅም ርቀት የሚጓዙ መሆኑን እና መልከዓምድሩን አስተዋዉቆናል።



**00፡07፡15**

ምስል 2፡ እጅግ በጣም የርቀት ምስል ቀረጻ

### 3.2.2 እጅግ በጣም የቅርበት ምስል ቀርጻ(extreme clouse up)

እጅግ በጣም የቅርበት ምስል ቀረጻ የሚቀረጸው የሰዉ ወይም የቁስ ምስል የተወሰነ አካል ክፍል ወም ቁስ ክፍል ብቻ በምሰል ማዕቀፍ ዉስጥ በማካተት ብቻ የሚፈለገው የአካል ክፍል ለምሳሌ የጣት ፣የዕግር፣ አፍንጫ፣ከፊል የፊት ገጽታ፣አይን፣እና የጆሮ እንቅስቃሴዎችን ብቻ በካሜራ ማዕቀፍ ዉስጥ በማስገባት የምንቀርጽበት የቀረጻ አይነት ነው ።በዚህ ፊልምም በ 00፡12፡22 ደቂቃ ላይ አቻም ከሰፈሩ መጠጥ ቤት ተቀምጦ በሚጠጣበት ጊዜ ሌሎች የመጠጥ ቤት ደንበኞች ገብተው ለመቀመጥ ሲፈልጉ የመጠጥ ቤቱዋ ሰራተኛ ቦታው ላይ መቀመጥ እንደማይችሉና ቦታው ለሌላ ሰዉ እንደሆነ ትነግራቸዋለች።ከዚያም ልጆቹ አሻፈረኝ ከዚህ ቦታ አትቀመጡም የሚለን ማን ወንድ ነው በማለት ሴትዮዋን ሲገላምጧትና የጥቃት ንግግር ሲናገሩዋት አንገቱን አቀርቅሮ ይመለከታቸዋል።በዚህ ጊዜ አቻም ተቀምጦ ሴትዮዋን ሲያንገራግሯት በጣም በንዴት እይታ ይመለከታቸዋል።ስለሆነም የአቻምን ንዴት ለመግለጽ የተጠቀመዉም ሁለት አይኖቹን ብቻ በጣም ፈጠዉ በካሜራ ማዕቀፍ ዉስጥ ያሳየናል።ስለሆነም በዚህ የቀረጻ አይነት አዘጋጁ የአቻምን ንዴት እና እንዲሁም ወንድነቱን ሊደፋፈሩት መሆኑን ሲረዳ ሊሰማዉ

የሚችለዉን ስሜት በአይኖቹ መፍጠጥ  በተገቢዉ ሁኔታ በመጠቀሙ አቻም በተፈጥሮዉ ደመ ሙቅ ወይም ንዴታም እንደሆነ ከአሁኑ ሊያስተዋዉቀን ችሏል።በተጨማሪም በዚህ ፊልም ዉስጥ በዚህ የቀረጻ አይነት የተካተቱ ብዙ የቅርበት ምስል ቀረጻዎች አሉ።00፡01፡07 የአቻምን የቁጣ እና በራስ የመተማመን፣ ቁርጠኛ የመሆንን ስሜት የተላበሰ ገጸ ባህርይ መሆኑን አሳይቶናል።



00፡12፡22

ምስል3 እጅግ በጣም የቅርበት ምስል ቀርጻ

## 3.2.3 የቅርብ ዕይታ ቀረጻ (clouse up)

የቅርብ እይታ ቀረጻ ከአንገት በላይ ያሉትን ዕይታዎች በመምረጥ እንደየአስፈላጊነቱ የተዋናዩን አትኩሮታዊ እንቅስቃሴ ለማሳየት ጥቅም ላይ ይዉላል።እንዲሁም የተዋናዩን ሙሉ የፊት እንቅስቃሴ እና ስሜት ለማስረዳት ያስችለናል።ስለሆነም በዚህ ፊልም ዉስጥ **00፡21፡38** ደቂቃ ላይ ማሬ እንጨቷን በጀርባዋ አዝላ ደግሞ በመዳበሪያ ያለዉን እቃዋን  አቻም ሊያሸክማት ሲሞክር እርዳታዉን እንደማትፈልግ ከንግግሯ በተጨማሪ በሙሉ የፊቷ እንቅስቃሴ ስትገላምጠው ያለዉን ስሜት በዚህ የቀረጻ አይነት ለመግለጽ ችለዋል።ይህ ስሜትም በዚህ የቀረጻ አይነት መገለጹ የማሬን አልደፈርም እና ማንም ሴት ናት ብሎ አይተናኮለኝም የሚለዉን ስሜቷን ለማመልከት እና ጀብደኝነቷን በማሳየት አስተዋጽኦ አድርጓል። ስለሆነም በዚህ ፊልም ዉስጥ በዚህ የቀረጻ አይነት የተካተቱ ትዕይንቶች ብዙዎች እንደመሆናቸው መጠን አጥኝዉ ጎለተው የታዩትን ያብራራል።**01፡36፡42** ደቂቃ ላይም ማሬ ከአቻም ጋር ስለፍልሚያው ስታወራ ይሄን የቀርጻ አይነት ተጠቅመዋል ይሄም የማሬን ወኔ እና ጥንካሬ አቅርቦ በማሳየት በፍልሚያው ምንም ጭንቅ እንዳልገባት እና ሴት ናት በሚል በሚመጣዉን ንቀት ችላ እንዳለችዉ አይኗን እና ጥርሷን በዕልህ ስታኮሳትረው በዚህ ቀረጻ በማገዝ በማሳየት አገልግሏል። እንዲሁም 00:43:10 በጫካው ዉስጥ ሆነው እያለ መሽቶ ጅብ ሲጮህባቸው የልዑልና ሃሴትን ፍራቻ መንቀጥቀጣቸዉን መደናበራቸዉን ከአንገት

በላይ በመቅረጽ ለማሳየት እና ተመልካችን አብሮቸዉ በስሜት እንዲገባ የሚያስችል የቀረጻ አይነት በመካተቱ ከስሜቱ ጋር ማጋባት ችሏል።





**00፡21፡38** **01፡36፡42**

ምስል 4 የቅርብ ዕይታ ቀረጻ

በተጨማሪም ከታች ከምንመለከተው **00፡50፡59** ደቂቃ ላይ የምንመለከተው ምስል በዚህ ሁለት የቀረጻ አይነቶችን ይዞ የተቀረጸ ነው።ይሄዉም የዝቅተኛ ማዕዘን ቀረጻ እና የቅርበት ምስል ቀረጻን አካቶ በመያት የተወሰደ በመሆኑ አቻም በከፍተኛ ወኔ ዉስጥ እንደሆነ የዝቅተኛን ማዕዘን ሲጠቀሙ ያን ዉስጡ ያለዉን ስሜት ለማስረዳት ደግሞ በቅርበት ምስል በማስደገፍ ሁነኛ ማብራሪያ በመስጠት ድጋፍ ሰጥቷል።



**00፡50፡59**

ምስል 5 የቅርብ እይታ ቀረጻ

## 3.2.4 የሩቅ ቀረጻ(Long shot)

የሩቅ እይታ ቀረጻ አንድን ምስል በርቀት መቅረጽ ሲሆን ሰፊ ዳራ ዙሪያዉን አስፈላጊ የሆነ ስፍራ ለማየት ይጠቅማል።ከዚህም በተጨማሪ ምስሉ ሙሉ ሲሆን ያለዉን ቀረጻ ለማወቅ እንድንችል ያደረጋል።በዚህም መሰረት 00፡37፡47 ደቂቃ ላይ የእነ ልዑል ሹፌር አቻም ተኩሶ ካስደነገጣቸው በኋላ እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ወደ ህግ አካላት በመሄድ የሰው ሃይል ከፖሊስ ጣቢያ ይዞ ሲወጣ ይታያል ።ይህ ቀረጻ

ሹፌሩ ፖሊስ ጣቢያ ይሂድ ሌላ ቦታ በቃለፊልም አልተገለጸም። ነገር ግን በዚህ ትዕይንት መልዕክት ለማስተላለፍ ሲፈልግ ከሩቅ የተቀመጠች ላንድ ክሩዘር መኪና እና ግቢው ላይ የቆመው ስለ ስብዕና የሚያወሩ ማለትም እነህ በተለምዱ መስሪያ ቤት ላይ የሚለጠፉት ተጠያቂነት፣ታማኝነት፣ ግልጸኝነት....የመሳሰሉት ፖሊስ ጣቢያ ላይም ግሊጋሎት ላይ ስለሚዉል በዚህም ሳቢያ ቦታዉን ለመጠቆም ችሏል። ይህ ቀርጻ አይነትም ሹፌሩ እነ ልዑልን የህግ አካላት እንዲታደጓቸዉ ወደ ፖሊስ ጣቢያ መሄዱን እና ስፍራዉን በዚህ በዕሩቅ እይታ ቀርጻ ለመግለጽ ተችሏል።በዚህ መሰረት በዚህ በሩቅ የቀረጻ አይነት የተሰሩትን ይዳስሳል።እንዲሁም 00፡47፡07፣00፡48፡39፣ 01፡10፡02፣ እና 01፡21፡14 ደቂቃ ላይ አቻም እና ሃሴት በዉሃ ዳር (ፏፏቴ)ላይ ሆነው እየተዝናኑ እና እየተጫወቱ ማለትም ከእስረኛ እና አሳሪነት ስሜት ወጥተው ወደ ጓደኝነት ህይወት እንደገቡ እና ያሉበትን ዋሻ ለቀው ዘና የሚያደርግ ቦታ ላይ እንዳሉ ጠቋሚ ሰጥቷል።



00፡37፡47



00፡21፡14

ምስል 6 የሩቅ ቀረጻ(Long shot)

## 3.2.5 ከትከሻ በላይ ቀረጻ

በዚህ የቀርጻ አይነት ከአንደኛው ገጸ ባህሪ አንጻር ትይዩ ሌላኛው ገጸ ባህሪ ያለዉን የትወና አትኩሮት ለማሳየት፣የሁለት ገጸ ባህርያትን የድርጊት ጥምረት ለማሳየት የሚረዳ እና የገጸ ባህርያትን ግንኙነት ያመለክታል።በዚህም መሰረት በ ደቂቃ ላይ አቻም ሃሰትን ጠልፎ ከወሰዳት በኋላ የማሬ አያትና ልዑል ለህግ አካል እናሳዉቅ ወይስ አናሳዉቅ በሚል ሃሳብ ሲከራከሩ እና ሁለቱ ቆመው ሲያወሩ ይታያል በዚህም መሰረት ።ይህን ምስልም ሲቀርጽም ከትከሻ በላይ የቀረጻ አይነት ለመጠቀም ችለዋል።00፡54፡57 ደቂቃ ላይ የማሬ አባትን ማሬ ስለ አቻም ፍልሚያ እና ልዑልን እንዴት ከመደናገጥ እና ነጻ ማዉጣት እንዳለባቸው ሲወያዩ ይታያል።ስለሆነም በዚህ ከትከሻ በላይ የቀረጻ አይነት መወሰዱ ሁለቱ ያላቸዉን መስተጋብር በማሳየት እና ሚስጥረኛ፣በሃሳብ በኩል ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን በማሳየት አገልግሎት ላይ ዉሏል።





00:50:16 00:54:57

ምስል 7 ከትከሻ በላይ ቀረጻ

## 3.2.6 pov (point of view)

Point of view የቀረጻ አይነት ከገጸ ባህሪው ዕይታ አንጻር የሚወሰድ ሲሆን የተዋናዩን የድብቅ ዕይታ ለማመላከት የምንጠቀምበት የቀረጻ አይነት ነው።በ 00:29:19 ደቂቃ ላይ ልዑልና ሀሴት ከመኪናቸው አጠገብ ቆመው ከጠላታቸው ለማምለጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሲመካከሩ አቻም በመደበቅ ጠመንጃዉን ደግኖ ሊተኩስባቸው ሲያጮልቅ እንመለከታለን ስለሆነም አቻም በጥብቅ እንደሚፈልጋቸዉ እና በድብቅ ሊገድላቸዉ እንደሆነ አመልክቷል። 00:34:02 ደቂቃ ላይ እነ ሃሴት አቻምን ፈርተው በጫካ ላይ በሚሮጡበት ወቅት የአቻም ተላላኪን አጮልቀው ሲመለከቱት በዚህ እይታ መጠቀማቸዉ ተደናግጠዉ በመሮጥ ታሪኩን ወደ ፊት እንዲሄድ አደርገዋል።

00፡29፡19 00፡34፡02

ምስል 8 ነጥብ እይታ ቀረጻ

### 3.2.7 የቅርብ ዕይታ ቀረጻ (clouse up)

ይህ የቀረጻ አይነት ከአንገት በላይ ያለዉን የሰዉነት ክፍል ብቻ በመለየት ወይም ከሰው ዉጭ የሆኑትን ለትዕይንቱ አስፈላጊ የሆኑ እቃ ሆነ ግዑዝ አካልን በቅርበት የምንቀርጸበት ሲሆን አገልግሎቱም የገጸ ባህርያትን ስሜት ለዉጥ እና እንቅስቃሴ በቅርበት የምንመለከትበት ነው።ነገር ግን በዚህ ፊልም ዉስጥ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ይህን የቀረጻ አይነት መጠቀም እያለበት ሳይጠቀም ቀርቶ ተስተዉሏል።ለምሳሌ በ 01፡01፡36 ደቂቃ ላይ አቻም ለ እና ማሬ ቤተሰብ የድርደር ሃሳብ ካቀረቡ በኋላ የማሬ አያት የመጡት ለሽምግልና ሳይሆን ለመሰለል እንደመጡ ይገባቸዋል ።በኋላም የአቻምን ወንድም እሰሩት ሲሉ አብሮት የመጣው መልዕክተኛም እኔ ለመያዣ ከዚህ እቆያለው እሱን ይልቀቁት ይላል።የማሬ አያትም በአሽሙር በጣም ጥሩ ሰው ነህ ብሎ ያሞግሰዉና ደስ ሲለው የማሬ አያት መልሶ አንተም እዚህ ትታሰራለህ አትሄድም ይለዋል። በዚህ ትዕይንት ላይም የተጠቀሙት የቀርጻ አይነትም የመካከለኛ የቅርበት ቀረጻ ሲሆን ለዚህ እንቅስቃሴ መደረግ የነበረበት የቀረጻ አይነት የቅርብ እይታ የቀረጻ አይነት መጠቀም ነበረበት ምክንያቱም ከ አቻም ወንድም ጋር የመጣዉ መልዕክተኛ መጀመሪያ ጥሩ ሰው ነህ ከተባለ በኋላ ደግሞ ታስረሃል ሲባል የሚሰማዉን የፊት ለውጥ ለተመልካች ግልጽ ሳይደረግ ቀርቷል ይህም ማለት ከተሞገሰ በኋላ ሊያሳየው የሚችል የፊት እንቅስቃሴን የተድበሰበሰ እና ግልጽ ያልሆነ የቀርጻ አይነት በመጠቀም የፊልሙን ተዓማኒነት ቀንሷል።



01፡01፡36

## 3.3 እንሳሮ ፊልም ከቀረጻ ማዕዘን አንጻር

### 3.3.1 የዝቅተኛ ማዕዘን ቀርጻ

ይህ የቀረጻ ማዕዘን የገጸ ባህርያትን ሃያልነት እና የበላይነት ለማሳየት የምንጠቀምበት የቀረጻ ማዕዘን ነዉ። ስለሆነም በዚህ ፊልም ዉስጥ 00፡38፡36 ደቂቃ ላይ ያለው ትዕይንት ላይ አቻም ልዑልና ሀሴትን ለመግደል  በሚፈልግበት ሰአት ከተራራዉ ላይ በግርማ ሞገስ ሲንጎራደድ ይታያል።ስለዚህ አቻም በዚህ ሰአት እሱ  የበላይ እና ሃይል መሆኑን አዘጋጁ ይህን የቀርጻ ማእዘን በተገቢዉ ጊዜ  ተጠቅሟል ምክንያቱም ይህን ቀረጻ መጠቀማቸው የአቻምን ግርማ ሞገስ የበላይ ነይ ባይነቱን በማንጸባረቅ አሳይቷል። በ 00፡28፡54 ደቂቃ ላይ አቻም ልዑል አለ ከተባለበት ቦታ ላይ ሂዶ ካገኛቸዉ በኋላ በንዴት ለመተኮስ ሲሄድ ያለዉን ትዕይንት ያሳያል፣ስለሆነም አቻም ሃያል፣የበላይ፣ገዳይ፣አስጨናቂ መሆኑን በዚህ ዝቅተኛ የቀረጻ ማዕዘን በመገለጹ ለተዋናዩን አትኩሮት እንድንሰጠው በማድረግ ጉልህ ሚና አበርክቷል።

እንዲሁም ይህ ፊልም በባህሪው የጀብዱ እና የሃይል እንደመሆኑ መጠን ብዛት ያላቸዉን የዝቅተኛ የቀረጻ ማዕዘን በመጠቀም ፊልሙን ለመግለጽ ተችሏል።ስለሆነም አግባብ ያለዉን በተለይም አቻም እና ማሬ ሁለቱም የሚያሳዩትን የአልሸነፍም ባይነት ሽቅድምድም በዚህ የቀረጻ ማዕዘን በማካተት እና ተመልካቾቹን ስሜት ዉስጥ ገብተው እንዲመለከቱ ግልጋሎቱን አሳይቷል።እነዚህም 00፡25፡37 ደቂቃ ላይ አቻም ተኩስ ከተራራዉ ላይ ሆኖ ሲለማመድ፣00፡47፡28 አቻም ያባቱን ጠላት አግኝቶ ሊገለው ሲል፣እነ አቻም ወደ ፍልሚያው ሃሴትን መያዣ አድርገው ለፍልሚያ በራስ መተማመን ሲሄዱ በዚህ ማእዘን አሳይቷል። 00፡ 27፡00 ደቂቃ ላይ ማሬ ልዑልን ጠላቶቹ ሊገሉት መሆኑን ስትሰማ ይሄን የቀረጻ ማዕዘን አገልግሎት ላይ አዉለዋል ይህ መደረጉም ማሬ ለቤተሰቧ ሃይል እና አቅም እንዳላት እንዲሁም ማንም ዘመዷን ለማዳን እንደማያግዳት ሊያሳየን በመፈለጉ ይህን ስሜት እንዲያጎላ በማድረጉም ለፊልሙ አስተዋጽኦ አድረጓል።





00፡38፡36 00፡28፡

54

ምስል 9 ዝቅተኛ ማዕዘን ቀረጻ



00፡27፡00

ምስል 10 ዝቅተኛ ማዕዘን ቀረጻ

## 3.3.2 የከፍተኛ ማዕዘን ቀረጻ (high angle)

ይህ የከፍተኛ ማዕዘን ቀርጻ በፊልሙ ዉስጥ ያሉ ገጸ ባህርያትን ያሉበትን የዝቅተኛ ስሜት፣ ፍርሃትን፣ ያልተጠበቀ ዱብዳን፣ጭንቀትን፣ሽንፈትን፣ እና የገጸ ባህርያትን የበታችነት ስሜትን ለማሳየት በሚፈልግበት ጊዜ የሚጠቀመው የቀረጻ ማዕዘን አይነት ሲሆን በዚህ ፊልም ዉስጥም በ 00፡29፡59 ደቂቃ ላይ አቻም

ሲተኩስ ልዑልና ሀሴት ተደናግጠው ሲሮጡ ሾፌሩ መኪናው ዉስጥ ስለነበር አቻም ጎትቶ ያስወጣዉና ጠመንጃዉን ደግኖ ሲያንገራግረው እና ሾፌሩ ሲርበተበት ያላሰበው ነገር ስላጋጠመው ሲደናገጥ ያመለክታል።ስለሆነም ይህ የቀረጻ ማዕዘን በተገቢው ቦታ በመጠቀሙ እና የሾፌሩ መጨነቅ፣መርበትበት የበታች እና በቁጥጥር ስር መሆኑን ለማመላከት በማሰብ ለተመልካች ገላጭ ሆኖ በዚህ ፊልም ዉስጥ ተካቷል።

በተጨማሪም በዚህ በከፍተኛ ማዕዘን የቀረጻ አይነት መቀረጽ እያለባቸው አላስፈልጊ እና ምክንያታዊ ያልሆነ እና ከያዘዉ መልዕክት ጋር ያለተዋሃደ በልከኛ የቀረጻ አይነት ሲጠቀም ተስተዉሏል።ይሄዉም በ00፡42፡45-00፡43፡33 ባሉት ሰከንዶች ዉስጥ ሃሴትና ልዑል ጅብ መጠባቸው በጫካ በሚሮጡበት ጊዜ እጅግ ሲፈሩ እና ሲደናበሩ ይታያል ነገር ግን የበለጠ መፍራታቸዉን፣ ተስፋ መቁረጣቸዉን፣ከዚህ ስቃይ እና መከራ ሊገላግላቸው የሌለ መሆኑን መደናበራቸዉን ለማንጸባረቅ ያስችላቸው ዘንድ የከፍተኛ ማዕዘን ቀረጻን በመጠቀም ተመልካቹን ለማሳመን እና የታሪኩ አንድ አካል ማድረግ ይቻል ነበር። ነገር ግን በዚህ ትዕይንት ላይ የተጠቀሙት የቀረጻ ማዕዘን ልከኛ የቀረጻ ማዕዘን እና በልከኛ ስሜት ጊዜ የምንጠቀመዉን ማዕዘን በመገልገል ሀሴት እና ልዑል የገቡበትን ዉጣ ዉረድ ፣ዉጥንቅጥ በደንብ ምስል ለመከሰት ባለመቻል ያልተገባ የቀረጻ ማዕዘን በመወሰዱ ይህ ትዕይንት መልካም ሳይሆን ቀርቷል።



00፡29፡59

ምስል 11 የከፍተኛ ማዕዘን ቀረጻ

## 3.3.3 የሰያፍ ማዕዘን ቀረጻ (oblique)

የሰያፍ ማዕዘን ቀረጻ ወደ ጎን ያጋደለ የቀረጻ ማዕዘን ሲሆን ከመደበኛው የቀረጻ ማዕዘን በ 40% ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ያጋደለ ሲሆን አገልግሎቱም የአንድን ገጸ ባህሪ የተዛባ ፍርድን ያልተጠበቀ ዱብዳን ፣ መጨናነቅን፣መደናበርን እና በሃሳብ መዋዠቅን የመሳሰሉትን ስሜቶች መገለጽ ስንፈልግ የምንጠቀመው የቀረጻ ማዕዘን ሲሆን በዚህ ፊልም ዉስጥ 00፡33፡17 ደቂቃ ላይ አቻም ሾፌሩን አንገራግሮ ከለቀቀው

በኋላ መኪናዉን ይዞ ወደ ህግ አካል በመደናበር እና በድንጋጤ ሲነዳ ማሳየቱ ሹፌሩ እንደተወዛገበ፣ እንደተጨናቀ፣የማያዉቀው ዱብዳ በማያዉቀው ሃገር የማያዉቀው አስደንጋጭ ነገር እንደተከሰተበት፣ መዉጫ መግቢያው እንደጠፋው ስሜቱን መቆጣጠር እንደተሳነው በመኪናዋ መጋደል ተገልጿል።ይሄን የቀርጻ ማዕዘን በተገቢው ጊዜ ለመጠቀም ችሏል ።



ምስል 11 የሰያፍ ማዕዘን ቀርጻ

## 3.3.4 የወፍ ዕይታ ቀረጻ ማዕዘን

አዘጋጆች ይህን የቀረጻ ማዕዘን የሚጠቀሙት ታሪኩ የሚፈጸምበት ቦታ እና የጊዜዉን ድባብ ከላይ ወደ ታች በወፍ ዕይታ ማዕቀፍ ለማሳየት የምንጠቀምበት

የቀረጻ አይነት ነው ።ይህ የቀረጻ አይነት በሄሊኮፍተር፣በአዉሮፕላን ወይም በብራሪ ቁስ አካል በመጠቀም በከባድና ቀላል መቅረጽ ምስል አማካኝነት ቀረጻዉን ያካሂዳሉ።ይሄም ያልተጠበቀ ክስተት ፣ፍርሃትን ፣ ፍሊጋን ፣ጊዜን ቦታን አልፎ መጓዝን ለመግለጽ የሚጠቅም የቀረጻ አይነት ነው። 00:16:50 ደቂቃ ላይ በተሽከርካሪ መኪናቸው ሲሄዱ ያለዉን ትዕይንት በዚህ የቀረጻ ማዕዘን መግለጹ የአካባቢዉን መልከዓ ምድር በማስቃኘት እና በማስተዋወቅ ጉልህ ሚና አበርክቷል። ይሄም ማለት ሰፊ የሆነ ዳራን ለማስቃኘት የምንጠቀምበት እንደመሆኑ መጠን በቦታው ትክክለኛዉን የቀረጻ ማዕዘን ተጠቅመዋል ። 00፡01፡03 ደቂቃ ላይ ያለዉን ትዕይንት በዚህ የቀረጻ ማዕዘን በመጠቀም ከላይ ሆኖ እነ ልዑልን እየፈለጋቸው መሆኑን ያመላክታል። 00፡42፡35 እነ ልዑል በጫካው ላይ የጅብ ድምጽ ሰምተው ሲደናገጡ በዚህ የቀረጻ ማዕዘን መታየቱ እነ ልዑል ያሉበትን ስቃይ ፍርሃት መደናበርና ያሉበት ቦታ ገደላገደል ዉስጥ መሆኑ ደግሞ የበለጠ ስቃይ ዉስጥ መሆናቸዉን በማሳየት አሳተዋጽኦ አድርጓል።





00:16:50 01፡27፡03

ምስል 12 የወፍ እይታ ቀረጻ (bird eye view)

### 3.3.5 ልከኛ የቀረጻ ማዕዘን

የፊልም አዘጋጅ መቅረጽ ምስል ማዕቀፍ የሚጠቃለለዉን የገጸ ባህርያት ሰዉነት ወይም የቁስ ክፍል በሰው ልጅ አይን ዕይታ ደረጃ የርቀት መጠን የሚቀረጽበት የመቀረጸ ምስል አይነት ነው፡፡ 00፡23፡43 ደቂቃ ላይ እነ እነ ሃሴት መጠጥ ቤት ላይ ተቀምጠው ሲጨዋወቱ ይታያል ስለሆነም ይህ ስሜት በዚህ ሰአት የተረጋጋ እንደመሆኑ መጠን የልከኛ አምዕዘን የቀረጻ አይነትን መጠቀማቸው እንደ ጥሩ ጎን ይወሰዳል፡፡01፡ 14፡34 ደቂቃ ላይ አቻም እና ሃሴት ቁጭ ብለው ሲጫወቱ ያለው ስሜት የተረጋጋ እንደመሆኑ መጠን በልከኛ የቀረጸ ማዕዘን በመቀረጽ ረጋ ተደርጓል ፡፡





00፡23፡43 01፡14፡34

ምስል 13 የልከኛ ማዕዘን ቀረፃ


እንዲሁም በዚህ ፊልም ዉስጥ ማሬ እና አወቀ ልዑልን ከአቻም ለማትረፍ መሳሪያቸዉን ይዘው ከወጡ በኋላ የማሬ አያት በማታ ጋቢያቸዉን ለብሰው 00፡42፡28 ደቂቃ ላይ ሲጨናነቁ ይታያል፡፡ነገር ግን እሳቸው በዚህ በጨለማ መጨናነቃቸዉን ተስፋ ማጣታቸዉን ማሬ አደጋ ሳይደርስባት የመመለሷ ጉዳይ በሃሳብ መብሰልሰላቸዉን ሊገልጽልን የሚችል የቀረጻ ማዕዘንን ማለትም  የከፍታ ቀረጻ (high angle)

ሊጠቀሙ ሲገባቸው የልከኛ ቀረጻ (eye view) የቀረጻ ማዕዘን በመጠቀም የተፈለገዉን ሃሳብ ሳያስተላልፍ ቀርቷል።አጥኚዉ ከታች ያለዉን ምስልም እንደምስክርነት ተጠቅሟል።



ምስል 14 የልከኛ ማዕዘን ቀረጻ

በተጨማሪም አቻም እነ ልዑልን በጫካው በሚያሯሩጣቸዉ ጊዜ 00፡43፡29 ደቂቃ ማታ እንደመሆኑ መጠን ጅብ ሲጮህባቸው ይሰማል።በዚህ ጊዜ ሀሴትና ልዑል ከነበረባቸው ዉጣ ዉረድ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ አስፈሪ ሲመጣ አስደንጋጭ ነገር መሆኑ ይታወቃል።በዚህ ጊዜም ሁለቱም ልጆች እጅግ በጣብ ይፈራሉ ይህን ፍራቻም ለተመልካች ትኩረት ለመስጠት መጠቀም የነበረባችዉ የከፍታ ቀረጻ አይነት (High angle) ነበር ምክንያቱም የተጋረጠባቸዉን አደጋ እና በሁለት አጣብቂኝ ዉስጥ እንደሆኑ መጠን ማለትም በአቻም አደን እና በጅብ መሃከል መከበባቸዉን የሚሰማቸውን ስሜት ለመግለጽ በከፍታ ማዕዘን መቀረጽ ነበረበት።ነገር ግን በዚህ ስሜት ላይ የተጠቀሙት የልከኛ የቀረጻ ማዕዘንን ሆኖ ተገኛቷል ስለሆነም በዚህ ቀረጻ ላይ ስህተት ተሰርቷል።



## 3.4 እንሳሮ ፊልም ከብርሃን አጠቃቀም አንጻር


ግብዓተ መብራት የፊልሙ አንድ አካል ሆኖ ስሜቶችን በተመልካቹ ዉስጥ እንዲጋባ እና ታሪኩን ከመቸቱ አጣምሮ የታሪኩን ቦታ እና ጊዜ በመገለጽ ምትሃት በመፍጠር አያሌ ሚና ከሚጫወቱት መካከል ግብዓተ

መብራት ነው። በዚህም መሰረት እንሳሮ ፊልም ሲዘጋጅ ሁለቱንም የመብራት አይነቶች ማለትም ሰው ሰራሽ ብርሃን እና የተፈጥሮ ብርሃን አይነቶችን ለመጠቀም ችሏል።የእንሳሮን ፊልም የመብራት አጠቃቀሙን ስንመለከትም አብዛኛዎቹ የቀረጻ ጊዜያቶች ወይ ትዕይንቶች የቀን ድባብን ተከትለው የተቀረጹ እንደመሆናቸው በይበልጥ የተፈጥሮ እና (high key lighting) የመብራት አይነቶችን በመጠቀም የተዘጋጀ ነው ።ነገር ግን ምንም እንኳን በብዛት እነዚህ የመብራት አይነት ቢጠቀምም ሌሎችን የመብራት አይነቶች አልተጠቀመም ማለት አይደለም።

በዚህ ፊልም ዉስጥ 00:39:40 ደቂቃ ላይ አቻም እነ ልዑልን ተኩሶ ካስደነገጣቸው በኋላ ወደ ጫካ ገብተው ለማምለጥ ሲሮጡ አቻም ቀኑን ሙሉ ሲያሳድዳቸው እንደዋለ እና ረጅም ሰአት ሲያንገላታቸው መቆየቱን የፀሐዩአን ማዘቅዘቅ በካሜራ ማዕቀፍ ዉስጥ በማስገባት ማለትም የተፈጥሮ ብርሃንን በመጠቀም ጥሩ የሆነ ገለጻ ተደርጓል። ደቂቃ ላይ ጊዜው መምሸቱን በማስገንዘብ አገልግሎት ላይ ዉሏል።

እንዲሁም 00:39:53 ደቂቃ ላይ ሃሴትና ልዑል እየመሸባቸው መሆኑንም በፊት ከነበረው ብርሃን ደብዘዝ በማድረግ እና ምናልባትም እየጨለመባቸው እና ሊገጥማቸው የሚችለዉን እና ከፊታቸዉ ያለዉን የተጋረጠ የኋላ ስቃይ ለማመላከት የተፈጥሮ ብርሃንን ሰአት በመጠበቅ የተቀረጸ ትዕይንት በመሆን ትዓማኒነቱ እዉን ሆኖ ታይቷል።





00:39:40 00:39:53

ምስል 15 የተፈጥሮ መብራት

በ00፡42፡28 ደቂቃ ላይ የማሬ አያት ኩታቸዉን ለብሰው ከጨለማ ላይ ብቻተዉን ቆመው ይታያሉ ምክናያቱም አቻምን ልዑልን የአባቱ ገዳይ መሆኑን ካወቀ እንደሚገለው ሲያዉቁ ማሬን አስታጥቀው ልጁን እንድታድነው ከላኳት በኋላ ለልጆቻቸው መጨነቃቸዉን ማሰባቸዉን፤ መረበሻቸዉን በ(low key lighting)ወይም የጨለማ የመብራት አይነት በመጠቀሙ ይበልጥ ገጸ ባህሪው ያለበትን ሁኔታ ተመልካቹ እንዲጋራው እና ከስሜቱ ጋር አብሮ እንዲዞር ተደርጓል ይህ ትዕይንትም እሳቸው በብዙ ነገር የተወጠሩ የተጨነቁ በማድረግ ምስል ከሳች በማድረጉ ይበል የሚያስብል ስራ ሰርቷል።

በፊልሙ 01፡04፡48_01፡06፡32 ደቂቃ ላይ ከእነ ማሬ ቤት ልዑልን እንዲበረታ ማሬ እና አያቷ ሲመክሩት ይታያል በዚህ ትዕይንት ላይ የተጠቀመው የመብራት አይነት ሰው ሰራሽ የሆነዉንና ቱባዉን የገጠሩን ባህል የሚያንጸባርቅ የማገዶ እሳትን በመጠቀም ቤቱን የጨለማ ብርሃን አድርገው ጊዜዉን እና የቤቱን ትክክለኛ ድባብ እንዲኖረው በማድረግ አሪፍ የመብራት አጠቃቀም ታይቷል።ከዚህም በስተጀርባ ግን በዚሁ ትዕይንት ላይ ከማገዶው እሳት ጋር የሚመሳሰል አይነት ሆኖ ከስክሪኑ ላይ ቦግ እልም ቦግ እልም በማድረግ ድባቡን ለመግለጽ ለመሞከር የታሰበው ስራ ጥሩ አልነበርም።ምክንያቱም ቦግ እልም በሚልበት ወቅት አርተፊሻል ወይም ቅንብር እንደሆነ ያሳብቃል።በዚህም ምክንያት ለመተልካች ምቾት ሳይሰጥ ቀርቷል።

በ 01፡27፤05 ደቂቃ ላይ እነ ማሬ ተኩስ ለመለማመድ ከሄዱበት ሲመለሱ ማሬ ከፊት ሆና ስትመራው ከሁዋላዋ የሚታይ የተፈጥሮ ጸሀይ የጠዋት መሆኑን እና ለስልጠና በማለዳው እንደወጡ ለማሳየት የተፈጥሮ ብርሃንን በመጠቀም ታሪኩን አስኪደዋል ።እንዲሁም በዚሁ ትዕይንት ላይ አላስፈላጊ ተንቀሳቃሽ ያፈተለኩ ቀለም ያላቸው መብራት ተስተዉለዋል።

## 3.5 እንሳሮ ፊልም ከሙዚቃ እና ድምጽ አጠቃቀም አንጻር

ግበዓተ ድምጽ አንድን የፊልም ታሪክ በምትሃት ለማስቀጠልና የተመልካችን ስሜት ከተዋናዩ የስሜት ሁኔታ ጋር እያዋዛ ታሪክን ጊዜን ቦታን የሚያመላክተን የአላባዉያን አይነት ነው ።ስለሆነም በዚህ ፊልም ዉስጥም የተለያዩ የሙዚቃ የድምጽ እና የልዩ ግብዓት ድምጾችን በፊልሙ ዉስጥ በማካተት ታሪኩን ታአማኒነት እንዲኖረው ተድርጓል ። በዚህም መሰረት በዚህ ፊልም ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት አብዛኞቹ ማጀቢያ ሙዚቃ ተብለው የገቡት የተፈለገዉን መልዕክት ሳያስተላልፉ ሲቀሩ ይታያል።ከእነነዚህም መካካል 00፡11፡16 ደቂቃ ላይ እነ ልዑል ወደ ገጠር በመኪና ሲሄዱ የማጀቢያ ሙዚቃ ተጠቅመዋል ።ነገር

ግን ይሄ ድምጽ የተቆራረጠ እና ለጆሮ በማይመች መልኩ የተከተተበት ሁኔታ አለ ስለዚህም የፊልሙን ዉበት ቀንሶታል።

በተጨማሪም 00፡20፡27 ደቂቃ ላይ ማሬ እንጨት ስትለቅም ይታያል።ስለሆነም በዚህ ጊዜ ማሬ ያለችበት አካባቢ ገጠር እንደመሆኑ የልዩ የድምጽ ግብዓትን (special sound)በመጠቀም ማሬን በድምጽ ብታንጎራጉር መልካም ይሆን ነበር ።ይሄም የተባለበት ምክንያት ወደ ገጠር አካባቢ የሚገኙ ሰዎች ብቻቸዉን ሲሆኑ ማንጎራጎር ልማዳቸዉ ስለሆነ ነዉ።

በዚህ ፊልም 00፡02፡04 ደቂቃ ላይ ሁለት ህጻናት ማሳ ላይ እየተጫወቱ በሚገኙበት ግዜ ከርቀት የጥይት ተኩስ ይሰማል።የተኩሱ ድምጽ መካተቱ መልካምነት እንዳለ ሆኖ ህጻናቱ ትንሽ እንደሮጡ ማለትም በ00፡02፡19 ደቂቃ ላይ በልጆቹ ሩጫ ጋር የሚዋሃድ ማለትም ጉጉት የሚፈጥር ግብዓት  ድምጽ ለመጠቀም ቢችሉ ኖሮ ተመልካች ምን ተፈጥሮ ይሆን? ማን ተኩሰ?ለምን ተተኮሰ? ልጆችስ ለምን ሮጡ?የሚሉትን ጥያቄዎች ተመልካቹ በጥያቄ ዉስጥ እንዲቆይ በማድረግ በስሜት እንዲቆይ ለማድረግ ይችሉ ነበር።

00፡04፡04 ደቂቃ ላይ ትዕይንት ሲቀየር ገጠር የነበዉ መቸት ወደከተማ የተለወጠበት ነው።ስለሆነም መቸቱን ለማወቅ ከሚያግዙ ነገሮች አንዱ ግብዓት ድምጽ ነው ስለሆነም መቼቱ ከተማ መሆኑን ሲጠቁመን የመኪና እና ሞቅ ያለ ጫጫታ በመጠቀም ተአማኒነቱን አጠናክሯል።

00፡04፡43 ደቂቃላይ  ሀሴት ልዑል ቀርቶባት ስልክ ስትደዉል ከ ልዑል ስልክ ላይ መጀመሪያ ይጠራል ቀጣይም የልዑል እናት ከሳሎን ሆና የስልኩን ጥሪ ከርቀት ትሰማዋለች።እንዲሁም ሃሴት ላይ የሚያስተላልፈው ጥሪ የገባበት የድምጽ አጠቃቀም አሪፍ ነበር።

00:07:33 _00፡07፡53 ደቂቃ ድረስ እነ ልዑል ወደ ገጠር እየሄዱ መሆናቸዉን ለመጠቆም የቀረርቶ ድምጽ ተጠቅመዋል።ይህ ግብዓት ድምጽ ለመቸቱ ትክክለኛ የግብዓት ሙዚቃ ቢሆንም ግን የጊዜ ቆዪታው ያልተሰላ እና ምክንያታዊ ያልሆነ የድምጽ መቆራርጥ በመታየቱ የገባው ድምጽ መልዕክቱን ጥርት ባለ መልኩ ለማስተላለፍ አልተቻለም።

እንደአጠቃላይ በዚህ ፊልም ላይ ገና መጀመሪያ የገጠር ትዕይንት በሚያሳዩበት ጊዜ መጠቀም የነበረበት አካባቢዉን የሚወክል እና ድባቡን ሊገልጽ የሚገባዉን ሲኖርበት ከመቼቱ ጋር የማይሄድ ድምጽ በመጠቀሙ ስሜቱን አጥፍቶታል።

00:22:23 እነ ልዑል ከሰፈር ጠላ ቤት ተቀምጠው ስለሃገሯ ጥሩነት  እና ስለተወለደበት አካባቢ ሲያሞጋግስ ያለበት ትዕይንት ላይ የተጠቀሙት የጠላ ቤት (የጀርባ ሙዚቃ)በጣም አሪፍ እና የአካባቢዉን ቱባ የተንጸባረቀበት ሙዚቃ በመጠቀም የፊልሙን ድባብ በማጠንከር አግዟል።

00:09:46 ደቂቃ ላይ አቻም ተፈቶ ከእናቱ ቤት ቤተሰቡ ማዕድ ላይ ሆነዉ በሚመገቡበት ሰአት የተጠቀሙት የፒያኖ ድምጽ አላስፈላጊ እና ከ አካባቢው ጋር ፍጹም የማይሄድ ነው።ምክንያቱም አቻም መፈታቱን የሚያወድስ ጅግንነቱን የሚነግር ገጠርኛ ዘፈን ለሰስ አድርገው መልቀቅ ይችሉ ነበር።

00፡11፡34 ደቂቃ ልዑልና ሀሴት ለመስክ ስራቸው ከወጡ በኋላ ቀጥታ የሄዱት ወደ ገዳማት ጉብኝት ነበር።ነገር ግን ወደዚህ ስፍራ መሄዳቸዉን ምንም እንኳን በስክሪን ብንመለከተዉም ግን መቸቱን እና የትዕይንቱን ድባብ ትኩረት ሰጠን እንዳናየዉ አድርጎናል።በዚህ ፋንታ የሙዚቃ አዘጋጁ ከገዳሙ ጋር የሚጣመር የሙዚቃ ግብዓት ባለማስገባቱ የዚህን ፊልም ትዕይንት አደብዝዞታል።ይልቁንስ የኦርቶዶክስ መዝሙሮች እና በገና ድርድሮችን የሙዚቃ አይነቶችን መጠቀም ያለበትን ወሳኝ ነገር ሳያካትት የቀረበትሁኔታ አለ።

## 3.6 እንሳሮ ፊልም ከትወና አንጻር

አጥኝዉ ይሄን ፊልም ከትወና መሰረታዊ ሃሳብ አንጻር ሲሰራ በዚህ ፊልም ዉስጥ ገጸ ባህርያትን ወክለው የሚጫወቱ ሰዎች የተሰጣቸዉን ገጸ ባህሪ በምን አይነት መልኩ ተዉነዉታል፣እንዴት ዋና ዋና ገጸ ባህርያትን ገልጸዉታል?የአተዋወናቸዉ ስልትስ ምን ያህል ነው ተመልካችን አሳምኗል በሚለው መሰረት የእንሳሮን ፊልም በመለየት ምክንያታዊ ሂስ ይሰጣል።ስለሆነም በዚህ ፊልም ዉስጥ የተሳተፉት ዋና ዋና ተዋናዮችም አማኑኤል ሃብታሙ አቻምን ወክሎ፣መስከረም አበራ ማሬን ወክላ፣ምስጋና አጥናፉ ልዑልን ወክሎ፣ማርያማዊት አባተ ሃሴትን በመከል ፊልሙ ላይ ተሳትፈዋል በዚህም መሰረት አማኑኤል ሃብታሙን ስንመለከተ አጠቃላይ የትዎና ስልቱ ገጸ ባህርያቱን የገለጸበት መንገድ ይበል የሚያስብል እና የተመልካችን ስሜትና ቀልብ ሲቆጣጠር ተመልክተናል።

ስለሆነም አማኑኤል እኩይ የሚባል እና ተጻራሪ ገጸ ባህሪን ሚና ይዞ የሚጫወትልን እና ግንባር ቀደም ሆኖ የምናገኘው ይሆናል።ስለሆነም አማኑኤል ሙሉ ሰዉነቱን በመጠቀም ማለትም በአይኑ ማጉረጥረጥ በፊቱ ንዴትና ቁጭት ገጸ ባህሪዉን በመገንባት በትክክል  ስራ ላይ ያዋለ ሲሆን እንዲሁም በአረማመዱ ጥይት አያያዝ ንቃቱ ፣በኮስታራነቱ፣በአባቱ ሞት ምክንያት የተጎዳ መሆኑን በአካላዊ እንቅስቃሴዉ ጥርት እና ኩልል አድርጎ ምስል ከስቷል።በአጠቃላይ አማኑኤል የያዘው ገፀ ባህሪ ፣ጀግና ፣ሽንፈትን የማይወድ፣ ፍትህ ፈላጊ፣የአባቱን ደም መመለስ የሚፈልግ፣አስነዋሪ ስራ መስራት የሚጸየፍ፣ለሴት ልጅ ክብር የሚሰጥ ተደርጎ ተስሏል፣ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ ዩሆን ዘንድ 00፡12፡29 ደቂቃ ላይ ይህ ተዋናይ ጠላ ቤት ተቀምጦ እየጠጣ ባለበት ወቅት ሌሎች የጠላ ቤቱ ደንበኞች መጥተው ከጠላ ቤቷ ባለቤት ጋር እሰጣ ገባ ዉስጥ ሲገቡ እና በጉልበት ሴትዮዋን አሸቀንጥረው ሲጥሏት አማን የነበረዉን ግብረ መልስ በአይኑ እነዛን

ጎረምሶች ሲገላምጣቸው እና ተነስቶ ሁሉንም በዱላ ብቻዉን ሲጥላቸው አማን ጉልበተኛ ደመ ፍሉ እና ቁጡ እንደሆነ በዚህ ትወናው አሳይቷል።

እንዲሁም 01፡25፡05 ደቂቃ ላይ አማን ዋሻ ዉስጥ ሆኖ እነ ለመግደል ዝግጅት በሚያደርገበት ወቅት አጎቱ መልዕክት ሊያደርስ ሲመጣ በሩቅ የእግር ኮቴ ይሰማል። እናም በዚህ ጊዜ አቻም ሌላ ጠላት የመጣበት ሲመስለው መሳሪያዉን በመደገን በጥንቃቄ የሰማዉን የግር ኮቴ ለማጣራት በእርምጃው እና በአይኑ አትኩሮት እንዲሁም በመሳሪያ አያያዙ ገልጾታል ይሄም አማን ኮስታራ ጥንቁቅ እና ብዙ ጠላቶች ያሉበት በመሆኑ ተጠራጣሪ መሆኑን በዚህ ትወናዉ ገልጾታል።

በዚህ ፊልም ዉስጥ በቀጣይ የምንመለከታት ደግሞ መስከረም አበራ ማሬን ወክላ የተጫወተችዉን ይሆናል። ይህች ተዋናይት በፊልሙ ዉስጥ እጅግ ጎልታ የታየች እና ታሪኩን ወደፊት ስታስኬደው ትታያለች። ስለሆነም እያንዳንዷን ስሜት በአይኗ በፊቷ ገለጻ እንዲሁም በአጠቃላይ ሰዉነት እንቅስቃሴዋ ገጸ ባህሪዋን አጉልታለች። በዚህም መሰረት 00፡26፡57 ደቂቃ ላይ እንጀራ እየጋገረች ባለችበት ሰአት አባቷ መጥቶ ለዑልን ሊገሉት እንደሆነ ሲነግራት በንዴት እና አይኑዋን በማጉረትረጥ አልሸነፍ ባይ እንደሆነች እና በቤተሰቧ ድርድር እንደማታዉቅ በአይኑዋ እና በመላ ፊቷ አንጸባርቃለች።

መስከረም በአካባቢያችን ባህልና ወግ መሰረት ሴት ልጅ ቤት ለቤት እንጂ አደባባይ መዉጣት አትችልም የሚለዉን አቋም ገርስሳ በመወጣት ሴት ልጅ የወንዱንም ስራ በብቃት ትዋጣለች የሚለዉን በትወና ብቃቷ አሳምናለች። ለምሳሌ 00፡28፡27 ደቂቃ ላይ አባቷ እንድትጠነቀቅ እና ብቻዋን እንዳትሄድ ሲነግራት መላው ፊቷን በመለዋወጥ አይኑዋን በማፍጠጥ እንዲሆን ጠንከር ባለ ቃለ ፊልም ማለትም እስኪ ይድረሱብኝ እና አይናቸዉን ጎልጉየ ነው የማዎጣው በማለት ወኔዋን አልሸነፍ ባይነቱዋን በራስ መተማመኗን ሴት የሚለዉን ነገር እንደማታምንበት በተወናዋ ገልጻዋለች።

በዚህ ፊልም ዉስጥም በቀጣይ ያለዉን ተዋናይ ስመለከት ምስጋና አጥናፉ ማለትም የልዑል ገጸ ባህሪ ወክሎ የሚጫወትልን ነው። በዚህ ፊልም ዋናው ባለታሪክ እና ሰናይ ገጸ ባህርይን ይዞ የሚጫወት ሲሆን ልዑል ከከተማ ወደ አደገበት ገጠር እንሳሮ ለስራ በመሄድ ባላሰበበት ዉጣዉርድ ይከተታል።ልዑል በዚህ ፊልም ላይ በባህሪው ጸብ የማይወድ በመደባደብ የማያምን ሆኖ እንደመሳሉ መጠን ይሄን ባህሪዉንምም ከተሰጠው ገጸ ባህርይ ጋር በመስፋት ሲተዉን ተመልክቻለው።በዚህ መሰረትም ልዑል ይሄን ባህሪውን አሳማኝ አድርጎ አንዳንድ ቦታዎች ላይ አሳይቶናል።

ለምሳሌ አቻም ሃሴትን መይዣ አድርጎ ዋሻ ከወሰዳት በኋላ የማሬ ቤተሰቦችም ልጅቷን ለማስመለስ ግጠመኝ ማለት ነው አቻምን መዋጋት ነው ብለው ሲመካከሩ ልዑል በመበርገግ ከተቀመጠበት ይነሳል።

እንዲሁም ማሬም የምንገጥመው እኮ በቡጢ ወይም ትግል አደልም በጥይት ነው ስትለው በድጋሜ ሲንቦቃቦቅ እና ደንግጦ ሲቀመጥ አይተናል።ይሄም ፈሪ ጸብ የማዪዎድ መሆኑን በትወናው አሳይቶናል።

በተጨማሪም ምስጋና ማሬ የተሰኘችዉ ገጸ ባህሪ ጠላት ስለመጣባቸው ምስጋናን የጥይት ልምምድ ማድረግ እንዳለበት ወስና ከዚያም ለፍልሚያው እንዲዘጋጅ ነግራው ወደጫካ ሊሄዱ ሲሉ 01፡08፡22 ደቂቃ ላይ ከግቢው በር ላይ በመቆም ሲያዎላዉል እና የመሳሪያ አያያዙም ፍዝ ቸልተኛ ሆኖ ሲተዉን ይታያል። ስለሆነም ምስጋና በዚህ ትወናው የምርም ፈሪ እንደሆነ አመላክቷል።

## 3.7 እንሳሮ ፊልም ከፊልም ቅንብር አንጻር

የፊልም ኤዲቲንግ ከፊልም ቀረጻ በኋላ ያለ የፊልም ሰሪው አንድ አካል ነው ።ፊልም ኢዲቲንግ የሚለው ቃል የተወሰደው ፊልምን ማረም ወይም ማስተካካል እንዲሁም አስፈላጊ ነገሮችን መጨመር የሚለዉን ሀሳብ የሚተካ ተደርጎ ነው።ሰለሞን መኮነን “የፊልም ጥበብ ገበታ”ፊልም ኤዲተሮች ተቀርጾ የመጣላቸውን ፊልም አንግሎች ፊልም አንግሎች ቅደም ተከተሎችን ድምጽና የምስል ጥራቱን ከግምት ዉስጥ በማስገባት የሚሰራ ስራ ነው።በዚህ መሰረት እንሳሮ ፊልም በምን መልኩ የቅንብር ስራዉ ተሰርቷል የሚለዉን አጥኝዉ ይዳስሳል።

የእንሳሮ ፊልም ቅንብሮች በመልካም እና መልካም ባልሆኑ ብዙ ስራዎች የተከበበ ነው ።ቅንብር በአብዛኛዉ

ከ ተዋናዩ ስሜት ጋር፣ ከቃለ ፊልም ጋር ከእጅ ከእግር ሙዚቃን ከትወና መብራትን ከድባቡ ጋር አሊያም ከሌላ እንቅስቃሴዎች ጋር በእኩል ስሜት እና ታይሚንግ ጋር መቀናበር የግድ ይለዋል።

00፡07፡38 ደቂቃ ላይ እነ ልዑል ወደገጠር እየሄዱ ባለበት ጊዜ መቸቱን ለመግለጽ የቀረርቶ ሙዚቃ ይሰማል። ይህ ግብዓት ሙዚቃ ጥሩ ቢሆንም የገባው ድምጽ በተደጋጋሚ ሲቆራረጥ ይሰማል።ስለሆነም በዚህ ትዕይንት ላይ ሙዚቃዉን ለተፈለገው አላማ ለመጠቀም የቅንብር ጉድለት ተከስቷል።

00፡12፡34 ደቂቃ ላይ አቻም የጠላ ቤቷን ባለቤት የሰፈሩ ጎረምሶች ገፍትረው ጥለው እሱንም ሲተናኮሉት የተናደደው አቻም ተነስቶ ሁሉንም በዱላ እየመከተ ሲደፋቸው እና ተደቅኖ የነበረዉን ትይት ወደ ላይ ሲያስይተኩሰው ያለውን ትወና በቅንብር የታገዘ እና እዉነታዉን ያልቀቀ ማለትም ሰዎቹ ተደብዳቢዎች እየተሙቱ ሲወድቁ ያለዉን በቅንብር ለማሳመን ተችሏል።

00:29:15 ደቂቃ ላይ አቻም እነ ልዑልን በጥይት ሲያድናቸው ቆይቶ በኋላ አነጣጥሮ ሲተኩስባቸው ከ አፈሙዙ የወጣዉ ጥይት እንዲሁም ተኩሶት ከመኪናው መስታዉት ላይ ጥይቱ ሲያርፍ ያለዉን ማለትም ጥይቱ የምርም እንደተተኮሰ በቅንብር ለተመልካቹ አሳማኝ በሆነ መንገድ ተቀናብሯል።

00፡35፡37 ደቂቃ ላይ አቻም በጫካው እያስሮጠ ካስገባቸው በኋላ ተከታትሎ ሲተኩስባቸው እና እነሱ ላይ የ ምስል መርገብገብ ታይቷል። ይህ መርገብገብ የአደጋን ምልክት ለማሳየት ቢሆንም የተጋነነ የምስል ቅንብር ተጠቅመዋል።

00፡37፡47 ደቂቃ ላይ ሹፌሩ ይህግ አካል ጠይቆ ፖሊሶችን ከ ፖሊስ ጣቢያ ሲያወጣቸው በዚህ ደቂቃ ላይ ሲህተት የሆነ እና የማያሳምን ቅጽበታዊ ስሎዉ ሞሽን ቅንብር ተጠቅመዋል።

## 3.8 እንሳሮ ፊልም ከገጽ ቅብ አንጻር

ገጽ ቅብ (makeup)የሚፈልገዉን ገጽታ ለመፍጠር ድርሻዉ ቀላል አይደለም ።ገጽ ቅብ የተዋናዩን ማንነት ፈጽሞ ወደተለየ ሌላ ማንነት የመቀየር አቅም አለው።እንሳሮ ፊልምም ለታሪኩ ግብዓት እና ተዓማኒነት እንዲኖረው ያስቻለው ዘንድ በገጽ ቅብ በኩልም ድጋፉን አግኝቷል።

00፡03፡36 ደቂቃ ላይ የ አቻም አጎት ክንዴ ከተኩሱ በኋላ (ከአቻም አባት ግድያ) የቀኝ እግሩ በጥይት ተመቶ ይታያል።በዚህ ትዕይንትም የተጠቀሙት እግሩን መመታቱን ለማሳየት መሆኑ እንደጥሩ ነገር ይታያል።ነገር ግን እግሩ ላይ የተጠቀሙት ሜካፕ የደረቀ እና ቀላ ያለ ሜካፕ ተጠቅመዋል በዚህም ምክንያት በተወሰነ መልኩ ተአማኒነቱን ቀንሶታል።ምክንያቱም ሰዉየው በጥይት ከተመታ ያለው ደቂቃ አጭር ስለሆነ  አዲስ የደማ በዛ ያለ እና ትኩስ ጠቆር ያለ ደም ቢጠቀም ለተመልካች ተአማኒነቱን ይገልጽ ነበር።

እንዲሁም የአቻም የፊት ገጽ ላይ የተሰራው የፊት ጠባሳ የአቻምን ከዚህ በፊት የአባቱን ደም ለማስመለስ ከደመኞቹ ጋር እንደሚጣላ እንዲሁም ጀግና መሆኑን የሚያመለክት ነው።ስለሆነም የአቻምን የፊት  ጠባሳ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ተጠቅመዋል።

የክንዴ የፊት ገጻታ ደግሞ ከ ሰዉነት አካሉ እና እንቅስቃሴው ጋር የሚዛመድ ሆኖ የፊት ገጽታ ማድያት ያለበት ተደርጎ መሰራቱ ጠንካራ ጎኑ ነበር።

በተጨማሪም ከማሬ ላይ የምንመለከተው ገጽ የመደበኛው ቅላቷን ለማደብዘዝ የተጠቀሙት የገጽ ቅብም አሪፍ ነው።ምክንቱም ማሬ ለቤተሰቦቿ እንደ ሴትም እንደወንድም የምታገለግል እንደመሆኑዋ መጠን ብዙ የሁኑ የስራ ጫናዎች ስለሚኖሩባት የፊት ገጿን ማድያት እንዲኖርባት እና አይኖቿ ላይ ጠቆር ጠቆር

በማድረግ በኑሮዋ ባለብዙ ዉጣ ዉረድ እና ብዙ ሃልፊነት እንዳለባት በማስመሰል ገጽ ቅቡ ለታሪኩ መልካም ግብአት ሆኗል።

ከዚህ በተቃራኒ ግን እንደ አጃቢ ተዋንያን የገቡ ተዋንያኖች ላይ በጥንቃቄ እንዳልተሰሩ ያስታዉቃል። ለምሳሌ መጀመሪያው ላይ የአቻም አባት ከሚገደልበት ትዕይንት ላይ ሞተ የተባለው ሰው የጸጉር ስታይል የከተማ ማለትም ስናፕ ብለን የምንጠራዉን የጸጉር ስታይል ተጠቅመው ታይቷል። ይህ መሆኑም የፊልሙ አጠቃላይ ቦታ ገጠር እንደመሆኑ መጠን ቦታዉን የሚዎክል የገጽ ቅብ ማለትም ኖርማል የሆነ የጠጉር ቁርጥ አይነት ቢጠቀሙ መልካም ይሆን ነበር።

## 3.9 እንሳሮ ፊልም ከአልባሳት አንጻር

አልባሳት የምንመለከተዉን ፊልም ከመቸቱ ጋር እየተጋገዘ ድባብ እና ምትሃት የሚከተን የፊልም አንዱ ግብዓት ነው።በእንሳሮ ፊልም ላይም ባህሉን ወጉን እንዲሁም አካባቢዉን የሚሸት አልባስ ሲጠቀሙ ተመልክተናል። በዚህ ፊልም ዉስጥ መልካም ከሚባሉ ስራዎች መካከልም አልባስ አንዱ ነው።

እንዲሁም 00፡01፡52 ደቂቃ ላይ ሁለቱ ህጻናቶች ማሳ ላይ ሲጫወቱ ያለበት ትዕይንት ገጠር ቦታ ላይ መሆናቸዉን ሁለቱንም ቁምጣ እና ኮት ለብሰው መታየታቸው ልጆችን ስናያቸው መቼቱ የገጠር ቦታ እንደሆነ ተዓማኒነቱን በማጉላት ለፊልሙ ጥቅም ዉሏል።

እንዲሁም ተተኩሶ ሰፈር ዉስጥ ላይ ያሉት እናቶች ሙሉ ከቤታቸው እየተሯሯጡ ሲወጡ ሁሉም አንድ አይነት አለባበስ ቀሚስ ወይም ሽብሽቦ ለብሰው ሲሮጡ ያለው አልባስ የአካባቢዉን ባህል እና ወግ የተከተለ በመሆኑ አልባሱ ከመቼቱ ጋር የተጣመረ እና አግባብ በመሆኑ ታዓማኒነት እንዲኖረው ተደርጓል። ለዚህም ማሳያ እና ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ የእንሳሮ ወረዳ ኮምኒኬሽን በሚለው የፌስቡክ ገጽ ላይ በተገኘዉ ምስል ተመሳክሯል።



የእንሳሮ አካባቢ አለባበስ



ፊልሙ ላይ የተወሰደው አልባስ

ምስል 16 የእንሳሮ ባህል አለባበስ እና በፊልሙ ላይ የተወሰደው አልባስ

ስለሆነም በዚህ ምስል እና ሌሎች ተያያዥ ምስሎች አንጻር በማደረግ የአልባስ ምደባ ወይም ምልከታው የተጠና እና አካባቢዉን መሰረት ያደረገ ነዉ። እንዲሁም አቻም የተጠቀማቸው ሙሉ አልባሶች የገጠር ድባብ ያለው እና ቦታዉን በደንብ የምገልጽልን እንዲሁም በዕንሳሮ የሚገኙ ወጣት ወንዶች የሚለብሱትን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው ስለሆነም ማህበራዊ ገጽ ላይ በተገኘዉ የሀገሩ ቱባ መሰረት ተጣቅሷል።






የእንሳሮ አካባቢ ወጣቶች ባህላዊ አለባበስ                 በፊልሙ ላይ የተጠቀሙት አልባስ

ምስል 17 የእንሳሮ ወጣት ባህል አለባበስ እና የእንሳሮ ፊልም አልባስ አጠቃቀም

በተጨማሪም በጠላ ቤቷ ትዕይንት ላይ ስለ ልዑል አባት ታሪክ ለልዑል ሲነገርው የነበረዉ ሽማግሌ ሰዉየ የተጠቀሙት አልባስ የአርበኛ ልብስ ነው።ስለሆነም ይህን ልብስ ለሰዉየው ማልበሳቸው ከዕድሚአቸው ጋር አብሮ የሚሄድና ስለ ልዑል አባት ጀግንነት ሲያወሩ ጀግና ወዳድ እና እሳቸዉም አርበኛ እንደነበሩ ያማለክታል።ስለዚህ ጥሩ አልባስ ተጠቅመዋል።

በአጠቃላይ በዚህ ፊልም ላይ የተጠቀሙት አልባሳቶች አብዛኛዉን አልባስ ከአካባቢው ወግ እና ስራአት እና ዶግማ ጋር ለማዛመድ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ ያመለክታል።ለምሳሌ የማሬ አለባበስ፣ፎጣው፣ጋቢዉ፣ ቲሸርቶችም የእንሳሮን አካባቢ የሚያንጸባርቁ በመሆናቸው አዘጋጁ በዚህ ረገድ ቦታዉን ዋጅቶ ጥሩ ስራ እንደሰራ ያስታዉቃል።

በተጨማሪም ከተገኘዉ መረጃ መሰረት ማሬ የለበሰችዉ አልባስ የዛው የእንሳሮ ባህል የሆነ እና ቦታን ለተመልካች በደንብ ለማሳወቅ የተደረገዉ ጥረት መልካልም ነዉ።ስለሆነም ማሬን ከታችኛው ምስል ጋር ስናመሳስል አዘጋጁ አልባስ ላይ መልካም ስራ ሰርቷል።





የእንሳሮ ሴቶች ባህላዊ አለባበስ　　　　　　　　　በፊልሙ ላይ የተጠቀሙት አልባስ

ምስል 18 የእንሳሮ ሴት ሴቶች ባህላዊ አለባበስ እና የእንሳሮ ፊልም አልባስ አጠቃቀም

## 3.10 እንሳሮ ፊልም ከመቼት አንጻር

መቼት የፊልሙ ታሪክ  የሚከናወንበት ቦታን ጊዜ ማለት ነው ።ለጭብጡም ሆነ ለአጠቃላይ ፊልሙ ዉጤትመቼት አካል ነው ።መቼት እንደሴራ ገጸ ባህሪ ፣ጭብጥ፣ግጭት፣ተምሳሌታዊነት ካሉት የፊልሙ አላባዉያን ጋር ዉስብስብና ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ በመቼት አማካኝነት የሚተላለፈው መልዕክት በአግባቡ በተመልካቹ ሊጤን ይገባዋል።

ስለሆነም አጥኝዉ እንሳሮ የተሰኘዉን ፊልም ከአጠቃላይ መቸት አንጻር ስመልከተው ከስሙ ለመነሳት ይሞክራል።ስለሆነም ይህ ፊልም ወደ ባህር ማዶ ተሻግሮ ለዕይታ ቢቀርብ ተመልካቹ ሊጠይቅ የሚችለው የት ሃገር ነው ከዚያም የት አካባቢ የሚለው ጥያቄ ስለሚያስቀድም ይሄን ለመመለስ ደግሞ አጥኝዉ የዚህን ፊልም አጠቃላይ መቼት ኢትዮጲያ አድርጎ ሌሎችን ዉስን መቸቶች ደግሞ እንሳሮ ወረዳ እንዲሁም አዲስ አበባ መሆኑን ያምናል።

በተጨማሪም የእንሳሮ ፊልም የቦታ አመራረጥ እጅግ ይበል የሚያስብል ቦታ እና ቦታው (tipical)ገጠር ቦታ መሆኑ በገደላ ገደሉ ጥሻው እንዲሁም ተራራው አማካኝነት መጤቱን በሚገባ አንጸባርቀዋል። እንዲሁም ገጸ ባህርያቱ በሚያወሩት ቃለ ተዉኔት ለምሳሌ የ “ቀ”ን ፊደል በመዋጥ ይበልጥ የአካባቢዉን የት እና መቼነት ገልጸዉታል።

እንዲሁም ይህ ፊልም ሲቀረጽ የተለያዩ ዉስን ቦታዎችን ተጠቅሟል።ከነዚህም መካከል አቻም ከዕስር ቤት ከተፈታ በኋላ የራሱን ምሽግ በመምሽግ እና በመሸፈት እንዲሁም ሃሴትን ከነ ማሬ ቤት ሄዶ አፍኖ ካመጣት በኋላ የሚቀመጥበት ዋሻ አለ። እንዲሁም የተለያዩ ዉስን መቼቶችን የተጠቀመ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ትዕይቱ ሲጀምር ያለው የልዑል እናት ቤት ማለትም አዲስ አበባ፣ የእነ ሐሴት የስራ ቦታ ቢሮ፣ የማሬ ቤተሰብ ቤት እንዲሁም የአቻም ቤተሰቦች መኖሪያ ቤቶችን በመጠቀም ታሪኩን አስኪደዉታል።

በዚህ ፊልም ዉስጥ አብዛኛዉን የጀብዱ ትዕይንቶች እንደመሆናቸው መጠን የዚህን ፊልም ሰፋ ያለዉን ጊዜ ለተመልካች ያሳዩት በጫካ፣በዋሻ እናንዲሁም ገደላገደሎች እና ዉጣዉረድ የበዛባቸዉን ቦታዎች በመምረጥ ቀረጻው ተካሂዷል። እነዚህን ቦታዎች በመጠቀማቸዉም ለታሪኩ ፍሰት ጥሩ ግብዓት የሆነበት እና በተለይም አቻም የሸፈበት ቦታ ዋሻ መደረጉ ተዓማኒነት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ ተኩስ ፣ ጦርነት የሚካሄዱት አሊያም የሚፈጠሩት በእነዚህ በተመረጡ ቦታዎች ጫካ እና ገደሎችን እንደዋነኛ ቦታ ተደርገዉ ስለሚመረጡ በዚህ ፊልም ላይም ይሄን ቦታ በመጠቀም ታሪኩን ምሉዕ ለማድረግ ተችሏል።

በተጨማሪም 00፡22፡23-00፡25፡32 ደቂቃ ላይ እነ ልዑል ጠላ ቤት ተቀምጠዉ ስለአደገበት ማህበረሰብ እያወራ ባለበት ጊዜ የልዑል ጠላት ለሆነው የአቻም ተላላኪዎች ይሄን ሚስጥር ሄደዉ ላቻም ሲነግሩት ይታያል።ይህ ትዕይንት ጠላ ቤት መሆኑም እንደዚህ አይነት ወሬ ወይም የተደበቀ ሚስጥር አብዛኛዉን ጊዜ ሊወጣ እና ሊሰማ የሚችለዉ መጠጥ ቤቶች ነዉ። ከዚህ አኳያም ይሄን ትዕይንት ገጠር እንደመሆኑ መጠን የተጠቀሙት መንገድ ወይም መቼት ጠላ ቤቷን ወይም በአካባቢው አጠራር (መሸታ) ቦታዋን በመጠቀም ከታሪኩ እና ማህበራዊ እዉነታው ጋር በማገናኘት ጉልህ ሚና ተጫዉቷል።

## 3.11 እንሳሮ ፊልም ከ ቃለ ምልልስ  አንጻር

ቃለ ፊልም በገጸ ባህርያት መካከል የቃላት ምልልስ ሲሆን ጠቀሜታዉም መቼትን ለመግለጽ ገጸ ባህርያትን ለማስተዋወቅ ማለትም አንደኛው ገጸ ባህሪይ ስለሌላኛው በሚያወራበት ወቅት ስለሌላኛው የሚገለጽበት ስልት ነዉ።በዚህም መሰረት እንሳሮ ፊልም ላይ የተካተተው ቃለ ፊልም ቦታዉን ወይም መቼቱን እንዲሁም የታሪኩን ፍሰት እና ሴራዉን ያራምድልኛል( ያስኬድልኛል) ያላቸዉን ቃለ ምልልሶች ተመልክትነናል።

ስለሆነም 00፡05፡30 ደቂቃ ላይ ሃሴት ልዑል ወደስራ ቦታ ለመዉጣት በተቀጣጠሩበት ወቅት አቻም በዕንቅልፍ ምክንያት ሲያረፍድ በዚህ ድርጊቱ የተናደደችዉ ሃሴት ስልክም አላነሳላት ሲል እንዲህ ትለዋለች።

ሀሴት

እንደው አንድ ቀን እንኳን አይሳካለት (በመሰላቸት)

በዚህ ቃለ ፊልም ላይ ሃሴት እንዲህ ስትናገረው ልዑል ሁል ጊዜ ሰአት እንደማያከብር እና አርፋጅ እንደሆነ በማዉራት የልዑልን ቅንጭብ ባህርይ ለመገለጽ ተሞክሯል።

እንዲህም 00፡06፡56 ደቂቃ ላይ ስራ አስኪያጁ ሃሴትን ለምን ሌላ ሰው አይቀየርም እና አትሄጅም ሲላት

ሀሴት

ኖ ጌች እንደዛ እማ መሆን የለበትም ልዑል ራሱ መምጣት አለበት አንደኛ ኀበዝ ካሜራ ማን ነዉ ሁለተኛ ደግሞ ከሌሎቹ በተሻለ ስለቦታዉ ኢንፎርሜሽን አለዉ።

በዚህ ቃለ ፊልምም ልዑል በስራው ትጉ ታታር እንደሆነ በዚህ ምልልስ ገጸ ባህርይ ተገንብቶበታል።

በ 00፡10፡06 ደቂቃ ላይ አቻም ከተፈታ በኋላ ተሰባስበዉ ማዕድ አየበሉ ባለበት ወቅት የአቻም አጎት ትንሽ ከተመገበ በኋላ የአቻም ወንድም የሚናገረዉን ቃለ ፊልም እንዲህ ተምልክተናል።

አቻም ወንድም

እህ ምነው አበይ ትኢት ብላይ

ክንዴ

ምኑን በላሁት ይሄ የሰው አተላ ጉድጓድ ገብቶ ሳላይ

የአቻም ወንድም

እረ ተው ተው ተው አንተ ሰው ወንድማችን ተፈርታ ብለን አመስግነን ታናበኣ

ስለሆነም ትዕይንት ዉስጥ ይሄን ቃለ ተዉኔት መጠቀሙ የቦታዉን ቲፒካል ዘዬ የተንጸባረቀበት ቃለ ምልልስ ነዉ። በተጨማሪም እንደአጠቃላይ በዚህ ፊልም ዉስጥ የሚነገሩት እና ገጸ ባህርያቱ የሚጠቀሙት ምልልስ ቦታዉን እና ማለትም እንሳሮ የሚባለዉን ቦታ የሚነገርበትን ዘዬ ጋር በማዛመድ ሲጠቀሙት ተመልክተናል። ከነዚህም መካከል 00፡41፡33 ደቂቃ ላይ እነ ማሬ ልዑልን ሲፈልጉ ባለበት ጊዜ ተኩስ ሲሠሙ ማሬ አወቀን “አወኸ” ብላ ስትጠራው ይሰማል። እናም ይህ ቃለ ፊልም ከፊልሙ መቼት ጋር መሰረት ተደርጎ የተዘጋጀ በመሆኑ መልካም ሲሆን ።ነገር ግን አልፎ አልፎ እነዚህ ቃላቶች እየተርተሱ እና ሲሸራረፉ ይታያል ።ለምሳሌ 00፡28፡22 ደቂቃ ላይ ራሷ ማሬ “አወኸ” ማለት ሲገባት አወቀ በማለት የቃለ ፊልም ፍልሰት በመፈጸም ታዓማኒነቱን ቀንሶታል።

## 3.12 እንሳሮ ፊልም ከጭብጥ አንጻር

ከፊልም ትንተና አንጻር “ጭብጥ”የተጠቃለለዉን የፊልሙን ማዕከላዊ ጉዳይ ወይም አንድ አንድ የሚያደርገዉን የትኩረት ነጥብ ያመለክታል።

የእንሳሮ ፊልም ዋነኛ ጭብጥ "በቀል" የሚለዉን በሰው ልጅ ህይወት የዕለት ትዕለት የሚከሰተዉን የኑሮ አካል ለማንጸባረቅ የታሰበ ነው።ለዚህ ማሳያም የአቻም አባኡ በክንዴ ሲሰኝነት ምክንያት ሲገደል የተመለከተዉ የተመለከተው በልጂነቱ ነበር።እናም ካደገ ብኋላ በማቄም የልዑልን ቤተሰቦች ለመግደል ይሯሯጣል።ስለሆነም የዚህ ፊልም ዋነኛ አላማው ቂም ጥላቻ መገዳደል መነታረክ ደም ከመፋሰስ ንብረት ከማዉደም በተርፈ አንዳች ፋይዳ እንደሌለው ሊያስገነዝበን የተነሳ ፊልም ነው።

እንዲሁም የዚህ ፊልም ንዑስ ጭብጦችም አሉት ከእነዚህም መካከልም ሴታዊ እኩልነት የሚለዉን በዚሁ አንተርሶ እንደጭብጥ ገብቷል።ይህን ለማለት የተፈለገዉም ወንድ ልጅ ብቻ ሳይሆን ሴት ልጅም ልክብሯ ለነጻነቷ መፋለም መዋጋት እንዲሁም መዋደቅ እንደምትችል እና ለክብር እና ፍትህ ወዳቂ እንደሆነችም በደንብ አስጨብጦናል።

## 3.13 በእንሳሮ ፊልም ዉስጥ የሴት ገጸ_ባህርያት አሣሣል ትንተና

የገጸ ባህርያት ትንተና ማለት ገጸ ባህርያቱ የተሳሉበትን ማህበራዊ፣አካላዊ፣ስነልቦናዊ እና ሞራላዊ መስፈርቶች አንጻር የሰዉ ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ጋር እያስተያዩ ትንተና መስጠት ማለት ነዉ። በዚህም መሰረት ከእነዚህ አራት እሳቤዎች አንጻር በእንሳሮ ፊልም ዉስጥ የሚገኙትን ሁለት ሴት ገጸ ባህርያትን ማለትም ማሬን እና ሀሴት የተሰኙትን ብቻ ይተነትናል።

### ማሬ

### አካላዊ አሳሳል

ማሬ ዕድሜዋ ከ 22_25 ክልል ዉስጥ የምትገኝ ምክንያቱም የልዑል ታላቅ እንደመሆኗ መጠን የልዑል እድሜ ደግሞ 26 አመቱ ነው ምክንያቱም ልዑል አባቱ ሲታሰር የ 6 አመት እንደሆነ እና አዲስ አበባ ከገባ ደግሞ 20 አመት እንደሆነው በታሪኩ ተገልጿል። ስለሆነም ከእሱ አንጻር ማሬ ቢያንስ በአምስት አመት ብትበልጠው የ 31 አመት ጎልማሳ ናት ማለት ነዉ። ስለሆነም አጥኚዉ በዚህ መሰረት እድሜዋን ለማስቀመጥ ደፍሯል። የፊት ቀለሟ በምስሉ ላይ እንደተመለከትነው ቀይ የፊት ገጽ ያላት ሆኖ በኑሮ ዉጣ ዉረድ የተከሰተ የሚመስል ከፊቷ እና አይኗ ላይ ማድያት ወይም ብልዝ ያለባት፣የተስተካከለ የሰዉነት ቅርጽ ያላት እና መካከለኛ የሆነ ቁመት ያላት ሆና ተስላለች።እንዲሁም ጸጉሯን በነጭ ሻሽ የምታስር እና የባላገር ቀሚስ የምትለብስ፣ሆና የተሳለች ገጸ ባህሪ ናት።

### ማህበራዊ አሳሳል

ማሬ በዚህ ተዉኔት ዉስጥ ቤተሰቦቿን ደጋፊ እና ያላገባች(ትዳር ያልመሰረተች) ያልተማረች ፣ምናልባት ያልተማረች የተባለበት ምክንያት የገጠር ልጅ እንደመሆኗ እና ብቸኛ ሴት ልጅ ስለሆነች እና የተማረች መሆኗን በቃለተውኔትም በታሪኩም አልተገኘም። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ከቤተሰቦቿ ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላት፣ከማህበረሰቡ ጋር ድንገት በተፈጠረ ግንኙነት የሻከረባት ፣እንዲሁም ገና ያለወለደች ተደርጋ ተስላለች።

## ስነልቦናዊ አሳሳል

በቤተሰቦቿ እና በቤተሰቦቿ ጥለኞች መካከል ያለዉን ጥል ከተቻል በሰላም ካለተቻለም በሃይል ለመመለስ የምትፈልግ ፣እንዲሁም ልዑል ከአለበት መከራ ወጥቶ መገላገልን የምትፈልግ፣ቤተሰቦቹዋን በጣም የምትወድ ፣ተደርጋ ተስላለች

## ሞራላዊ አሳሳል

ማሬ በዚህ ፊልም ላይ እጅግ ሞራላዊ ገጸ ባህርይ ተሸክማ እንድትጫወት ተደርጋለች።ከእንነዚህም መካከል ዋነኛውና አንኳሩ ነገር ማሬ በዚህ ታሪክ ላይ እጅግ ጀግና ሴት ተደርጋ ተስላለች።ለዚህ ማሳመኛም ማሬን በፊልሙ ዉስጥ የምታደርጋቸዉን ውኔያዊ የሆኑ በሴት ልጅ ክንድ የማይደረግ እና ከባድ የሆነዉን ነገር ለመከወን አቅም እና ሞራል ያላት ተደርጋ ተስላለች።

ስለዚህ ማሬ ጀግና ፣እንዲሁም የቤተሰቧን ክብር ፈላጊ ይሄም የተባለው አቻም ከተፈታ በኋል ልዑልን ሊገለው እንደሆን ስትሰማ በመናደድ እና በመባሸቅ መላው ቤተሰቡን ወክላ ስትታገል ትሞታለች። እንዲሁም ብልህ ፣አስተዋይ እና ለክብር እና ቤተሰብ ስትል ራሷን አደጋ ላይ ጥላ ስትታገል ታይቷል። ቆራጥ ይሄም ላመነችበት ወደኋላ የማትል እና የማትዎላዉል ናት።

## ሀሴት

## አካላዊ አሳሳል

ሃሴት ቀይ የቆዳ ቀለም ያላት ፣ደንደን ያለ የሰዉነት ቁመና (ቅርጽ) ያላት 33 እድሜ ክልል ዉስጥ ልትገኝ የምትችል ሆና ተስላለች ምክኒያቱም ከ ማሬ የአካልና ቁመት እንዲሁም ፊት አንጻር ስንመለከታት ከማሬ በተወሰነ መልኩ እንደምትበልጣት ያሳያል።በጣም ረዥምና ሉጫ ጸጉር ያላት ፣እንዲሁም ረዥም ቁመት ያላት ገጸ ባህሪ ተደርጋ ተስላለች።

## ማህበራዊ አሳሳል

የሀሴት ማህበራዊ ህይወት በዚህ ፊልም ዉስጥ ያን ያህል ጎልቶ እና ጎልብቶ ያልታየበት ሁኔታ አለ ። በዚህም ምክኛት ይሄ ነው ተብሎ ለምዘርዘር አስቸጋሪ ሁኔታ ቢኖርም የተገለጠዉን ለማብራራት ተሞክሯል።እንዲሁም ሃሴት የተማረች እና የጋዜጠኝነት ሙያ ያላት ሴት ናት ። ከአቻም ጋር በሚያደርጉት ቃለ ምልልስ መሰረት እንዳላገባች እና ብቸኛ እንደሆነች በተደጋጋሚ ስትናገር ተሰምቱዋል።ስለሆነም ሃሴት ያላገባች ሴት እና ልጅ የሌላት ነች። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ተደርጋ ተስላለች።

## ስነ ልቦናዊ

ሃሴት አካባቢን ቶሎ የምትለምድ እና ሰው አማኝ ነው።ለዚህ ማስረጃም አቻም ጋር እንዲያ አይኑን እያጉረጠረጠባት እንኳን እንደምንም ለመላመድ አቅሙ ስላላት በቀላሉ አሸንፋዋለች።ከዛም አልፎ ለ ፍቅር ግንኙነትም ለመድረስ ችላለች።እንዲሁም ጀግና የምትወድ እና በጀግና ቶሎ እንደምትማረክ ከሽፍታው አቻም ጋር ባደረገቸው ቅርርብ ተመልክተናል።ደስተኛ ።ሳቂታ፣ተጫዋች እና እንድሁም ካለችበት የእስር ኑሮ መገላገል የምትፈልግ አይነት ገጸ ባህሪ ተደርጋ ተስላለች።

## ሞራላዊ

ሃሴት ጥሩ የሆነ ባህሪ ያላት፣ሰዉን መዉቅስ የማትወድ ምክንያቱም በልዑል ምክንያት እንደመታሰሯ መጠን አንድ ጊዜም እንኩዋን ስትወቅሰው አልሰማንም።ቆራጥ እና ለአመነችበት የማትደክም ለምሳሌ ለመስክ ስራ ወጥተው ጠላ ቤቱ ላይ ልዑል ደመኛ እንዳለዉና አባቱ ሊፈታ እንደሆነ ሰምተው ከወጡ በኋላ ሾፌሩ እንሂድ ቢላቸዉም እንኳን ለምን እንሂዳለን ስራችንንስ የት ጥለን ነው በማለት ስትሟገት እና አቋሟን የማትሸርብ ሴት ሆና ተስላለች።

## 3.14 እንሳሮ ፊልም ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው "እንስታዊነት" ማለት ለሴቶች እኩልነት በህጋዊ መልክ እኩልነትን ለማስከበር የሚታገል ንቅናቄ ነዉ።ስለሆንም በእንሳሮ ፊልም እንስታዊነት እንዴት ተገልጿል።ያንጸባረቀው ነገርስ ምንድን ነው የሚሉትን እያነሳ ይተነትናል። ስለሆነም የሚገኙትን ገጸ ባህርያት እንድንተነትነው ምክንያት የሆነችን ጎልብታ እና ዳብራ የታየችን አንድ ገጸ ባህሪ የማርሸት (ማሬ)ናት ።በርግጥ በፊልሙ ዉስጥ ይህች ገጸ ባህሪ ብቻ ከዕንስታዊነት ዕሳቤ አንጻር ያነሳሳችን ብትሆንም በስሯ ሰፋፊ የሆኑ መልዕክቶችን ያዘለች በመሆኗ አጥኚዉ ይተነትናል።

ስለሆነም ማሬ በዚህ ፊልም ዉስጥ በማህበርሰቡ ዘንድ እንደ ዶግማ እና  ቀኖና የተቀመጡትን ህጎች በመስበር ለሌሎች ሴቶች አርዓያ እና ምሳሌ ስትሆን በዚህ ፊልም ላይ በምታደርገው ተጋድሎ ፍንትው

አድርጎ ያሳያል።ለዚህም ማሳያ ሁላችንም የማናዉቀው እና የምንስማማበት እና ብዙ የሆኑ ስለ ሴት ልጅ የተሳሳቱ አመልካከቶች አሉ።ሴት ልጅ ወደ ጓዳ ወንድ ልጅ ወደ አደባባይ የሚል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አባባል አለ በተለይም አሁን እንሳሮ ፊልም መቼቱን አድርጎ ከተሰራበት አካባቢ እና ወደ ገጠር  አካባቢ ይህ ሴትን የሚያንኳሡ እና የሚያቀጭጩ ድርጊቶችን ሙሉ በሙሉ በመስበር ትታያለች ።

00፡20፡27 ደቂቃ ላይ አቻም ከሸፈተበት ዋሻ አጠገብ ማሬ እንጨት ስትለቅም አቻም ሊተኩስባት ሲል ሴት መሆኗን አይቶ ከተዋት በኋላ እየተጠጋጥት...

አቻም፡- (የደገነዉን መሳሪያ አዉርዶ) እረግ ሴት ነሽና አሁን ተኩሸ ብላሽ ባደርግሽ ሴት የገደለ ልታሰኝኝ ኖሯል?

ማሬ፡- (ዝቅ ካለችበት በመቃናት) አሞከረዉም ኖሯል?ከጎንህ ታገኘው ነበር

አቻም፡-እመክ ተሞትሽ በኋላ ምን ታደርጊኝ ነበር በይ?

ማሬ፡-ትያይዘን እናልቃለንይ (በመናደድ) አሁን ከመንገዱ ገለል በልልኝ

በዚህ ትዕይንት ላይ ማሬን ስንመለከታት ያለችዉ ጥቅጥቅ ካለ ጫካ ላይ ነው።ነገር ግን ሴት ልጅ በተፈጥሮም ሆነ በማህበረሰቡ ጫና ልታደርገው የሚይቻላትን ተግባር ስትፈጽም ተምልክተናል።ይሄም አቻም መሳርያን ያክል ነገር ትሽክሞ በሴትነቷ እየተንጎራደደ ሊያወራት እና ሊያንጓጥጣት ቢሞክርም በተረጋጋ ስሜት እና በከፍተኛ ራስ መተማመን  እና ቀጥተኛ በሆነ መልስ ራሷን ነጻ አውጥታች።ስለሆነም በዚህ ድርጊቷ ሌሎች ሴቶች ልክ እንደ ማሬ አይነት ሁኔታ እና ገጠመኝ ቢደርስባቸው እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው አስገንዝባለች።ይሄን ማደረጓም ማለትም በራስ መተማመን ማሳየቷ ሊደርስባት የሚችለዉን ሴታዊ ጥቃት ለምሳሌ መደፈር እና መደብደብ ድርጊቶችን በማስቀረቷ እና ሴት ልጅ ለራሷ ሙብት መከበር ራሷ መቆም እንዳለባት እና ሴት ወንድ ብሎ ጾታዊ ክፍፍል የለም ሁሉም እኩል ነው የሚሉትን የእንስታዊነት ጽንስ ሃሳብ እንዳይባክን እና ስራ ላይ እንዲዉል በዚህ ድርጊቷ አሳይታለች።

በዚሁ ትዕይንት ላይ ማለትም 00፡21፡12 ደቂቃ ላይ አቻም ስለጅግንነቷ ከተረዳ በኋላ እንጨቷን ሊያሸክማት ሲሞክር ያለዉን ትዕይንት በዚህ ቃለ ተዉኔት እንመለከታለን።

አቻም፡-አይ ልበ ሙሉ ነሽና ባይሆን ወግ ወጉ ነው የተሳተሽ መቀነትሽን ሳታወልቂ ስለከተሜነት መሳለቅሽ አላዋቂነትሽን ይገልጣል።

ማሬ፡-(ቆጣ በማለት )ባታቀው ነውይ መቀነት ለቆለኛ ግብሩ ነዉ።አሁን ከመነገዱ ገለል በልልኝ

አቻም፡- (ልያሸከማት እየሞከረ)በይ ላሸክምሽ

ማሬ፡-(ቀና በማለት) አንተ ሰው አደብ ብትገዛ ይሻልሃል!!! አልያ የድፍን ለሜ መሳቂያ መሳለቂያ ነው የማደርግህ ነግሬሀለዉ።

በዚህ ሰአት አቻም በመገረም ይተዋትና ወደ ሚሄጃዋ እንድትሄድ ያደርጋታል።ስለሆነም ማሬ ከመጀገኗም በተጨማሪ አቻም ስለ መቀነት እና አለባበሷ ሲናገራት የምታምንበትን በአካባቢዋ ወግ እና ስርዐት የማትደራደር እና አሁን ባለችበት የገጠር ኑሮ ደስተኛ እና ኩሩ እንዳደረጋት በራስመተማመን ስታወራ ይሄም ይበልጥ ለሴቶች ብቻም ሳይሆን ለመላው የአካባቢው ሰዎች አርዓያ ስትሆን ይታያል።

00፡26፡46 ደቂቃ ላይ ማሬ ማዕድ ቤት ላይ ሆና ምግብ በማበሳሰል ላይ እያለች አባቷ እየሮጡ መጥተው።

አባቷ፡-ማሬ ጉድ ሆነናል

ማሬ፡-(ደንደን በማለት)ስለምን ጉድ ነው እሱ ምታወራዉ

አባቷ፡-የእህትሽ ልጅ ወንድምሽ ቤተሰቦችን ሊያጣራ ከለሜ መጥቶ ሲያጠያይቅ የአባቱ ደመኞች ሰምተው ምሽቱን ገደለው ሊቀብሩት ሲቀጣጠሩ ሰምተው አሁን መጠው ነገሩኝ

ማሬ፡-(በመጀነን) እረግ አይደረግማ እኮ እኔ ቆሜ ማን ወንድ ነው ይሄን ሚያደርግ!!!

በዚህ ቃለተዉኔት ላይ ማሬን ስንመለከታት አባቷ ይሄን ዱብዳ ሲነግራት ከመደናገጥ እና ከመደናበር ይልቅ በወኔ ስትንገሸገሽ ይታያል።ይሄም በባህላችን መሰረት ጥል ወይ ግጥሚያ ሲመጣ ለወንድ ልጅ እንጂ ለሴት ልጅ ቦታ የለዉም ነገር ግን አባቷ ዱብዳዉን ከቤት ላለው ልጅ ሳይሆን ሄዶ የነገራት ለሴቷ ማሬ ነው ስለሆነም በዚህ ጥዕይንት ላይ ሴት ልጅም ለክብሯ ለቤተሰቧ ክብር እና ነጻነት እንደምትቆም ያሳያል።

በ 00፡28፡02 ደቂቃ ላይ ማሬ መሳርያዋን አዝላ ስትወጣ አባቷ ብቻዋን እንዳትሂድና እንዲሁም ሌላ ሰው አብሯት እንዲሄድ ከዚህም ሌላ ደመኞቿ የዋዛ እና ቀላል እንዳልሆኑ ሲነግራት ባለመዳነገጥ ስሜት 'እስኪ ይድረሱብኝና መርዛቸዉን ጎልጉየ ነው የማወጣው'በማለት በወኔ ለፍልሚያ ስትወጣ ይታያል።በዚህም የተለመደው በራስ መተማመን ለቤተሰብ ክብር ማንንም ያለመስማት እና የብቻ ተጋድሎ የማድረግ አቅም እንዳላትና ሴት ልጅ የማንም እርዳታ ሳያስፈልጋት ራሷን ማስከበር እንደምትችል ፍንተው አድርጋ በማሳየት እንስታዊነትን አንጸባርቃለች።

እንዲሁም በሙሉ ፊልሙ ላይ ማሬ ጠመንጃዋን በጀርባዋ አዝላ ልዑልን ሊገለው የሚፈልገዉን ከ አቻም ለማዳን አደለም ለሴት ይቅርና ለወንድ ልጅ ሊከብድ የሚችለዉን ተራራ እና ገደል ያለምንም መቸገር ስትወጣ እና ስትወርድ እንዲሁም ምንም አይነት የመሰላቸት እና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሳይታይባት

ለወጣችበት አላማ ስትሯሯጥ ተመልክተናል።ስለሆነም ይህች ሴት ወንድ ሴት ተብለው የተከፋፈሉትን ነገሮች ሰባብራ ለመልካም ነገር ስትታገል ትታያለች።ለዚህም እንስታዊነት የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ በደንብ ሲያጠናክርልን እንመለከታለን።

00፡43፡15 ደቂቃ ላይ ልዑልን ሀሴት ጅብ ሲመጣባቸው ሁለቱም ሲደናገጡ እና ከዛም አልፎ ወንድ የሚባለው ልዑል ከሃሴት የበለጠ ሲቀጠቀጥ እና ሲፈራ እንመለከታለን።ከዚህ በተቃራኒ እነ ማሬ ልዑልን ፍለጋ ዉለው ቢመሽባቸዉም ምንም አይነት ፍራት ሳታሳይ አብሯት ያለዉን አወቀን መንገድ ስታሳየዉና እየመራቸው በስተመጨርሻም በስንት ድካምን አሰሳ እነ ልዑልን ስታገኛቸዉ ይታያል።ስለሆነም ሴት ልጅ አሁንም በዚህ ትዕይንት ምንም ነገር ቢሆን ከወንዱ እኩል አቅምና እስከመጨረሻው ሄደው አላማቸዉን ማሳካት እንደሚችሉ ያሳያል።

00፡58፡45 ደቂቃ ላይ የአቻም አጎት ከንዴ የእንግጠምና ይዋጣልን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ልጁን እንወስደዋለን ካለ በኋላ ማሬ ኮራ በማለት ወስዳችዉ ምን ልታደርጉት ነው ትለዋለች።እሱም በማፌዝ የጅል ጥያቄ ሲላት ተስፈንጥራ ጠመንጃዋን ስታነሳ እናቱግ ስትል ይታያል።ይህ ማለት እሱ አፉን እንደፈለገ ሲከፍት ሌላ ሰዎች ሲናገሩ ሳይሆን የሰማን ሴት የሆነችዉን ማሬን ነበር ።በዚህም ሴት ነኝ የሚለዉን አመልካከት ከዉስጧ በመፋቅ ለስሜቷ እና ለክብሯ ስትሟገት ይታያል። ስለሆነም እንሳሮ በተሰኘዉ ፊልም ላይ እንስታዊነትን በዚህች ማሬ በተባለች ገጸ ባህሪ በደንብ እና ጽንሰ ሃሳቡ ተግባር ላይ እንዋለ ከላይ  ባየናቸው ትንተናዎች ተገልጸዋል።

## 3.15 በእንሳሮ ፊልም ዉስጥ ያሉ ሴት ገጸ ባህርያት ከራዲካል ጽንሰ ሀሳብ አንጻር ምን ይመስላል ?

በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው ራዲካል ፌሚኒዝም በትንታኔው አባዊ ስረአት መደቆስ አለበት። በሚሉ መርሆዎች የሚመራ በመሆኑ ለውግ ጠባቂዎች በአያሌው ፈታኝ ነው።ምክንያቱም ይህ ንቅንቄ የሚያራምደው ወግ፣ባህል፣እምነት፣...የሚለው ህግ ሴቶችን ለመጨቆንና ለማሰር የመጣ ነው ብለው ያምናሉ።በዚህ ፊልም ዉስጥም ደራሲው ወይም አዘጋጁ ሆነኝ ብሎ ይሄን ንቅናቄ መሰረት አድርጎ ያዘጋጀዉ ባይሆንም አጥኝዉ ካሉት ጸንስ ሃሳቦች አንጻር ከራዲካል ፈሚኒዝም ንቅናቄ ጋር አዛምዶታል። ምክንያቱም ወንድ እና ሴት እኩል የሚለዉን እሳቤዉን ስንመለከተው በዚህ ፊልም ላይ ከዛም አልፎ ሴቷ ፊልሙ ዉስጥ ካሉት ወንዶች የበለጠ ሚዛን ስትደፋና ትኩረትን በመዉሰድ ከእኩልነትም በላይ እንደሆኑ ማሬ ባሳየችው አቅም ተመልክተናል።በተጨማሪም ባህል ወግ እንዲሁም የማህበረሰብ ጫና የሚለዉን አስተሳሰብ ይሰብራል ይህ አመለካከት ሴትን ልጅ ወደ ኋላ ለመጎተት የታሰበ ነው ብሎ የሚያምንነው ይህ ንቅናቄ ተግባራዊ ሲደረግ እንመለከታለን።ለምሳሌ ሴት ልጅ ለማጀት ወንድ ልጅ ላደባባይ የሚለዉን

ወጋዊ አስተሳሰብ በመገርሰስ ማሬ ለቤተሰቧ ክብር ጠመንጃዋን በማነገት ጋራ እና ሸንተረሩን እያቁራረጠች ስትፋለም እና ሴት ነኝ ሳይሆን ሰው ነኝ የሚለዉን አንድምታ በመያዝ እስከመጨረሻው ስትፋለም ትታያለች።ስለሆነም ራዲካል እንስታዊነትም እነዚህ ባህል፣ወግ፣እምነት እና የማህበርሰብ ህጎች ተከልለው በራሳቸው የመወሰን በራሳቸው የመተማመን እንዳያዳብሩ የሚያደርጉ ስርዓቶችን በማስወገድ እንዲሁም ሴቶች አካላዊም ሆነ አእምሮአዊ መብታቸው ከወንዱ እኩል ነው ብሎ የሚያምን በመሆኑ ከፊልሙ ጋር ተቀራራቢ እሳቤ ኖሮት ተገኝቷል።

# ምዕራፍ አራት

## 4 ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

## 4.1 ማጠቃለያ

አጥኝዉ ይሄን ጥናታዊ ጽሁፍ ማለትም እንሳሮ ፊልምን በአትኩሮት በመመልከት ትንታኔ ሰጥቶበታል ።

በዚህም ጥናታዊ ጽሁፍ ዉስጥም የፊልሙን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን በማንሳት ተንትኖታል። የፊልም ጥበብ ታሪክን በድርጊት እና በምስል ቀርጾ በተዋንያን ተተዉኖ በምስል ቅንብር ተቀናብሮ የማሳየት ጥበብ ነዉ። ስለሆነም የዚህ ጥበብ አዘጋጅ በምስል መልኩ ሊያሳየው ስለሚገባው የፊልም ዝግጅት አላባዉያን አንጻሮችን በሚገባ መመልከት እና ማጤን ይጠበቅበታል። በዚህ መሰረትም በሀገራችን ብዛት ያላቸዉ ፊልሞች ተሰርተው ለተመልካች ጠቃሚ እና ጉልህ ሚና ተጫዉተው አልፈዋል።እንሳሮ ፊልምም የፊልም ዝግጅት አላባዉያኖችን በዉስጡ ያዘለ ሲሆን የካሜራ ቀረጻ፣የግብዓተ ብርሃን፣ የትወና፣መቼት፣ቃለ ፊልም፣ምስል ቅንብር፣አልባሳት አላባዉያኖችን የተጠቀመ ሲሆን በሌላ ጎኑ ደግሞ የድምጽ ግብዓትን በአግባቡ ያልተዋቀረ የሆነበት እና እንደአጠቃላይ ግን በተለይም የምስል ቀረጻ እና ቦታ መረጣ ላይ ለሌሎች ፊልም አርዓያ ሊሆን የምችል ፊልም ነዉ።

በተጨማሪም በዚህ ፊልም ላይ ተንተርሶ9 ሴት ገጸ ባህርያትን ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር ቅኝት አድርጓል። እንስታዊነት በጽንሰ ሃሳቡ በህጋዊነት መልኩ የሴት ልጅ መብትን መከበር አለበት የሚል እሳቤ ነዉ።ስለሆነም በዚህ ፊልም ዉስጥ እንስታዊነትን ያንጸባረቀ እና ሴት ልጅ ከወንድ ጋር እኩልነት ያላት መሆኑን እንዲሁም ከዛም አልፎ ተርፎ ጠንክራ ከሰራች እና ከተጋች አንዱን ወንድ ሌላዉን ተጽዕኖ በመፍጠር እንደሚለያዩ ሁሉ ሴቷም የበላይ፣አሸናፊ፣ስኬታም፣ጠንካራ፣ብርቱ እና በራስ መተማመን መፍጠር እንደምትችል ፍንትው ተደርጎ በ ማሬ በተባለችዋ ገጸ ባህርይ በኩል በዚህ ፊልም ዉስጥ

ለመመልከት ችለናል።እንዲሁም የሴት ልጅ መዋያ ማደሪዋ ጓዳ፣ከቤት መዋል፣ከቤት ምግብ ማበሳሰል፣ ልጆችን መንከባከብ፣ልብስ ማጠብ እና አጠቃላይ የቤታቤት ስራዎችን ብቻ ለመሰራት እንጂ ለአደባባይ ወይም ወንድ ልጅ ሊሰራው የሚችለውን ስራ ሴት ልጅ መስራት የለባትም ከዛም አልፎ አትችለዉም የሚለዉን እሳቤ ተለዉጦ እና ተቃራኒ ሆኖ ማሬ መሳሪያዋን በመያዝ ከወንዱ አኩል በሆነ ወኔ ለሙብቷ እንዲሁም ለክብሯ ስትፋለም ተመልክቷል።ስለሆነም ሴት ልጅ ከወንድ እኩል አቅም እንዳላት በዚህ ፊልም ላይ ፍንትው ተደርጎ ተገልጿል።

## 4.2 የመፍትሄ ሃሳብ

አጥኚዉ ይሄን እንሳሮ የተሰኘዉን ፊልም በሚያጠናበት ወቅት ፊልሙ ከፊልም ዝግጅት አላባዉያን አንጻር በምን መልኩ ተግብሯል፣ አግባብ ባለዉ መልኩ ከመጠቀሙ አንጻር ምን ይመስላል የሚለዉን ተመልክቷል። በመሆኑም በዚህ ፊልም ላይ የተካተቱት አላባዉያኖች መልካም ነገር ያላቸዉ ቢሆኑም በዛዉም ልክ በፊልሙ ላይ የታዩ ክፍተቶችን ቢቀረፉ እና ቢስተካከሉ ብሎ ያሰበዉን ሃሳብ እንዲህ ያስቀምጣል።በፊልሙ በተካተቱት የድምጽ እና ሙዚቃ ግብዓት አንጻር ደከም ያለ እና በተለይም የመቆራረጥ ነገር በተደጋጋሚ በፊልሙ ላይ የተፈጠረ ችግር ሆኖ ታይቷል።ስለሆነም በዚህም ምክንያት የፊልሙን ድባብ አንኳሶታል።ስለዚህ አግባብ ያለዉና ቦታዉን የሚወክል (ገጠር) እንደመሆኑ መጠን ያንን ቦታ በደንብ ሊወክል የሚችል ነገር በመጠቀም ፊልሙን ከዚህ የበለጠ በደንብ ጠንካራ ያደርገዉ ነበር።

እንዲሁም ዋና ያልሆኑ ማለትም እንደ አጃቢ ተዋንያን የተካተቱ ገጸ ባህርያት ላይ አልባስን ማልበስን እንጅ የገጽ ቅብ ስልት ላይ የላላ እና ክፍተት የነበረብት ሆኖ ታይቷል ስለሆነም ይሄንንም በደንብ ቢታሰብበት ኖሮ ይበልጥ ምስል ከሳች የመሆን እድሉ ይሰፋ ነበር።

በሰተመጨረሻም የሮጠ እና የተራመደ አንድ አይደሉም እና ፊልሙ በአብዛኛዉ መልካም ጎኖች የተስተዋሉበት ነዉ። ስለዚህ እንሳሮ ፊልምም ለተቀማጭ አንጋጣጮች እየሮጠ መንገድ ከፋች ፊልም ይሆናል እላለሁ።

## ዋቢ መጽሃፍት


አዲስ ተስፋየ። የፊልም ድርሰት አጻጻፍ ብልሃት ።አዲስ አበባ።ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት፣(2005)

ኤልያስ ጋሻዉ ማንኩልህ። ስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛው ህግጋት ባሻገር ።አዲስ አበባ።ነጭ ሳር . ማተሚያ ድርጅት ። (2007)

ቤተልሄም ነጋሽ ።የእንስታዊነት ምንነት። አዲስ ማለዳ።አዲስ አበባ።(2012)

ዘላለም ተፈሪ። የፊልም ትወና ጥበብ።አዲስ አበባ።ፋር ኢስት ትሬዲንግ ።(2010)

ወሰን የለህ ጥላሁን፣ የፊልም ጥበብ ቅኝት።አዲስ አበባ።ፋር ኢስት ትሬዲንግ።(2005)


ፋንታሁን እንግዳ። የተዉኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ።አዲስ አበባ ።(2009)

ጳዉሎስ አዕምሮ። የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ ።አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ።(2010)

ዘሪሁን አስፋዉ። የስነ-ጽሁፍ መሰረታዉያን ።አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ።ንግድ ማተሚያ ድርጅት(2005)

## አባሪ

### የእንሳሮ ሴቶች ባህላዊ አለባበስ



በፊልሙላይ የተጠቀመች አልባስ

የእንሳሮ አካባቢ





እጅግ በጣም የሩቅ ቀረጻ

የእንሳሮ አካባቢ

አለባበስ





ፊልሙ ላይ የተወሰደው  አልባስ





የልከኛ ማዕዘን ቀረፃ





የወፍ እይታ ቀረጻ (bird eye view)





የእንሳሮ አካባቢ ወጣቶች ባህላዊ አለባበስ

በፊልሙ ላይ የተጠቀሙት አልባስ



የሰያፍ ማዕዘን ቀርጻ



።



ከትከሻ በላይ ቀረጻ

Pov



